# ኦሪት ዘመሳፍንት

ምዕራፍ ፩።

፩ ወኮነ እምድኅረ ሞተ ኢያሱ ተስእሉ ደቂቀ እስራኤል
ኀበ እግዚአብሔር እንዘ ይብሉ መኑ የዐርግ ለነ ኀበ ከና
ኔዎን መልእከ ዘይትቃተሎሙ ለነ።
፪ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ይሁዳ ይዕርግ ወናሁ አግ
በእክዋ ለምድር ውስተ እዴሁ።
፫ ወይቤሎ ይሁዳ ለስምዖን እኁሁ ዕርግ ምስሌየ በው
ስተ መክፈልትየ ወንትቃተሎሙ ለከነአን ወአሐውር አነኒ
ምስሌከ በውስተ መክፈልትከ ወሖረ ስምዖን ምስሌሁ።
፬ ወዐርገ ይሁዳ ወአግብኦሙ እግዚአብሔር ለከናኔዎን
ወለፌርዜዎን ውስተ እዴሁ ወቀተሎሙ በባዜቅ አልፈ
ብእሲ።
፭ ወረከብዎ ለአዶንቤዜቅ በባዜቅ ወተቃተልዎ ወቀተ
ልዎሙ ለከናኔዎን ወለፌርዜዎን።
፮ ወጐየ አዶንቤዜቅ ወዴገንዎ ወተለውዎ ወአኀዝዎ
ወመተሩ አርእስተ እደዊሁ ወእገሪሁ።
፯ ወይቤሎሙ አዶንቤዜቅ ዘሰብዓ ነገሥት አርእስተ እደ
ዊሆሙ ወእገሪሆሙ ምቱራት ሀለዉ እስተጋቢእየ በታ
ሕተ ማእድየ ወበከመ ገበርኩ ከማሁ ፈደየኒ እግዚአብ
ሔር ወወሰድዎ ኢየሩሳሌም ወሞተ በህየ።

፰ ወተቃተሉ ደቂቀ ይሁዳ ምስለ ኢየሩሳሌም ወአስተ
ጋብእዋ ወቀተልዋ በአፈ ሐፂን ወአውዐዩ ሀገራ በእሳት።

፱ ወእምዝ ወረዱ ደቂቀ ይሁዳ ይትቃተልዎሙ ለከናኔ
ዎን እለ ይነብሩ ውስተ አድባር።
፲ ወሖረ ይሁዳ ውስተ ከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስተ ኬብ
ሮን ወወፅኡ ሰብአ ኬብሮን ወተቀበልዎሙ ወስማ ለኬብ
ሮን ትካት ቀርያርበቃሴፌር ወቀተልዎሙ ለሴሲ ወለኡኪ
ማም ወለታሚን ትውልደ ኤናቅ።

፲፩ ወሖሩ እምህየ ኀበ እለ ይነብሩ ዳቤር፡ ወስማ ለዳቤር
ትካት ሀገረ መጽሐፍ።
፲፪ ወይቤ ካሌብ ለዘቀተላ ለሀገረ መጽሐፍ ወአስተጋብኣ
እሁብ አስካሃ ወለትየ ትኩኖ ብእሲተ።
፲፫ ወአስተጋብኣ ጎቶንያል ወልደ ቄኔዝ እኁሁ ለካሌብ
ዘይንእስ ወወሀበ አስካሃ ወለቶ ትኩኖ ብእሲተ።
፲፬ ወሶበ ለሐዊር አምከራ ጎቶንያል ትስእሎ ለአቡሃ ይጸ

ምዕራፍ ፩።

ኢያሱ ከሞተ በኋላ እንዲህ ሆነ፤ ወደ ከናኔዎን ወጥ
ቶ የሚዋጋልን አለቃ ማነው፤ ብለው የእስራኤል ልጆች
ወደ እግዚአብሔር ጠየቁ። ዘኁ፡ ፳፯ ፳፩።
እግዚአብሔርም ይሁዳ ይዝመት፤ እነሆ ከነዓንን በ
እጁ አግብቼለታለሁ አላቸው። መሳ፡ ፳ ፲፰።
ይሁዳም ወንድሙ ስምዖን በኔ ዕጣ ከኔ ጋራ ውጣ፤
(ዝመት) የከነዓንን ሰዎች እንዋጋቸው፤ እኔም በንተ ዕጣ
ከንተ ጋራ እሄዳለሁ አለው፤ ስምዖንም ከሱ ጋራ ሄደ።
ይሁዳም ዘመተ እግዚአብሔርም ፌርዜዎንንና ከናኔ
ዎንን በእጁ ጣላቸው፤ በባዜቅም አጠፋቸው፤ እነዚህም
አልፍ (ዓሥር ሺሕ) ሰዎች ናቸው። ፩ ሳሙ፡ ፲፩ ፰።
አዶንቤዜቅም አግኝተው ተዋጉት፤ ፌርዜዎንንና ከና
ኔዎንንም አጠፉዋቸው።
አዶንቤዜቅም ሸሸ አሳድደውም ያዙት፤ የእጆቹንና
የእግሮቹንም ጣቶች ቈረጡ።
አዶንቤዜቅ የእግሮቻቸውንና የእጆቻቸውን ጣቶች
የተቈረጡ ሰባ ነገሥታት ሰብስቤ ጕልበት ገበታዬን ስመ
ግባቸው ነበር፤ እኔም እንዳደረግሁ እግዚአብሔር እንደ
ዚያው መለሰልኝ (ከፈለኝ) አላቸው፤ ወደ ኢየሩሳሌምም
ወሰዱት፤ በዚያም ሞተ። መሳ፡ ፩ ፯። ሩት ፪ ፮።
የይሁዳም ልጆች ከኢየሩሳሌም ሰዎች ጋራ ተዋጉ፤
በጦር መግተውም እጅ አደረጓት፤ አገሯንም በእሳት
አቃጠሉ። ኢያ፡ ፲፭ ፷፫።
ከዚህም በኋላ የይሁዳ ልጆች በተራራዎች የሚኖ
ሩት ከናኔዎንን ይዋጉዋቸው ዘንድ ወረዱ። ኢያ፡ ፱ ፩።
ይሁዳም በኬብሮን ወደ ሚኖሩ ወደ ከናኔዎን ሄደ፤
የኬብሮንም ሰዎች መጥተው ተቀበሉዋቸው (ገጠሙዋ
ቸው) ጥንትም የኬብሮን ስሟ ቀርያር በቃሴፌር ይባል
ነበር፤ የኤናቅንም ልጆች ኡኪማምንና ሴሲን ታሚንን
አጠፉዋቸው። ኢያ፡ ፲ ፵፮፤ ፲፩ ፳፩።
ከዚያም በዳቤር ወደ ሚኖሩ ሰዎች ሄዱ፤ የዳቤርም
ጥንተ ስሟ የወግ የታሪክ አገር ይባል ነበር።
ካሌብም የወግ የታሪክ አገርን ወግቶ እጅ ላደረጋት
ሰው ሚስት ልትሆነው ልጄ አስካን እሰጠዋለሁ አለ።
የካሌብ ታናሽ ወንድሙ የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያልም ወግ
ቶ እጅ አደረጋት ሚስትም ልትሆነው ልጁ አስካን ሰጠው።
ለመሄድም በተነሣ ጊዜ ጎቶንያል መሠማሪያ ቦታን

ግዋ ዓፀደ ወፍር፡ ወአንጐርጐረት በዲበ አድግ ወጸርሐት ወትቤ ውስተ ብሔረ አዝያብ ፈነውከኒ፡ ወይቤላ ካሌብ ምንተ ኮንኪ ።

እንዲሰጣት አባቷን ትለምነው ዘንድ መከራት፡ በበቅሎዋም ላይ ሁና አንጐራጐረች፡ ወደ በረኻ አገር ሰደድከኝ ብላ ጮኸች፡ ካሌብም ምን ሆንሽ፧ አላት ።

፲፭ ወትቤሎ አስከ ሀበኒ በረከተ እስመ ብሔረ አዝያብ ፈነውከኒ ወሀበኒ ቤዛ ማይ፡ ወወሀበ ካሌብ በከመ ትፈቱ በልበ ቤዛ ሕሙም ወቤዛ ትኩዝ ።

እስካም ወደ በረኻ ሰደኸኛልና በረከትን (ጕልት)፡ ስጠኝ ውኃ የማጣቴንም ዋጋ ስጠኝ አለችው፡ ካሌብም በልቧ እንደ ተመኘች የኃዘንዋንና የመከራዋን ዋጋ ሰጣት።

፲፮ ወደቂቀ ዮባብ ቄንያዊ ሐሙሁ ለሙሴ ዐርጉ እምሀገረ ፈንቆን ኀበ ደቂቀ ይሁዳ ውስተ ሐቅለ ይሁዳ ዘመንገለ አዜብ ውስተ ሙራደ አራድ ወሖረ ወነበረ ምስሌሆሙ ።

የሙሴ አማት የቄንያው ሰው የዮባብ ልጆችም ፊንቆን ከሚባል አገር በአራድ መውረጃ ግራ አንጻር ወዳለች ወደ ይሁዳ ዕጣ ከይሁዳ ልጆች ዘንድ ወጡ፡ እሱም ሄዶ ከወገኖቹ ጋራ ተቀመጠ ። መሳ፡ ፬ ፲፩ - ፲፯ ።

፲፯ ወሖረ ይሁዳ ምስለ ስምዖን እኁሁ ወቀተልዎሙ ለከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስተ ሴፍር ወአሕረምዋ ወአጥፍእዋ ።

ይሁዳም ከወንድሙ ከስምዖን ጋር ሄደ፡ በሴፍር የሚኖሩ ከናኔዎንን አጠፋቸው አገሪቱንም ሕርም ብለው አጠፉዋት ። ሙሴ፡ ፩ ፫ ። ፪ ዜና መ፡ ፲፬ ፲ ።

፲፰ ወኢተዋረሰ ይሁዳ ለጋዛን ወለደወላ ለአስቃሎና ወለደወላ ለአቃሮን ወለደወላ ለአዛጦን ወለደወላ ወሙፋሬቲሃ ።

ይሁዳም ጋዛን ከአውራጃዋ ጋር አስቃሎናን ከአውራጃዋ ጋር አቃሮንን ከአውራጃ ጋራ አዛጦንን ከአውራጃዋና ከመሠማሪያዎቿ ጋር አልወረሳትም ።

፲፱ ወሀለወ እግዚአብሔር ምስለ ይሁዳ ወተዋረሰ ደብረ ወስእነ ተዋርሶቶሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ ቈላት እስመ ሠረገላተ ሐፂን በሙ ።

እግዚአብሔር (በረድኤት) ከይሁዳ ጋራ ኖረ፡ ደጋውንም ወረሰ፡ የብረት ሠረገላዎች ነበሯቸውና በቈላ የሚኖሩ ሰዎች ግን መውረስ አልተቻለውም ።

፳ ወወሀብዎ ለካሌብ ኬብሮን በከመ ይቤ ሙሴ ወተዋረሰ እምህየ ሠለሰ አህጉረ ወአሰሰሎሙ እምህየ ለሠለስቱ ደቂቀ ኤናቅ ።

ለካሌብም ሙሴ እንዳዘዘ ኬብሮንን ሰጡት፡ ከዚያም ሠላሳ አገሮችን ወረሰ፡ ከዚያም ሦስቱን የኤናቅ ልጆችን አጠፋቸው ። ዘኍ፡ ፲፬ ፳፬ ። ዘዳ፡ ፩ ፴፯ ።

፳፩ ወለኢያቡሴዎን እለ ይነብሩ ውስተ ኢየሩሳሌም ኢያሰሰልዎሙ ደቂቀ ብንያሚ ወነበሩ ኢያቡሴዎን ምስለ ደቂቀ ብንያሚ እስከ ዛቲ ዕለት ።

በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢያቡሴዎንን ግን የብንያም ልጆች አላጠፉዋቸውም፡ ኢያቡሴዎንም እስከዚች ቀን ድረስ ከብንያም ልጆች ጋራ ኖሩ ።

፳፪ ወዐርጉ ደቂቀ ዮሴፍ እሙንቱኒ ውስተ ቤቴል ወእግዚአብሔር ምስሌሆሙ ወተዐየኑ ወርእይዋ ለቤቴል ወስማ ለይእቲ ሀገር ትካት ሉዛ ።

እነዚያም የዮሴፍ ልጆች ወደ ቤቴል ወጡ፡ እግዚአብሔርም (በረድኤት) ከነሱ ጋር ነበረ፡ ተከማችተውም ቤቴልን አዩዋት የዚያችም አገር ጥንት ስሟ ሉዛ ይባል ነበር ። ዘኍ፡ ፲፱ ፯ ። ሙሴ፡ ፲፰ ፯ ።

፳፫ ወርእዩ ሰብአ ማዕቅብ ብእሴ እንዘ ይወፅእ እምሀገር ወአኀዝዎ ወይቤልዎ አርእየነ ምብዋአ ለሀገር ወንገብር ምሕረተ ምስሌከ ።

አምባን የሚጠብቁ ሰዎች አንድ ሰው ከከተማው ሲወጣ አይተው ይዘው የከተማይቱን መግቢያ አሳየን ላንተ (ምሕረት) ወረታን እናደርግልሃለን አሉት ።

፳፬ ወአርአዮሙ እንተ ኀበ ይበውእዋ ለሀገር ወቀተልዋ ለይእቲ ሀገር በአፈ ሐፂን ወለዝክቱሰ ብእሲ ወለአዝማዲሁ አግዐዝዎሙ ።

ከተማይቱን የሚገቡባትንም አሳያቸው፡ ያችንም አገር በጦር አጠፉዋት፡ ያንን ሰውና ዘመዶቹን ግን ነፃ አወጡዋቸው ።

፳፭ ወእተወ ውእቱ ብእሲ ውስተ ምድረ ኬጤኤን ወነደቀ በህየ ሀገረ ወሰመየ ስማ ሉዛ ወውእቱ ኮነ ስማ እስከ ዮም ።

ያም ሰው ወደ ኬጤኤን አገር ገብቶ በዚያች ከተማ ሠራ፡ ስሟንም ሉዛ አላት፡ ስሟም እስካሁን ድረስ ሉዛ ተባለ ። ኢያ፡ ፩ ፱ ። ፩ ነገ፡ ፰ ፯ ።

፳፮ ወኢተዋረሰ ምናሴ ቤተሰን እንተ ሀገረ ሰቂቶን ወአዋልዲሃ ወኢጺአታቲሃ ወኢቀጸአድ ወአዋልዲሃ ወኢ እለ ይነብሩ ውስተ አዶር ወአዋልዲሃ ወኢ እለ ይነብሩ ውስተ በለዓም ወአዋልዲሃ ወኢ እለ ይነብሩ ውስተ መጌዶ ወአዋልዲሃ ወኢ እለ ይነብሩ ውስተ ዮበለዓም ወአዋልዲሃ ወአኀዙ ከነአን ይንበሩ ውስተ ይእቲ ምድር ።

ምናሴም በሰቂቶን አገር ያለች ቤተሰንን ከጥቃቅን አገሮችዋ ጋራ ኢቀጸአድንም ከጥቃቅን አገሮቿ ጋር በአዶር የሚኖሩትንም ከጥቃቅን አገሮቿ ጋራ፡ በበለዓም የሚኖሩትንም ከጥቃቅን መንደሮቿ ጋራ፡ በመጌዶ የሚኖሩትንም ከጥቃቅን አገሮቿ ጋራ፡ በዮበለዓም የሚኖሩትንም ከጥቃቅን መንደሮቿ ጋራ አልወረሰም፡ የከነዓንም ሰዎች በዚያች አገር ይኖሩ ጀመር ። ኢያ፡ ፲፯ ፲፩ ፲፫ ።

፳፯ ወእምዝ ሶበ ጸንዑ እስራኤል መጸብሔ ረሰይዎሙ ለከነአን ወአጥፍእሰ ኢያጥፍእዎሙ ።

ከዚያ በኋላ እስራኤል በጸኑ ጊዜ የከነዓንን ሰዎች ገባር አደረጉዋቸው፡ ማጥፋትን ግን አላጠፏቸውም ።

፳፰ ወኤፍሬምኒ ኢያጥፍእዎሙ ለከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስተ ጋዜር ወነበሩ ከናኔዎን ማእከሎሙ ውስተ ጋዜር

የኤፍሬምም ነገድ በጋዜር የሚኖሩ ከናኔዎንን አላጠፉዋቸውም፡ ከናኔዎንም በጋዜር በመካከላቸው ኖሩ፡ ገባር

ወክንዎሙ መጸብሐ ።

፳፱ ወዘብሉንሂ ኢያጥፍእዎሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ ቄድ
ሮን ወለእለ ይነብሩ ውስተ ኢማን ወነበሩ ከናኔዎን ማእከ
ሎሙ ወኮንዎሙ መጸብሐ ።

፴ ወአሴርሂ ኢያጥፍእዎሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ አክ
ወኮንዎሙ መጸብሐ ወለእለ ይነብሩ ውስተ ዶሬ ወለእለ
ይነብሩ ውስተ ዶላፍ ወእለ ይነብሩ ውስተ ሲዶና ወእለ
ይነብሩ ውስተ አስከድ ወኬድያ ወአፌቅ ወሮአብ ።

፴፩ ወነበረ አሴር ማእከለ ከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስተ ይ
እቲ ምድር እስመ ስኢኑ አጥፍኦቶሙ ።

፴፪ ወንፍታሌምሂ ኢያጥፍእዎሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ
ቤተ ሳሚስ እስመ ስእኑ አጥፍኦቶሙ ወኢ እለ ይነብሩ
ውስተ ቤቴኔስ ወነበሩ ማእከሎሙ ከናኔዎን ለእለ ሀለዉ
ውስተ ይእቲ ምድር ወኮንዎሙ መጸብሐ እለ ይነብሩ
ውስተ ቤተ ሳሚስ ወውስተ ቤቴኔስ ።

፴፫ ወአጠቅዎሙ አሞሬዎን ለደቂቀ ዳን በውስተ አድባር
እስመ ኢያበውሕዎሙ ይረዱ ውስተ ቈላት ።

፴፬ ወአኀዙ አሞሬዎን ይንበሩ ውስተ ደብረ መርስኖኖስ
ዘበ ውስቴቱ ድብ ወቈናጽል ወጸንዐት እዴሆሙ ለቤተ
ዮሴፍ ላዕለ አሞሬዎን ወኮንዎሙ መጸብሐ ።

፴፭ ወደብረ አሞሬዎን ወኢዶሜዎን ላዕላይ ዘአቅራቢን
እለ ውስተ ላዕለ ኰኵሕ ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩ ወዐርገ መልአከ እግዚአብሔር እምገልገላ ላዕለ ቀለው
ትሞኖስ ወላዕለ ቤቴል ወላዕለ ቤተ እስራኤል ወይቤሎሙ
እግዚአብሔር ይቤ አውፃእኩክሙ እምግብጽ ወአበእኩ
ክሙ ውስተ ምድር ዘመሐልኩ ለአበዊክሙ ከመ እሁብክ
ሙ ወእቤለክሙ ኢየኀድግ ኪዳንየ ዘምስሌክሙ ለዓለም ።

፪ ወአንትሙኒ ኢትትከየዱ ኪዳነ ምስለ እለ ይነብሩ
ውስተ ዛቲ ምድር ወኢ ለአማልክቲሆሙ ወኢትስግዱ
ሎሙ ወኢ ለግልፎሆሙኒ ቀጥቅጡ ወምሥዋዒሆሙኒ
ንሥቱ ወኢሰማዕክሙኒ ቃልየ እመ ገበርክሙ ዘንተ ።

፫ ወአንሂ እቤ ኢይደግም አሰስሎቶሙ ለአሕዛብ እለ እቤ
ከመ አውፅኦሙ እምቅድሜክሙ ወይከውኑክሙ ለኀዘን
ወአማልክቲሆሙኒ ይከውኑክሙ ለዕቅፍት ።

፬ ወእምዝ ሶበ ይቤሎሙ መልአከ እግዚአብሔር ለኵሉ
እስራኤል ዘንተ ነገረ ጸርሐ ኵሉ ሕዝብ ወበከየ ።

፭ ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየ ስሙ ለውእቱ መካን መካነ
ብካይ ፤ ወሦዑ በህየ ለእግዚአብሔር ።

፮ ወፈነዎሙ ለሕዝብ ወአተዉ ደቂቀ እስራኤል ኵሎ
ሙ ውስተ አብያቲሆሙ ወውስተ ርስቶሙ ከመ ይትዋረ
ስዋ ለምድር ።

፯ ወተቀንዩ ሕዝብ ለእግዚአብሔር በኵሉ መዋዕሊሁ
ለኢያሱ ወበኵሉ መዋዕሊሆሙ ለሊቃናት ወኵሉ እለ

ንም ሁኑዋቸው ። ኢያ፣ ፲ ፴፫ ፣ ፲፯ ፲ ።

የዛብሉንም ነገድ በአማን የሚኖሩትንና በቄድሮን
የሚኖሩትን ሰዎች አላጠፉዋቸውም ፤ ከናኔዎንም በመካከ
ላቸው ኖሩ ፤ ገባርንም ሆኑዋቸው ።

ነገደ አሴርም በአክ የሚኖሩትን ሰዎች አላጠፉዋቸ
ውም ፤ ገባርንም ሆኑዋቸው ፤ በዶላፍ የሚኖሩ ሰዎችንና
በዶር የሚኖሩትን ሰዎች ፤ በአስከድ የሚኖሩትንና በሲ
ዶና ፤ በአፌቅና በኬድያ የሚኖሩትን በሮኦብም የሚኖሩ
ትን ሰዎችን አላጠፉዋቸውም ። ኢያ፣ ፲፱ ፲፰ - ፴፰ ።

አሴርም እነሳቸውን ማጥፋት ተስኖታልና በዚያች
አገር በሚኖሩ በከናኔዎን መካከል ኖረ ። ኢያ፣ ፲፱ ፴፰ ።

የንፍታሌም ነገድ እነሳቸውን ማጥፋት ተስኖአቸዋ
ልና በቤተ ሳሚስ የሚኖሩትን ሰዎች አላጠፉዋቸውም ፤
በቤቴኔስ የሚኖሩትን ሰዎች አላጠፉዋቸውም ፤ ከናኔዎ
ንም በዚያች አገር በሚኖሩት ሰዎች መካከል ኖሩ ፤ በቤ
ቴኔስና በቤተሳሚስ የሚኖሩ ሰዎች ገባር ሆኑዋቸው ።

አሞሬዎንም ወደ ቈላ ይወርዱ ዘንድ አላሰናበቱዋቸ
ውምና በደጋ የሚያስጨንቋቸው የዳንን ልጆች በቈላ አስ
ጨነቋቸው ። ኢያ፣ ፲፱ ፵ ። መሳ፣ ፲፰ ፩ ።

አሞሬዎንም ቀበሮችና ድብ በሉበት በመርስኖኖስ
ተራራ ይኖሩ ጀመር ፤ የዮሴፍም ነገድ ሥልጣን በአሞሬ
ዎን ላይ ጸናች ፤ ገባርንም ሆኑዋቸው ።

በዋሻ የሚኖሩ የአቅራቢን ዕጣ የሚሆኑ በላይኛው
ኤዶሜዎንና በአሞሬዎን የሚኖሩ ሰዎች ገባር ሆኑዋቸው ።

ምዕራፍ ፪ ።

ከእግዚአብሔር የተላከ መልአክ ከገልገላ ወደ ቤቴ
ልና ወደ ቀለውትሞኖስ ወደ እስራኤልም ወገን መጥቶ
እግዚአብሔር ከግብጽ አውጥቼ እሰጣችሁ ዘንድ ለአበቶ
ቻችሁ ወደ ማልኩላቸው አገር መሐላዬንም ለዘለዓለሙ
አላፈርስባችሁም አልኋችሁ ። ዘጸ፣ ፴፩ ፲፯ ።

እናንተም በዚች አገር ከሚኖሩ ሰዎች ጋራ መሐላን
አትማማሉ ለጣኦቶቻቸውም አትስገዱላቸው ፤ ጣኦቶቻቸ
ውን ስበሩ ፤ መሠውያቸውንም አፍርሱ አልኋችሁ ፤ ነገር
ግን ቃሌን አልሰማችሁኝም ፤ ይህንን ብታደርጉ ።

እኔም ከፊታችሁ አወጣቸው ዘንድ አወጣቸዋለሁ
ያልኳቸው አሕዛብን ዳግመኛ አላጠፋቸውም ፤ ለኃዘንም
ይሆኑዋችኋል ፤ ጣኦቶቻቸውም መሰናከል ይሆኑባችኋል
አልሁ አለ አላቸው ። ዘኍ፣ ፴፫ ፶፭ ። ኢያ፣ ፳፫ ፲፫ ።

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር የላከው መልአክ ይህንን
ነገር ለእስራኤል ሁሉ በነገራቸው ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ጮኸ
አለቀሰ ።

ስለዚህም ነገር የዚያ ቦታ ስሙ የልቅሶ ቦታ ተባለ ፤
በዚያም ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ሠዉ ።

ሕዝቡንም አሰናበቱዋቸው ፤ የእስራኤል ልጆች ሁሉ
ወደ ቤቶቻቸው ምድራቱንም (ከነዓንን) ይወርሷት ዘንድ
ወደ ርስታቸው ገቡ ። መሳ፣ ፪ ፲ ።

ሕዝቡም በኢያሱ ዘመን ሁሉ በአለቆችም ዘመን ሁሉ
ለእግዚአብሔር ተገዙ ፤ ለእስራኤል ያደረገው የእግዚአብ

ኖኅ መዋዕሊሆሙ እምድኅረ ኢያሱ ኵሎሙ ዘአእመሩ
ኵሎ ግብረ እግዚአብሔር ዐቢየ ዘገብረ ለእስራኤል ።
፰ ወሞተ ኢያሱ ወልደ ነዌ ገብረ እግዚአብሔር እንዘ
ወልደ ምእት ወዓሠርቱ ዓመት ።
፱ ወቀበርዎ ውስተ ደብረ ርስቱ ውስተ ተምናሥራሕ
ውስተ ደብረ ኤፍሬም እምንገለ መስዕ ለደብረ ገዓስ ።
፲ ወኵላ ይእቲ ትውልድ አተዉ ኀበ አበዊሆሙ ወተን
ሥአት ካልእት ትውልድ እምድሬሆሙ ኵሉ እለ ኢየአ
ምርዎ ለእግዚአብሔር ወግብረ ዘገብረ ለእስራኤል ።

፲፩ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል እኪተ ቅድመ እግዚአብሔር
ወአምለኩ በዓሊምሃ ።
፲፪ ወኀደግዎ ለእግዚአብሔር አምላከ አበዊሆሙ ዘአው
ፅአሙ እምድረ ግብጽ ወተለዉ ባዕዳነ አማልክተ አሕዛብ
እለ ዐውዶሙ ወሰገዱ ሎሙ ወአምዕዕዎ ለእግዚአብሔር ።
፲፫ ወኀደግዎ ለእግዚአብሔር ወአምለክዎሙ ለበዓሊም
ወለአስጠራጢን ።
፲፬ ወተምዐ እግዚአብሔር መዐተ ላዕለ እስራኤል ወእግ
ብአሙ ውስተ እደ እለ ይፄውውዎሙ ወፄወውዎሙ ወአ
እተውዎሙ ውስተ ምድረ ፀሮሙ እለ ዓውዶሙ ወኢክ
ህሉ ተቃውሞ ቅድመ ፀሮሙ በኵሉ ዘበርበርዎሙ ።

፲፭ ወእደ እግዚአብሔር ላዕሌሆሙ በእኪት በከመ ይቤ
እግዚአብሔር ወበከመ መሐለ እግዚአብሔር ወሣቀዮሙ
ጥቀ ።
፲፮ ወአቀመ እግዚአብሔር መሳፍንተ ወአድኀኖሙ እም
እደ እለ ፄወውዎሙ ።
፲፯ ወለመሳፍንቲሆሙኒ ኢሰምዕዎሙ እስመ ዘመዉ ወተ
ለዉ አማልክተ ባዕድ ወሰገዱ ሎሙ ወአምዕዕዎ ለእግዚ
አብሔር ወኀደግዋ ፍጡነ ለፍኖት እንተ ባቲ ሖሩ አበዊ
ሆሙ ከመ ኢይስምዑ ቃለ እግዚአብሔር ወኢገብሩ
ከማሁ ።
፲፰ ወሶበ አቀመ ሎሙ እግዚአብሔር መሳፍንተ ወሀለወ
እግዚአብሔር ምስለ ውእቱ መስፍን ወአድኀኖሙ እም
እደ ፀሮሙ በኵሉ መዋዕሊሁ ለውእቱ መስፍን እስመ
ተሣሀሎሙ እግዚአብሔር እምሕማሞሙ በቅድመ እለ
ይትቃተልዎሙ ።
፲፱ ወአምዝ ሶበ ሞተ ውእቱ መስፍን ይገብኡ ካዕበ ወይ
ኤብሱ ፈድፋደ እምአበዊሆሙ ወየሐውሩ ወይተልዉ ድ
ኅረ አማልክተ ባዕድ ወያመልክዎሙ ወይሰግዱ ሎሙ
ወኢየኀድጉ እከዮሙ ወኢይገብኡ እምፍኖቶሙ እኪት።

፳ ወተምዐ እግዚአብሔር መዐተ ላዕለ እስራኤል ወይቤ
እስመ ኀደጉ እሉ ሕዝብየ ኪዳንየ ዘአዘዝክዎሙ ለአበዊ
ሆሙ ወኢሰምዑ ቃልየ ።
፳፩ ወአነኒ ኢይደግም እንከ አሰስሎ ብእሴ እምኔሆሙ
ወእምቅድሜሆሙ እምነ አሕዛብ እለ አትረፈ ኢያሱ ።
፳፪ ወኀደጎሙ ከመ ያመክሮሙ ቦሙ ለእስራኤል እመ
የዐቅቡ ፍኖተ እግዚአብሔር ወየሐውሩ ባቲ በከመ ዐቀቡ

ሔርን ብዙ ተአምራት ሁሉ ያወቁ፣ ከኢያሱ በኋላ ዘመና
ቸው የበዛ ሰዎችም ሁሉ ተገዙ ። ኢያ፣ ፳ ፩ - ፴፩ ።
የእግዚአብሔር አገልጋይ የነዌ ልጅ ኢያሱም መቶ
ዓሥር ሲሆነው ሞተ ።
በገዓስ ተራራ ቀኝ አንጻር በነገደ ኤፍሬም ዕጣ ባለች
ርስቱ በምትሆን በተምናሥራሕ ቀበሩት ።
እነዚያም ወገኖች ሁሉ ሙተው አባቶቻቸው ወደ
ተቀበሩበት መቃብር ገቡ፣ (ተቀበሩ) ከነሳቸውም በኋላ
እግዚአብሔርን የማያውቁት ለእስራኤል ያደረገውንም
ተአምራት የማያውቁ ሌሎች ትውልድ ተነሡ ።
የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ
ሠሩ፣ በዓሊም የተባለ ጣኦትንም አመለኩ ።
ከግብጽ ያወጣቸው የአባቶቻቸው ፈጣሪ እግዚአብ
ሔርን ትተው በዙርያቸው ያሉ ልዩ የሆኑ የአሕዛብን ጣኦ
ታት አምልከው ሰገዱላቸው፣ እግዚአብሔርንም አሳዘኑት።
እግዚአብሔርንም ትተው አስጠራጢንንና በዓሊምን
አመለኩዋቸው መሳ፣ ፪ ፲፩ ። መዝ፣ ፻፮ ፴፮ ።
እግዚአብሔርም በእስራኤል ቍጣን ተቈጥቶ በሚማ
ርኩዋቸው ሰዎች እጅ ጣላቸው፣ እነሱም ማርከው ወስ
ደው በዙርያቸው ወዳሉ ጠላቶቻቸው አገር አገቡዋቸው
ማርከው በወሰዷቸው ጠላቶቻቸውም ሁሉ ፊት መከራከ
ርን አልቻሉም ። መሳ፣ ፪ ፩ ። መዝ፣ ፻፮ ፵ ።
የእግዚአብሔርም ሥልጣን እግዚአብሔር ምሎ እን
ደተናገረ በነሳቸው ላይ በመዓት አለች፣ ፈጽሞም መከ
ራን አጸናባቸው ። ዘሌ፣ ፳፮ ፩ ። ዘዳ፣ ፳፰ ፩ ።
እግዚአብሔርም መሳፍንትን አስነሥቶ ከማረኩዋ
ቸው ሰዎች እጅ አዳናቸው ። መሳ፣ ፫ ፱ - ፲፭ ።
ለስነዋልና ልዩ የሆኑ ጣኦታትንም አምልከው ሰግደ
ዉላቸዋልና ሹማምንቶቻቸውንም አልሰሙዋቸውም እግ
ዚአብሔርንም አሳዘኑት የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይ
ሰሙ አባቶቻቸው ጸንተው የኖሩበትንም ሥርዓት ፈጥ
ነው ተዉዋት፣ እንደሱም አላደረጉ ። ዘፀ፣ ፴፬ ፲፭ ።
እግዚአብሔር መሳፍንትን በስነሣላቸው ጊዜ እግዚአ
ብሔር ከዚያ መስፍን ጋራ በረድኤት ኖረ፣ በሚዋጉዋቸ
ውም ሰዎች ፊት እግዚአብሔር ከመከራቸው ይቅር ብሎ
አቸዋልና፣ በዚያ መስፍን ዘመን ሁሉ ከጠላቶቻቸው እጅ
አዳናቸው ። ዘፍ፣ ፮ ፮ ። ዘዳ፣ ፴፪ ፴፮ ።
ከዚህ በኋላ ያ ሹም በሞተ ጊዜ ዳግመኛ ወደ ኃጢ
አት ይመለሱ ነበር፣ ከአባቶቻቸው ይልቅ ይበድሉ ነበር፣
ሂደውም ልዩ የሆኑ ጣኦታትን ተከትለው ያመልኳቸው
ነበር፣ ይሰግዱላቸውም ነበር፣ ክፋታቸውን አይተዉም
ነበር፣ ከክፉ ሥራቸውም አይመለሱም ነበር ።
እግዚአብሔርም በእስራኤል ተቈጣ፣ እነዚህ ወገኖቼ
ለአባቶቻቸው ያዘዝኳቸውን ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋልና፣
ቃሌንም አልሰሙምና ። ዘዳ፣ ፲፯ ፪ ። መሳ፣ ፪ ፲፬ ።
እኔም እንግዲህ ወዲህ ከነሳቸው ሰውን አላጠፋም፣
ከፊታቸውም ኢያሱ ያስቀራቸው አሕዛብን አላጠፋም አለ።
የእግዚአብሔርን ሕግ ይጠብቁ እንደሆነ አባቶቻቸው
እንደ ጠበቁ በሷም ጸንተው አይኖሩም እንደሆነ እስራኤ

አበዊሆሙ ወእመ አልቦ ።
፳፫ ወኀደጎሙ እግዚአብሔር ለእሉ አሕዛብ ወኢያሰሰ
ሎሙ ፍጡነ ወኢያግብኦሙ ውስተ እዴሁ ለኢያሱ ።

ምዕራፍ ፫ ።

፩ ወኀደጎሙ እግዚአብሔር ለእሉ አሕዛብ ከመ ያመክ
ሮሙ በሙ ለእስራኤል ወለሎሙ እለ ኢየአምሩ ኵሎ
ፀብአሙ ለከነአን ።
፪ ዳዕሙ በእንተ ትውልዶሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ
ይምሀርዎሙ ቀትለ ።
፫ ወበሕቱ እለ እምቅድሜሆሙኒ ኢያእመርዎሙ ፣ ለእሉ
ኃምስቱ አሕዛበ ኢሎፍሊ ወበኵሉ ከነአን ወሲዶና ወኤ
ዊዎን እለ ይነብሩ ውስተ ሊባኖስ እምደብረ ባላሄርሞን
እስከ ሙበአ ኤማት ።

፬ ወተርፉ ከመ ያመክሮሙ በሙ ለእስራኤል ከመ ያእ
ምር እመ ይሰምዑ ትእዛዘ እግዚአብሔር ዘአዘዞሙ ለአበ
ዊሆሙ በእደ ሙሴ ።
፭ ወነበሩ ደቂቀ እስራኤል ማእከለ ከናኔዎን ወኬጤዎን
ወአሞሬዎን ወፌርዜዎን ወኤዌዎን ወኢያቡሴዎን ።

፮ ወነሥኡ አዋልዲሆሙ ወአውሰቡ ወአዋልዲሆሙኒ
ወሀቡ ለደቂቆሙ ወአምለኩ አማልክቲሆሙ ።

፯ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል እኩየ ቅድመ እግዚአብሔር
ወረስዕዎ ለእግዚአብሔር አምላኮሙ ወአምለክዎሙ ለበ
ዓሊም ወለአስጣሮት ።
፰ ወተምዐ እግዚአብሔር መዓተ ላዕለ እስራኤል ወአግ
ብኦሙ ውስተ እዴ ኵስአርስቴም ንጉሠ ሶርያ ዘመስጴጦ
ምያ አፍላግ ወተቀንዩ ደቂቀ እስራኤል ለኵስአርስቴም
ሰመንተ ዓመተ ።
፱ ወገዐሩ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር ወአቀመ
ሎሙ እግዚአብሔር መድኃኒተ ለእስራኤል ወአድኀኖሙ
ጎቶንያል ወልደ ቄኔዝ እኁሁ ለካሌብ ዘይንእስ እምኔሁ
ወተአዘዙ ሎቱ ።
፲ ወኮነ ላዕሌሁ መንፈሰ እግዚአብሔር ወኮነኖሙ ለደ
ቂቀ እስራኤል ወወፅአ ፀብአ ወአግብአ እግዚአብሔር ው
ስተ እዴሁ ለኵስአርስቴም ንጉሠ ሶርያ ወአዕረፈት ምድር
ኃምስተ ዓመተ ።
፲፩ ወሞተ ጎቶንያል ወልደ ቄኔዝ ፣ ወደገሙ ደቂቀ እስራ
ኤል ገቢረ እከይ ቅድመ እግዚአብሔር ።
፲፪ ወአጽንዖ እግዚአብሔሩ ለኤግሎም ንጉሠ ሞአብ ላዕ
ለ እስራኤል እስመ ገብሩ እኪተ ቅድመ እግዚአብሔር ።
፲፫ ወአስተጋብአ ላዕሌሆሙ ኵሎ ደቂቀ አሞን ወአማሌቅ
ወሖረ ወቀተሎሙ ለእስራኤል ወተዋረሳ ለሀገረ ፊንቆን ።
፲፬ ወተቀንዩ ደቂቀ እስራኤል ለኤግሎም ንጉሠ ሞአብ
ዐሠርተ ወሰመንተ ዓመተ ።
፲፭ ወገዐሩ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር ወአቀመ
ሎሙ እግዚአብሔር መድኀኒተ ለእስራኤል ናአድሃ ወልደ

ልን ይፈትንበቸው ዘንድ ተዋቸው ። ዘፀ፣ ፲፭ ፳፭ ።
እግዚአብሔር እነዚያን አሕዛብ ተዋቸው ፈጥኖም
አላጠፋቸውም በኢያሱም እጅ አልጣላቸውም ።

ምዕራፍ ፫ ።

እግዚአብሔር እነዚህን አሕዛብ የተዋቸው እስራኤ
ልን ሊፈትንባቸው ነው ፣ ሁሉም የከነዓን ሰዎች ጦርነት
ሁሉ የማያውቁ ናቸው ።
ሰልፍንም ያስተምሩዋቸው ዘንድ ስለ እስራኤል ልጆ
ች ነው እንጂ ።
ነገር ግን ከነሳቸውም አስቀድመው የነበሩ አባቶቻ
ቸው እነዚህን አምስቱን የኢሎፍሊ ወገኖች በማጥፋት
አላወቋቸውም ፣ እነዚህም በከነዓን ሁሉ በሲዶናም በኤዌ
ዎንም ከበላሄርሞን ተራራ ጀምሮ እስከ ኤማት መግቢያ
ድረስ በደጋ የሚኖሩ ናቸው ።
እግዚአብሔር በሙሴ ቃል አባቶቻቸውን ያዘዛቸውን
ትእዛዝ ይሰሙ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ እስራኤልን ሊፈት
ንባቸው ቀሩ ። መሳ፣ ፪ ፳፩ - ፳፪፣ ኢያ፣ ፲፫ ፪ - ፮ ።
የእስራኤልም ልጆች በኬጤዎንና በከናኔዎን ፣ በፌር
ዜዎንና በአሞሬዎን ፣ በኢያቡሴዎንና በኤዌዎን መካከል
ኖሩ ። ዘፀ፣ ፲፫ ፭ ። መዝ፣ ፻፮ ፴፭ ።
ሴቶች ልጆቻቸውን ወስደው አገቡ ፣ ሴቶች ልጆቻ
ቸውንም ለወንዶች ልጆቻቸው ሰጡ ፣ ጣኦቶቻቸውንም
አመለኩ ። ዘፀ፣ ፴፬ ፲፮ ።
የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራን
ሠሩ ፣ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርንም ዘነጉት ፣ አስጣሮት
ንና በዓሊምንም አመለኩዋቸው ። ዘፀ፣ ፴፬ ፲፫ ።
እግዚአብሔርም በእስራኤል ተቈጥቶ በመስጴጦምያ
ወንዞች መካከል ባለች በሶርያው ንጉሥ በኵስአርስቴም
እጅ ጣላቸው ፣ የእስራኤልም ልጆች ለኵስአርስቴም
ስምንት ዓመት ተገዙ ። መሳ፣ ፪ ፲፬ ።
የእስራኤልም ልጆች ወደ እግዚአብሔር ጮኹ ፣ እግ
ዚአብሔርም ለእስራኤል የሚያድናቸው መስፍንን አስነ
ሣላቸው ፣ ከሱ የሚያንስ የካሌብ ታናሽ ወንድሙ የቄኔዝ
ልጅ ጎቶንያልም አዳናቸው ፣ ለሱም ታዘዙለት ።
የእግዚአብሔርም ረድኤት አደረበት ፣ የእስራኤልንም
ልጆች ገዛቸው ፣ ወደ ሰልፍ ወጣ ፣ እግዚአብሔርም የሶር
ያው ንጉሥ ኵስአርስቴምን በእጁ ጣለው ፣ ምድርም አም
ስት ዓመት አረፈች ።
የቄኔዝም ልጅ ጎቶንያልም ሞተ ፣ የእስራኤልም ልጆች
ዳግመኛ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራን ሠሩ ።
በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ ሥራ ስለ ሠሩ እግዚአብ
ሔር የሞዓብ ንጉሥ ኤግሎምን በእስራኤል ላይ አጸናው ።
የአማሌቅንና የአሞንን ልጆች ሰብስቦ ሄዶ እስራኤ
ልን ወጋቸው ፣ ፊንቆንንም ወረሳት ።
የእስራኤልም ልጆች ለሞዓብ ንጉሥ ለኤግሎም ዓሥ
ራ ስምንት ዓመት ተገዙ ። መሳ፣ ፳፰ ፵፰ ።
የእስራኤል ልጆች ወደ እግዚአብሔር ጮኹ ፣ እግዚ
አብሔርም ለእስራኤል የሚያድናቸው ሁለት እጆቹ ቀኝ

ጌራ ወልዩ ኢያሚን ብእሴ ዘክልኤሆን እደዊሁ የማን ወፈነዉ ደቂቀ እስራኤል አምኃ ምስሌሁ ለኤግሎም ንጉሠ ሞአብ ።

፲፮ ወገብረ ሎቱ ናኦድ መጥባሕተ እንተ ክልኤ አፉሃ ወእንተ ስዝር ኑኃ ወቀነታ ታሕተ ቀናቱ ውስተ ሐቌሁ መንገለ የማኑ ።

፲፯ ወአብአ ሎቱ አምኃሁ ለኤግሎም ንጉሠ ሞአብ ወኤግሎምሰ ቈጢጥ ብእሲሁ ውእቱ ጥቀ ።

፲፰ ወእምዝ ሶበ ፈጸመ ናኦድ አብአ ሎቱ አምኃሁ ፈነዎሙ ለእለ ያሩ አምኃሁ ።

፲፱ ወገብአ ኤግሎም እምቤተ አማልክት ምስለ ገልገል ወይቤሎ ናኦድ ብየ ኅቡእ ነገር ኀቤከ ንጉሥ እንተ ባሕቲትከ ፤ ወአዘዘ ኤግሎም ይፃእ ኵሉ እምኀቤሁ ወወፅኡ ኵሎሙ እለ ይቀውሙ ኀቤሁ ።

፳ ወቦአ ናኦድ ኀቤሁ ወይነብር ውእቱ ባሕቲቱ ውስተ ጽርሑ ወሐጋይ ውእቱ ወይቤሎ ናኦድ ብየ ነገር ዘእነግረከ ንጉሥ ፤ ወተንሥአ ኤግሎም እመንበሩ ወቀርበ ።

፳፩ ወሶበ ተንሥአ አልዐለ ናኦድ እዴሁ እንተ ፀጋም ወመልሐ መጥባሕቶ እምገቦሁ ዘየማን ወረገዞ ውስተ ከርሡ ለኤግሎም ።

፳፪ ወአብአ እስከ ለዐታ ወበርበሮ እስከ ዘባኑ ወመልሐ መጥባሕቶ እምከርሡ ።

፳፫ ወወፅአ ናኦድ ጸናፌ ወዐጸወ ኆኅተ ጽርሕ ላዕሌሁ ወቀተረ ።

፳፬ ወወፂአ ውእቱ ቦኡ ደቂ ወርእዩ ወረከቡ ኆኅተ ጽርሕ ዕፁወ ወይቤሉ ዮጊ ባሕቲቱ ይነብር ጽምወ ውስተ ምግኃሠ ጽርሑ ቅስፈ ።

፳፭ ወጸንሑ እስመ ኀፍሩ ወአልቦ ዘአርኀወ ኆኅተ ጽርሕ ወነሥኡ መርኆ ወአርኀዉ ወረከብዎ ለእግዚአሙ ውዱቀ ውስተ ምድር ምዉተ ።

፳፮ ወናኦድሰ አምሠጠ እስከ እሙንቱ ይትሀወኩ ወአልቦ ዘአእመሮ ወውእቱሰ ኀለፈ እምአማልክቲሆሙ ወአምሠጠ ውስተ ሴይሮታ ።

፳፯ ወእምዝ ሶበ በጽሐ ውስተ ምድረ እስራኤል ነፍሐ ቀርነ በውስተ ደብረ ኤፍሬም ፤ ወወረዱ ምስሌሁ እምደብር ደቂቀ እስራኤል ወውእቱ ቀድሚሆሙ ።

፳፰ ወይቤሎሙ ረዱ ትልዉኒ እስመ አግብኦሙ እግዚአብሔር ለፀርነ ሞአብ ውስተ እዴነ ወወረዱ ወተለውዎ ወበጽሑ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ወአኀዙ ምዕዳወ ዮርዳኖስ ዘሞአብ ወኢያብሑ ሰብአ ይዕዱ ።

፳፱ ወቀተልዎሙ ለሞአብ በእማንቱ መዋዕል ወየአክሉ እልፈ ብእሲ ኵሎሙ መስተቃትላነ ወኵሎ እደወ ኀይሎሙ ወአልቦ ዘአምሠጠ እምኔሆሙ ወኢ አሐዱ ብእሲ ።

፴ ወገብኡ ሞአብ በእማንቱ መዋዕል ውስተ እደ ሆሙ ለእስራኤል ወአዕረፈት ምድር ሰማንየ ዓመተ ወኰነኖሙ ናኦድ እስከ ሞተ ።

የሆኑ የኢያሚን ልጅ የጌራን ልጅ ናኦድን አስነሣላቸው የእስራኤልም ልጆች ለሞዓብ ንጉሥ ለኤግሎም ከሱ ጋራ እጅ መንሻን ላኩ ። መሳ፣ ፫ ፱ ፤ ፳ ፲፯ ።

ናኦድም አፍዋ ሁለት ፤ ቁመቷ ስንዝር የሆነ ሰይፍን አሠርቶ በቀኝ በኩል ባለ ወገቡ ከዝናሩ በታች ታጠቃት።

ለሞዓብ ንጉሥ ለኤግሎም እጅ መንሻውን አገባለት ኤግሎም ግን ፈጽሞ ቀጭን ሰው ነበር ።

ከዚህ በኋላ ናኦድ ለሱ እጅ መንሻን አግብቶ በፈጸመ ጊዜ እጅ መንሻውን የተሸከሙትን ሰዎች አሰናበታቸው ።

ኤግሎምም ከጣኦታቱ ቤት ከገልገል ጋራ ተመለሰ ፤ ናኦድም ለብቻህ ባንተ ዘንድ የተሠወረ ምሥጢር አለኝ አለ ፤ ኤግሎምም ከሱ ዘንድ ሰው ይመለስ ብሎ አዘዘ ፤ በሱ ዘንድ የቆሙ ሰዎችም ሁሉ ወጡ ።

ናኦድም ወደሱ ገባ ፤ እሱም በእልፍኙ ብቻውን ተቀምጦ ነበር ወራቱም በጋ ነበር ፤ ናኦድ ንጉሥ የምነግርህ ነገር አለኝ አለው ፤ ኤግሎምም ከዙፋኑ ተነሥቶ ቀረበ ።

በተነሣም ጊዜ ናኦድ ግራ እጁን ከፍ ከፍ አድርጎ ፤ ከቀኝ ጐኑ ሰይፉን መዝዞ ኤግሎምን ሆዱን ወጋው ።

እስከ ውላጋዋም ድረስ አገባበት ፤ እስከ ጀርባውም ድረስ አማሰለው (በረበረው) ከሆዱም ሰይፉን ስቦ አወጣ።

ናኦድ ደጃፉን የኋሊት ዘግቶ ወደ አዳራሹ በር ወጣ።

እሱም በወጣ ጊዜ አሽከሮቹ ገብተው የእልፍኙ ደጃፍ ተዘግቶ አገኙት ፤ ወደ አዳሪ ባደረገው እልፍኝ ዓይነ ምድር ተቀምጦ ይሆናል አሉ ። ፩ ሳሙ፣ ፳፬ ፫ ። ~

አፍረዋልና ጠበቁ የእልፍኙን ደጃፍ የከፈተ የለም ፤ መክፈቻውንም አምጥተው ደጃፉን በከፈቱ ጊዜ ጌታቸውን በምድር ላይ ወድቆ ሙቶ አገኙት ።

ናኦድ ግን እነሱቸው እስኪታወኩ ድረስ ፈጥኖ አመለጠ ፤ ያወቀውም የለም ፤ እሱ ግን ከጣኦቶቻቸው አልፎ ወደ ሴይሮታ ሄዶ አመለጠ ። ዘፍ፣ ፲፱ ፲፯ ።

ከዚህ በኋላ ወደ እስራኤል አገር በደረሰ ጊዜ በኤፍሬም ነገድ ዕጣ ነጋሪት መታ ፤ የእስራኤልም ልጆች ከሱ ጋር ከተራራ ወረዱ ፤ እሱም በፊት በፊታቸው ይሄድ ነበር።

እግዚአብሔር የሞዓብ ሰዎች ጠላቶቻችንን በእጃችን ጥሎልናልና ተከትላችሁኝ ውረዱ አላቸው ፤ ተከትለዉትም ወርደው ከዮርዳኖስ ማዶ ደረሱ ፤ የሞዓብ ክፍል የምትሆን የዮርዳኖስ መሻገሪያን ያዙ (ያዙ) ፤ ይሻገር ዘንድ ሰውን አላሰናበቱም ። መሳ፣ ፲፱ ፯ ፤ ፯ ፳፬ ።

በነዚያም ወራቶች የሞዓብን ሰዎች አጠፉዋቸው ፤ እነዚያም እልፍ ሰዎችን ይሆናሉ ፤ ሁሉም አርበኞች ናቸው ፤ የሠራዊቶቻቸውንም አለቆች ሁሉ አጠፉ ፤ ከነሳቸውም አንድ ሰው ስንኳ አላመለጠም ።

በዚያም ወራቶች የሞዓብ ሰዎች በእስራኤል እጅ ወደቁ ፤ ምድርም ሰማንያ ዓመት ዓረፈች ፤ ናኦድም እስኪሞት ድረስ ገዛቸው ። መሳ፣ ፫ ፲፩ ።

፴፩ ወእምድኅረዝ ቆመ ሴሜጌር ወልደ ሐናት ወቀተለ እምኢሎፍሊ ስድስተ ምእተ ብእሴ በማሕረስ ላሕም ወውእቱኒ አድኀኖሙ ለእስራኤል ።

ከዚህ በኋላ የሐናት ልጅ ሴሜጌር ተነሥቶ ከኢሎፍላውያን ስድስት መቶ ሰዎችን ገደለ፤ እሱም እስራኤልን አዳናቸው ። ዘሌ፡ ፳፯ ፲ ። መሳ፡ ፭ ፮ ።

## ምዕራፍ ፬ ።

፩ ወደገሙ ደቂቀ እስራኤል ገቢረ እኩይ ቅድመ እግዚአብሔር፤ ወናአድስ ሞተ ።

የእስራኤል ልጆች ዳግመኛ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራን ሠሩ፤ ናአድ ግን ሞተ ። መሳ፡ ፪ ፲፱ ።

፪ ወአግብኦሙ እግዚአብሔር ውስተ እደ ኢያሚን ንጉሠ ከናኔዎን ዘነግሠ በሰርያ ወመልአከ ሠራዊቱ ሲሳራ ወውእቱሰ ይነብር ውስተ አሴሮት ዘአሕዛብ ።

እግዚአብሔርም በሰርያ በነገሠ በከናኔዎን ንጉሥ በኢያሚን እጅ ጣላቸው፤ ቢትወደዱም ሲሳራ ነበር፤ እሱም የአሕዛብ ዕጣ በምትሆን በአሴሮት ይኖር ነበር ።

፫ ወገዐሩ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር እስመ በተስዐቱ ምእት ሠረገላት ዘሐፂን ወውእቱ አሕመሞሙ ለእስራኤል እንዘ ይሣቅዮሙ ዕሥራ ዓመተ ።

ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገላዎች ነበረውና የእስራኤል ልጆች ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤ እስራኤልንም እሱ ሃያ ዓመት ያህል መከራ አጽንቶ አሳዝኖአቸው ነበር ።

፬ ወዲቦራ ብእሲት ነቢይት ብእሲቱ ለፌዶት ይእቲ ትኬንኖሙ ለእስራኤል በእማንቱ መዋዕል ።

ነቢይት የምትሆን የፌዶት ሚስት ዲቦራ በነዚያ ወራቶች እስራኤልን ትገዛቸው ነበር ።

፭ ወዲቦራሰ ትነብር ኀበ ፊንቂ ማእከለ ኢያማ ወማእከለ ቤቴል ውስተ ደብረ ኤፍሬም ወዐርጉ ኀቤሃ ደቂቀ እስራኤል ከመ ይትኳነኑ ።

ዲቦራ ግን በኤፍሬም ዕጣ ባሉ በቤቴልና በኢያማ መካከል በፊንቂ ትኖር ነበር፤ የእስራኤልም ልጆች ይፈራረዱ ዘንድ ወደሷ ወጡ ። ኢያ፡ ፲፫ ፳፭፤ ፳፩ ፴፫ ።

፮ ወፈነወት ዲቦራ ወፀውዓቶ ለባርቅ ወልደ አቤኔሔም እምቃዴስ ዘንፍታሌም ወትቤሎ አኮኑ ኪያከ አዘዘ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ከመ ትሑር ውስተ ደብረ ታቦር ወንሣእ ምስሌከ አልፈ እደወ እምደቂቀ ንፍታሌም ወእምደቂቀ ዛብሎን ።

ዲቦራ ልካ የአቤኔሔምን ልጅ ባርቅን የንፍታሌም ዕጣ ከምትሆን ከቃዴስ አስጠራችው፤ ወደ ደብረ ታቦር ትሄድ ዘንድ የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር አንተን ያዘዘ አይደለምን! ከዛብሎን ልጆችና ከንፍታሌም ልጆች አልፍ ሰዎችን ካንተ ጋራ ይዘህ ሂድ ። ኢያ፡ ፲፱ ፴፯ ።

፯ ወእወስደከ ኀበ ፈለገ ቂሶን ላዕለ ሲሳራ መልአከ ሠራዊቱ ለኢያሚን ወሠረገላቲሁ ወብዝኁ ወአገብኦ ውስተ እዴከ ።

በኢያሚን ሠራዊት አዛዥ በሲሳራ ላይ በሠራዊቱና በሠረገላዎቹም ላይ ወደ ቂሶን ወንዝ እወስድኻለሁ በእጅህም እጥለዋለሁ አለችው ። መሳ፡ ፬ ፲፫ ። መዝ፡ ፹፫ ፱ ።

፰ ወይቤላ ባርቅ እመ ተሐውሪ ምስሌየ አሐውር ወእመሰ ኢተሐውሪ ምስሌየ ኢየሐውር እስመ ኢየአምር ዕለተ እንተ በቲ ይፈቅድ እግዚአብሔር ይፈኑ መልአኮ ምስሌየ ።

ባርቅም እግዚአብሔር መልአኩን ከኔ ጋር ይልክ ዘንድ የሚወድበትን ቀን አላውቅምና ከኔ ጋራ ብትሄጂ እሄዳለሁ፤ ከኔ ጋራ ካልሄድሽ ግን አልሄድም አላት ።

፱ ወትቤሎ ዲቦራ አሐውር ምስሌከ ወባሕቱ አአምር ከመ ኢይከውነከ ክብረ ዘቀዳሙ ቃልከ በፍኖት እንተ ሖርከ እስመ ውስተ እደ ብእሲት ያገብኦ እግዚአብሔር ለሲሳራ፤ ወተንሥአት ዲቦራ ወሖረት ምስለ ባርቅ እምቃዴስ ።

ዲቦራም ካንተ ጋር እሄዳለሁ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሲሳራን በሴት እጅ ይጥለዋልና፤ በሄድክበት ጐዳና የቀደመው ቃልህ ክብር እንዳይሆንህ አውቃለሁ አለችው ዲቦራም ተነሥታ ከባርቅ ጋር ወደ ቃዴስ ሄደች ።

፲ ወአዘዞሙ ባርቅ ለዛብሎን ወለንፍታሌም በቃዴስ ከመ ይትልውዎ ወዐርጉ ምስሌሁ አልፍ ብእሲ፤ ወዲቦራኒ ዐርገት ምስሌሁ ።

ባርቅም ይከተሉት ዘንድ ንፍታሌምንና ዛብሎንን ወደ ቃዴስ ጠራቸው አልፍም ሰዎች ከርሱ ጋራ ወጡ፤ ዲቦራም ከሱ ጋራ ወጣች ። ዘፀ፡ ፲፩ ፰ ። መሳ፡ ፭ ፲፰ ።

፲፩ ወእለ ቅሩቦ ለቁኔዝ ተፈልጡ እምደቂቀ ኢዮባብ ሐሙሁ ለሙሴ ወኃደረ ትዕይንቱ ኀበ ዕፀ ለበዩት ኀበ ቅሩበ ቃዴስ ።

የቁኔዝ አቅራቢያዎች የሚሆኑ ሰዎችም ከሙሴ አማት ከኢዮባብ ልጆች ተለዩ፤ ሠራዊቱም በቃዴስ አቅራቢያ (በወይራ) በግራር ዛፍ ሥር አደሩ ። መሳ፡ ፩ ፲፮ ።

፲፪ ወዜነውዎ ለሲሳራ ከመ ዐርገ ባርቅ ወልደ አቤኔሔም ውስተ ደብረ ታቦር ።

ለሲሳራም የአቤኔሔም ልጅ ባርቅ ወደ ደብረ ታቦር እንደወጣ (ዘመተ) ነገሩት ። ኢያ፡ ፲፱ ፲፪ ።

፲፫ ወአምጽአ ሲሳራ ኵሎ ሠረገላቲሁ እስመ ተስዓቱ ምእት ሠረገላቲሁ ዘሐፂን ቦቱ ወኵሎ ሕዝቢሁ እምአሴሮት ዘሕዛብ ውስተ ፈለገ ቂሶን ።

ሲሳራ ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገላዎች ነበሩትና ሠረገላዎቹን ሁሉ የአሕዛብ ዕጣ ከምትሆን ከአሴሮት ወደ ቂሶን ወንዝ አመጣ ። መሳ፡ ፯ ፴፬ ። ፪ ሳሙ፡ ፳ ፭ ።

፲፬ ወትቤሎ ዲቦራ ለባርቅ ተንሥእ እስመ ዛቲ ዕለት እንተ በቲ ያገብኦ እግዚአብሔር ለሲሳራ ውስተ እዴከ ወናሁ እግዚአብሔር የሐውር ቅድሜከ፤ ወወረደ ባርቅ እምደብረ ታቦር ወአልፍ ብእሲ ይተልውዎ ።

ዲቦራም ባርቅን እግዚአብሔር ሲሳራን በእጅህ የሚጥልበት ቀን ይህች ናትና ተነሥ እነሆ እግዚአብሔርም በፊትህ ይሄዳል አለችው፤ ባርቅም አልፍ ሰዎች ተከትለዉት ከደብረ ታቦር ወረደ ። ዘዳ፡ ፱ ፫ ። መሳ፡ ፫ ፳፰ ።

ወአደንገፆ እግዚአብሔር ለሲሳራ ወለኵሉ ሠረገላቲሁ ፲፭
ወለኵሉ ትዕይንቱ ወአውደቆሙ ቅድመ ባርቅ በአፈ ሐ
ፂን ወወረደ ሲሳራ እምላዕለ ሠረገላሁ ወጐየ በእግሩ ።
ወዴገኖ ባርቅ ወተለወ ሠረገላቲሁ ወዴገነ ትዕይንቶ ፲፮
እስከ አኅለቀ አሕዛቢሁ ወሞተ ኵሉ ትዕይንተ ሲሳራ በአ
ፈ ሐፂን ወኢተርፈ ወኢ አሐዱ ።
ወሲሳራሰ ጐየ በእግሩ ውስተ ትዕይንተ ኢያኤል ብእ ፲፯
ሲተ ክቤር ከልአ፡ ለቄኔው እስመ ሰላም ውእቱ ማእከሎሙ
ለኢያቢን ንጉሠ ሶርያ ወማእከለ ቤተ ክቤር ቄንያዊ ።

ወወፅአት ኢያኤል ወተቀበለቶ ለሲሳራ ወትቤሎ ገኀ ፲፰
ሥ እግዚእየ ገኀሥ ኀቤየ ወኢትፍራህ ወገኀሠ ኀቤሃ
ውስተ ደብተራሃ ወከደነቶ ሠቀ ።
ወይቤላ ሲሳራ አስትይኒ ንስቲተ ማየ እስመ ጸማእኩ፡ ፲፱
ወፈትሐት ዝቅዐ ሐሊብ ወአስተየቶ ወከደነቶ ገጾ ።

ወይቤላ ቁሚ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ወእመቦ ዘመጽአ ፳
ኀቤኪ ወይቤለኪ ሀለወኑ ዝየ ብእሲ በሊ አልቦ ወከደነቶ
ሠቀ ።
ወነሥአት ኢያኤል ብእሲተ ክቤር መትከለ ደብተራ ፳፩
ወአኀዘት በክልኤቲ እደዊሃ ወበአት ወጸቀወቶ ወተከለት ው
እተ መትከለ ውስተ መልታሕቱ ወኀደአቶ እስከ ፀመረቶ
ምስለ ምድር ወተራገጸ ውእቱ ማእከለ እገሪሃ ወተሠጥሐ
ወሞተ ።
ወበጽሐ ባርቅ እንዘ ይዴግኖ ለሲሳራ ወወፅአት ኢያ ፳፪
ኤል ወተቀበለቶ ለባርቅ ወትቤሎ ነዓ አርኢከ ብእሴ ዘት
ኀሥሥ፣ ወቦአ ኀቤሃ ወረከቦ ለሲሳራ ወዱቅ በድኖ ወመ
ትከል ውስተ መልታሕቱ ።
ወአኅሠሮ እግዚአብሔር ለኢያሚን ንጉሠ ከነአን በይ ፳፫
እቲ ዕለት በቅድሜሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ።
ወሖረት እዴሆሙ ለእግዚአብሔር ምስለ ደቂቀ እስራ ፳፬
ኤል ወጸንዓት ላዕለ ኢያሚን ንጉሠ ከነዓን እስከ አጥፍእ ።

ምዕራፍ ፭ ።

ወኀለየት ዲቦራ በይእቲ ዕለት ቅድመ ባርቅ ወትቤ ፩
እንዘ ትኄሊ ሰበ አኀዙ መሳፍንተ እስራኤል በሕሊና ሕ
ዝብ፡ ይባርክዎ ለእግዚአብሔር ።
ስምዑ ነገሥት ወአጽምኡ መኳንንት ጽኑዓን ። ፪

ወአንሰ እኀዝኩ ኣኀሊ ለእግዚአብሔር አምላከ እስ ፫
ራኤል ።
እግዚኦ በፀአትከ እምነ ሴይር ሰበ ተንሣእከ እምሐ ፬
ቅለ ኤዶም፡ ምድር አድለቅለቀት ወሰማይኒ ደንገፀት ወደ
መናት አንጠብጠቡ ማየ ።
ወአድባር ተከውሁ እምቅድመ እግዚአብሔር ዝንቱኒ ፭
ሲና እምቅድመ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ።

በመዋዕለ ሴሜጌር ወልደ ቄኔት ወበመዋዕለ ኢያኤል ፮

እግዚአብሔር ሲሳራን አስደነገጠው ሠረገላውንም ሁሉ
ሠራዊቱንም ሁሉ በባርቅ ፊት በጦር በአፈ ሐፂን ጣላ
ቸው፣ ሲሳራም ከሠረገላ ወርዶ በእግሩ ሸሸ ።
ባርቅም አሳደደው፣ ሠረገላውንም ተከተለ፣ ሠራዊ
ቱን እስኪያጠፋ ድረስ ተከተለ፣ የሲሳራ ሠራዊት ሁሉ
በጦር ጠፉ፣ አንድ ሰው ስንኳ አልቀረም ።
ሲሳራ ግን በቄንያው ሰው በክቤር ወገን መካከልና
በሶርያው ንጉሥ በኢያቢን መካከል ፍቅር ነበርና ወደ ቄ
ኔም ወንድም ወደ ክቤር ሚስት ወደ ኢያኤል ሰፈር በእ
ግሩ ሸሸ ።
ኢያኤልም ወጥታ ሲሳራን ተቀበለችው ጌታዬ ! ወደ
ኔ ግባ አይዞህ አትፍራ አለችው፣ እሱም ከእርሷ ዘንድ ወደ
ድንኳና ገባ፣ ምንጣፍንም አለበሰችው ።
ሲሳራም ጠምቶኛልና ጥቂት ውኃ አጠጪኝ አላት፣
እሷም የወተቱን ጮጮ ከፍታ አጠጣችው ፊቱንም ሸፈ
ነችው ። መሳ፡ ፭ ፳፭ ።
በድንኳኑ ደጃፍ ቁሚ፣ ወዳንቺ መጥቶ በዚህ ሰው
አለን፣ ብሎ የጠየቀሽ ሰው ቢኖር የለም በይው አላት
ምንጣፍንም አለበሰችው ።
የክቤር ሚስት ኢያኤልም በአንድ እጅዋ የድንኳን
ካስማ፣ በሁለተኛይቱ እጅዋ ደንጊያ ይዛ ገብታ ወግታ
ያነን ካስማ በጕንጬ ተከለችው፣ ከምድር ጋር አንድ
እስከሚያደርገው ድረስ መታችው፣ እሱም በእግሯ መካከል
ተንፈራፍሮና ተዘርሮ ሞተ ።
ባርቅም ሲሳራን እየተከተለ ደረሰ፣ ኢያኤልም ወጥታ
ባርቅን ተቀበለችው የምትፈልገውን ሰው ና ላሳይህ አለ
ችው፣ እሱም ወደሷ ገብቶ ሲሳራን ሬሳው ወድቆ ከስ
ማው በጕንጬ ተተክሎ አገኘው ።
እግዚአብሔር በዚያች ቀን በእስራኤል ልጆች ፊት
የከነዓን ንጉሥ ኢያሚንን አኰሰሰው ።
የእግዚአብሔርም ሥልጣን ከእስራኤል ልጆች ጋር
ጸንታ ኖረች፣ እስኪያጠፋውም ድረስ በከነዓን ንጉሥ
በኢያሚን ላይ እየጸናች ሄደች ።

ምዕራፍ ፭ ።

ዲቦራም ስታመሰግን የእስራኤል መሳፍንት የሕዝቡን
ልቡና በያዙ ጊዜ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ብላ በዚ
ያች ቀን በባርቅ ፊት አመሰገነች ። ዘፀ፡ ፲፭ ፩ ።
ነገሥታቱ ስሙ፣ ጽኑዓን የምትሆኑ መኳንንትም አድ
ምጡ ። ዘዳ፡ ፴፪ ፵፪ ። ፪ ሳሙ፣ ፳፪ ፵፪ ።
እኔም ለእስራኤል ፈጣሪ ለእግዚአብሔር ምስጋናን
ላቀርብ ጀመርሁ (አቀርብለሁ) ። መዝ፡ ፪ ፪ ። ምሳ፡ ፴፭ ፬።
አቤቱ ! ከሴይር (ከግብጽ) በወጣህ ጊዜ ከኤዶም ምድ
ረ በዳም በተነሣህ ጊዜ ግብጽ ተንቀጠቀጠች፣ ሰማይም ደነ
ገጠች፣ ደመናትም ዝናምን አዘነሙ ። ዘዳ፡ ፴፫ ፪ ።
ተራሮችም ከእግዚአብሔር መገለጽ የተነሣ ተንቀጠቀጡ
ይህም ደብረ ሲና በእስራኤል ፈጣሪ በእግዚአብሔር ፊት
ተንቀጠቀጠ ። ዘጸ፡ ፬ ፲፩ ። ኢሳ፡ ፷፬ ፩ - ፫ ።
በኢያኤል ዘመንና በቄኔት ልጅ በሴሜጌር ዘመን ነገ

ኀልቁ ነገሥት ወሖሩ ፍና መብእሰ ወፍኖተ ማፍቀፍተ ።

፯ ወኀልቁ መፈክራን እምእስራኤል እስከ ተንሥአት ዲ
ቦራ ወቆመት እመ ለእስራኤል ።

፰ ወሠምሩ በአማልክተ ከንቱ ከመ ኅብስተ ሰገም ሶበ
ይከድንዎ ውዕዩ አርማኅ፣ አርባዕቱ እልፍ አርማኅ ።

፱ ልብየ ውስተ ዘተአዘዘ ለእስራኤል፣ ኃያላኒሆሙ
ለእስራኤል ባርክዎ ለእግዚአብሔር ።
፲ እለ ትጼዕኑ ላዕለ አእዱግ ፀዐድዋን፣ ወትነብሩ ውስተ
ብርሃን፣ ንቡ ቃለክሙ ።
፲፩ ወሰንቀው ማእከለ ብዙኃን ፍሡሐን ወበህየ ይሁቡ
ጽድቀ ለእግዚአብሔር፣ ጽድቀ ወጽንዐ በውስተ እስራ
ኤል፣ ወይእተ አሚረ ወረደ ውስተ አህጉሪሁ ሕዝበ እግ
ዚአብሔር ።
፲፪ ተንሥኢ ዲቦራ ወአንሥኢ አእላፈ ምስለ ሕዝብ ተን
ሥኢ ተንሥኢ ምስለ ማኅሌት፣ ወበኃይል ተንሥእ ባር
ቅ፣ ወጼንዊዮ ዲቦራ ለባርቅ ወጼዉዉ ፄዋከ ባርቅ ወልደ
አቢኔሔም ከመ አመ ዓብየ ኃይሉ ።

፲፫ እግዚእ አድክሞሙ ሊተ ለእለ ይጸንዑኒ ሕዝበ ኤፍ
ሬም ።
፲፬ ወቀሠፎሙ በውስተ ቈላት እኁከ ብንያም በሕዝብከ
እምነ ማኪር፣ ወወረዱ ይፍትኑ ።
፲፭ ወእምዘብሎን እግዚአብሔር ይጸብእ ሊተ፣ ወእምኃ
ያላን እምህየ ወተረ በኃይለ ነገር ።
፲፮ ወእምውስተ ይሳኮር ምስለ ዲቦራ ፈነወ እጋሪሁ
ውስተ ቈላት ከመ ትንበር እንተ ማእከለ ከናፍር ወሰፍሐ
በእገሪሁ ነፍቆ ሮቤል ዓቢይ ጥይቀና ልቡ ።
፲፯ ወለምንትኑ ለከ ትነብር ምስለ መስፌተም ከመ ታጽ
ምእ ከመ ይትፋጸዩ እለ ይነሥኡ ከመ ይኅልፉ ውስተ
ዘሮቤል ።
፲፰ ዓቢይ አሠረ ልቡ ለጋድ ውስተ ማዕዶተ ዮርዳኖስ
ኀደረ፣ ወዳን ለምንት ይነብር ውስተ አሕማር ወአሴርሰ
ነበረ ውስተ ሐይቀ ባሕር ወውስተ ወሰኑ ነበረ ።
፲፱ ዘብሎን ሕዝብ ዘአየረ ነፍሶ ለሞት ወንፍታሌም ው
ስተ መልዕልተ ሐቅል ።
፳ ወመጽኡ ነገሥት ወተቃተሉ ወይእተ አሚረ ተቃ
ተሉ ነገሥተ ከነአን በቶናኅ በኀበ ማየ መጊዶ ወኢነሥአ
በትዕግልት ብሩረ ።
፳፩ ወበሰማይ ተፃብኡ ከዋክብት እምቀትሎሙ ወተቃ
ተሉ ምስለ ሲሳራ ።
፳፪ ወአውዕአሙ በፈለገ ቂሶን ወፈለገ ቄሔሚን ወተቃ
ተሉ በፈለገ ቂሶን ነፍስየ ጽንዒ ።
፳፫ ወይእተ አሚረ ተቀጥቀጠ ሰኰና አፍራሲሆሙ ለአ
ምዳሮት ወኀያላኒሁ ለማዘር ይረግምዎ ።
፳፬ ወይቤ መልአከ እግዚአብሔር በመርገም ርግምዎሙ

ሥቃቱ አለቁ፣ የተሰነከከሉና ግልብጥብጥ ያሉ ጐዳናዎ
ችንም ሄዱ ። መሳ፡ ፫ ፴፩፣ ፬ ፲፯ ።
ዲቦራ እስክትነሣ ድረስና ለእስራኤልም እናት ሁና
እስክትተካ ድረስ ከእስራኤል ሕልምን የሚተረጕሙ
ሰዎች ጠፉ ። መሳ፡ ፭ ፲፩ ።
ከንቱ የሆኑ ጣኦታትን ወደዱ፣ የገብስ እንጀራ በከዱ
ኑት ጊዜ ከሸልሸል ብሎ እንዲያር ለእስራኤል በታዘዘ
ረድኤት በሰሽፋፍ ዘገርን የያዙ አራት እልፍ (ጦሮች)
ኃያላን ጠፉ ። ዘዳ፡ ፴፯ ፲፯ ። መሳ፡ ፬ ፲፪ - ፲፯ ።
ልቤ ወደ እስራኤል አለቆች ነው፣ የእስራኤል መኳ
ንንትም እግዚአብሔርን አመስግኑት ።
በነጫጮች አህዮች የምትቀመጡም በተድላ ደስታ
የምትኖሩም ሰዎች በቃላችሁ ተናገሩ ። ዘኍ፡ ፳፪ ፳፩ ።
ደስ በላቸው ሰዎች መካከል መሰንቆን ምቱ፣ በዚያ
ለእግዚአብሔር እውነተኛ ምስጋናን ያቀርባሉ በእስራኤል
ዘንድ ጽናትንና እውነትን ያቀርባሉ፣ በዚያን ጊዜም የእ
ግዚአብሔር ወገን ወደ አገሩ ወረደ ። ዘፍ፡ ፳፬ ፲፩ ።
ዲቦራ ተነሺ፣ አእላፈ ዘብሉንን ከእእላፈ ይሳኮር ጋራ
አንሺ ከምስጋና ጋራ ተነሺ ተነሺ ባርቅም በኃይል ተነ
ሣ፣ ዲቦራ ባርቅን አጽኚው የእግዚአብሔር ኃይሉ በተገ
ለጠ ጊዜ እንደ ተገለጠልህ መጠን የአቢኔሔም ልጅ ባርቅ
ምርኮህን ማርክ ።
አቤቱ፤ በኔ የሚጸኑብኝን የኤፍሬምን ወገን አድክ
ምልኝ ።
ወንድምህ በእውራጃ አጠፋቸው፣ ብንያም በወገንህ
አፍራለሁ፣ ይዘርፉ ዘንድ ከማኪር ወረዱ ።
እግዚአብሔር በኃያላኑ አድሮ ወትሮ በሚነገር ነገር
ከዛብሎን ያጠፋልኛል ። ዘዳ፡ ፴፫ ፳፩ ።
ከነገደ ይሳኮርም ከዲቦራ ጋራ አርበኞችን ላከ፣ በወን
ድሞችህ መካከል ትቀመጥ ዘንድ ምን አለህ፤ እግሩን አን
ፈራጠ ቀረ፣ የሮቤል የልቡ ዕውቀት ደግ ነበር ።
በነገደ ሮቤል ዕጣ ይኼዱ ዘንድ ገድለው ሲደነፉ ትሰማ
ዘንድ ከመስፌተም (ከሳፊታዎች) ጋራ ለምን ትኖራለህ፤ ።

የጋድ የልቡ ዕውቀት ደግ ነበር፣ በዮርዳኖስ ማዶ ቀረ
ጋድ መርከቦች በወደብ እንዲኖሩ ከነገዶች ጋራ ለምን
ተቀመጠ፤ አሴር ግን በባሕር ዳርቻ ባለ በወሰኑ ኖረ ።
ዛብሎን ሰውነቱን ለሞት የሰጠ ወገን ነው፣ ንፍታሌ
ምም በበረኻው በአገሩ ይኖራል ። መሳ፡ ፬ ፲ ።
ነገሥታቱም ወጥተው ተዋጉ፣ የዚያን ጊዜ የከነዓን
ነገሥታት የመጊዶ ውኃ ባለበት በቶናህ ተዋጉ፣ ብርቅ
ብርን ቀምቶ አልወሰደም ። ኢያ፡ ፲፪ ፳፩ ።
ከሰልፋቸው የተነሣ እስራኤል በደብረ ታቦር ተዋጉ፣
ከሲሳራም ጋር ተዋጉ ።
ወደ ቂሔሚን ወንዝና ወደ ቂሶን ወንዝ አወጣቸው፣
በቂሶን ወንዝም ተዋጉ፣ ሰውነቴ ጽኚ ። መሳ፡ ፬ ፯ ።
የዚያን ጊዜ የአምዳሮች የፈረሶቻቸው ሰኰና አጐበ
ጐበ የአሕዛብ አርበኞች (ማዘርን) ጣኦቱን ይረግሙታል ።
ከእግዚአብሔር የተላከው መልአክም ጽኑዓን ከሆኑ አር

ለእለ ውስተ አብያቲሃ እስመ ኢመጽኡ ውስተ ረድኤተ እግዚአብሔር እመስተቃትላን ጽኑዓን ።

፳፭ ቡርክተ ትኩን እምነ አንስት ኢያኤል ብእሲተ ክቤር ቁንያዊ እምነ አንስት ቡርክት በውስተ ደብተራ ።

፳፮ ማየ ሰአላ ወሐሊበ ወሀበቶ ወበአይገን ዐቢይ አቅረበት ሎቱ ዕቋነ ።

፳፯ ወበእዴሃ እንተ ጸጋም ተመጠወት መትከለ ወበየማና ጒድአተ ወቀተለቶ ለሲሳራ ወቀጥቀጠቶ ርእሶ ወደመቀቶ መልታሒቶ ።

፳፰ ወተራገጸ በማእከለ እገሪሃ ወበጎበ ተራጋጸ በህየ ኀሥረ ።

፳፱ ወእንተ መስኮት ትሔውጽ እሙ ለሲሳራ እንተ ሰቅሰቅ ትሬኢ እመ በዘገብአ እምኀበ ሲሳራ ወበበይነ ምንት ተድኅረ ሠረገላሁ ለሲሳራ በጺሐ ወበበይነ ምንት ጐንደየ እግረ ሠረገላቲሁ ጠቢባት ።

፴ ወላእክቲሃ ላቲ አውሥእሃ ወእማንቱሰ አውሥእሃ በከመ ቃላ ።

፴፩ አኮ ረከቡሁ እንዘ ይከፍል ምኅርከ ወይትዓረክ አዕርክተ በላዕለ አርእስቲሆሙ ለኀያላን፤ ወበርበረ ውእቱ ሲሳራ በርበረ ኅብር፣ ወዘዘኢአሁ ጥምዐተ ኅበሪሁ ወእሥቅ ውስተ ክሳዱ ዘበርበረ ።

፴፪ ከማሁ ለይትኀጐሉ ኵሎሙ ፀርከ እግዚኦ ወእለሰ ያፈቅሩከ ከመ ሠርቀ ፀሐይ በኀይሉ ወአዕረፈት ምድር አርብዓ ዓመተ ።

## ምዕራፍ ፯ ።

፩ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል እኩየ ቅድመ እግዚአብሔር ወአግብኦሙ እግዚአብሔር ውስተ እደ ምድያም ሰብዐተ ዓመተ ።

፪ ወጸንዐት እዴሆሙ ለምድያም ላዕለ እስራኤል ወገብሩ ሎሙ ደቂቀ እስራኤል እምቅድመ ምድያም በዓታተ ወአጽዋናተ ውስተ አድባር ወውስተ አጽዳፍ ።

፫ ወእምዝ ሶበ ይዘርኡ ሰብአ እስራኤል የዐርጉ ምድያም ወአማሌቅ ወደቂቀ ጽባሕ የዓርጉ ላዕሌሆሙ ።

፬ ወይትዐየኑ ዲቤሆሙ ወያማስኑ ፍሬ ገራውሂሆሙ እስከ ይበጽሑ ውስተ ጋዛን ወኢያተርፉ ሎሙ ወኢምንተኒ በዘየሐይዉ ለእስራኤል ወመራዕይሆሙኒ ወላሕሞሙኒ ወአድጎሙኒ ።

፭ እስመ የዐርጉ ላዕሌሆሙ እሙንቱ ወእንስሳሆሙ ወተዓይኒሆሙ ያመጽኡ ወይበጽሕዎሙ ወከመ አንበጣ ብዝኆሙ ወአልቦሙ ኊልቈ ኢእሙንቱ ወኢአግማላቲሆሙ ወይመጽኡ ውስተ ምድረ እስራኤል ከመ ያማስንዎሙ ።

በኖች ጋራ እግዚአብሔር ወደ ሚያደርግላቸው ረድኤት አልመጡምና በቤቶቿ የሚኖሩ ሰዎች ርግማንን ርገሟቸው አለ ። ነህ፣ ፫ ፳ ። ፩ ሳሙ፣ ፩ ፲፭ ።

የቄንያዊው የክቤር ሚስት ኢያኤል ከሴቶች ተለይታ የከበረች ትሁን በድንኳን ውስጥ ከሚኖሩ ሴቶች ይልቅ የተባረከች ትሁን ። መሳ፣ ፬ ፲፯ ።

ውኃን ለመናት ወተትን ሰጠችው በታላቅ መንቀልም መገሜትን አቀረበችለት ። መሳ፣ ፬ ፲፱ ።

በግራ እጅዋ ካስማውን ተቀብላ፣ በቀኝ እጅዋ መትቻ ሲሳራን ገደለችው፣ ራሱንም ከሰከሰችው ጒንጩንም ጨፈለቀችው ። መሳ፣ ፬ ፳፩ ።

በእግሯ መካከል ተንፈራፈረ፣ በተንፈራፈረበትም በታ ተዋረደ ተገሰቈሰ (ሞተ) ።

የሲሳራ እናት በሰገነት ሁና ከሲሳራ ዘንድ የተመለሰ አለ እንደሆነ ብላ በመስኮት ትመለከት ነበር፣ የሲሳራም ሠረገላ ወደ፴ ከመድረስ ስለምን እንደ ዘገየ፣ ቀላሎች የሆኑ የሠረገላዎቹ እግሮችም እንደምንም እንደ ዘገዩ ታይ ዘንድ በመስኮት ትመለከት ነበር ። ዘፀ፣ ፴፪ ፳ ።

ገረዶቿም መለሱላት፣ እነሳቸው ግን እንደ ቃሏ መለሱላት ።

ብዙ ምርኮ አግኝተዋልና ምርኮውን ሲያከፍል የኃያላኑን ቸብቸብ እየቈረጡ እየሰጡት በወዳጅ ላይ ወዳጅ ሲገዛ ሲሳራም ምርኮውን ማርኮ አበላሉ አጠላለቁ ልዩ የሆኑ አራት ኅብር አምስት የወርቀ ዘቦ ግምጃ ሲሸልም የማረከውን ዝርግፍ በአንገቱ ሲያስር ይሆናል ብለው እንደ ቃሏ መለሱላት ።

አቤቱ! ጠላቶችህ ሁሉ እንደሱ ይጥፉ፤ የሚወዱህ ሰዎች ግን በኃይሉ እንደሚወጣ እንደ ፀሐይ ብርሃን ይሁኑ አለች፣ ምድርም አርባ ዘመን አረፈች ።

## ምዕራፍ ፯ ።

የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራን ሠሩ፣ እግዚአብሔርም ሰባት ዓመት በምድያም እጅ ጣላቸው ።

የምድያም ሥልጣንም በእስራኤል ላይ ጸናች፣ የእስራኤልም ልጆች ከምድያም ፊት በገደሎች ላይና በተራሮች ላይ አምባዎችንና ዋሻዎችን ሠሩ ።

ከዚህ በኋላ እስራኤል ዘር በዘሩ ጊዜ አማሌቅና የምድያም ሰዎች በምሥራቅ ያሉ ልጆችም ወደነሳቸው ዘመቱ ።

በነሳቸውም ላይ ይሰፍሩ ነበር፣ ወደ ጋዛን እስኪደርሱ ድረስ ደርሰው አዝመራቸውን ያጠፉባቸው ነበር፣ እስራኤል በሚድኑ ገንዘብ ምንም ምን አያስቀሩላቸውም ነበር፣ መንጋዎቻቸውንም ሆነ፤ ላሞቻቸውንና አህያዎቻቸውንም ሆነ ።

እነሱ በነሳቸው ላይ ይዘምቱ ነበር፣ ከብቶቻቸውንና ሠራዊቶቻቸውን ይዘው ይመጡባቸው ነበር፣ ብዛታቸውም እንደ አንበጣ ነበር፣ ለነሳቸውም ሆነ ለግመሎቻቸው ስፍር ቍጥር አልነበራቸውምና ያጠፉዋቸው ዘንድ ወደ እስራኤል አገር ይመጡ ነበር ። መሳ፣ ፮ ፲፪ ።

## ኦሪት ዘመሳፍንት፣ ምዕራፍ ፮ ።

፮ ወነድዩ ጥቀ እስራኤል እምቅድመ ምድያም ወገዐሩ
ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር ።

እስራኤልም ከምድያም ፊት የተነሣ ደኸዩ (ተቸገሩ)
የእስራኤልም ልጆች ወደ እግዚአብሔር ጮኹ ።

፯ ወሶበ ጸርሑ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር በእ
ንተ ምድያም ፈነወ ሎሙ እግዚአብሔር ብእሴ ነቢየ ለደ
ቂቀ እስራኤል ።

በምድያም ሰዎች ምክንያት ወደ እግዚአብሔር በጮ
ኹ ጊዜ እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች አንድ ነቢይ
ላከላቸው ።

፰ ወይቤሎሙ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ እስራ
ኤል አነ ውእቱ ዘአውፃእኩክሙ እምግብጽ እምነ ቤተ
ቅኔት ።

እንዲህም አላቸው የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር
ከግብጽ አገዛዝ ያወጣኋችሁ እኔ ነኝ ። መዝ፡ ፺ ፲፩ ።
መዝ፡ ፻፰ ፴፩ ። ሆሴ፡ ፩ ፲፩ ።

፱ ወአድኀንኩክሙ እምእደሆሙ ለግብጽ ወእምኵሎሙ
እለ ይሣቅዩክሙ ፣ ወአውፃእክዎሙ እምቅድመ ገጽክሙ
ወወሀብኩክሙ ምድሮሙ ።

ከግብጽም ሰዎች መከራንም ከሚያጸኑባችሁ ሁሉ ያዳ
ንኋችሁ የከነዓንንም ሰዎች ከፊታችሁ አስወጥቼ አገራቸ
ውን የሰጠኋችሁ እኔ ነኝ ።

፲ ወእቤለክሙ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክክሙ
ወኢትፍርሁ እምአማልክተ አሞሬዎን እሉ እለ ትነብሩ
ውስተ ምድሮሙ ወውስተ ሀገሮሙ አንትሙ ፣ ወኢሰማ
ዕክሙ ቃልየ ።

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ፣ እናንተ በመንደ
ራቸውና በአገራቸው ከምትኖሩባቸው ከነዚህ ከአሞሬ
ዎን ጣኦታት የተነሣ አትፍሩ አልኋችሁ ፣ ነገር ግን ቃሌን
አልሰማችሁም አለ አላቸው ። ኢያ፡ ፳፬ ፲፭ ።

፲፩ ወመጽአ መልአከ እግዚአብሔር ወነበረ ታሕተ ዕፀ
እንተ ኤፍራታ ዘኢዮአስ አቡሁ ለኢያዝሬ ወጌዴዎን
ወልዱ ይዘብጥ ሥርናየ በውስተ ዐውዱ ከመ ያምስጥ
እምቅድሜሆሙ ለምድያም ።

እግዚአብሔርም የላከው መልአክ መጥቶ በኢያዝሬ
አባት በኢዮአስ እርሻ አጠገብ ባለች በኤፍራታ ዛፍ ሥር
ተቀመጠ ፣ ጌዴዎንም ከምድያም ሰዎች ፊት ያሸሽ ዘንድ
ሥንዴውን እያጨደ ይወቃ ነበር ። ኢያ፡ ፮ ፱ ።

፲፪ ወአስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር ወይቤሎ ፣ እግ
ዚአብሔር ምስሌከ ጽኑዐ ኀይል ።

የእግዚአብሔርም መላክተኛ ታየው ፣ ኃይልህ ጽኑ
የሆነ ጌዴዎን ! እግዚአብሔር ካንተ ጋር በረድኤት አለ
አለው ። ኢያ፡ ፩ ፭ ። ሉቃ፡ ፩ ፲፩ ።

፲፫ ወይቤሎ ጌዴዎን አሆ እግዚኦ እግዚእየ ወእመሰ ሀሎ
ወ እግዚአብሔር ምስሌነ ለምንት ረከበተነ ኵሉ ዛቲ እ
ኪት ወአይቴ ውእቱ ኵሉ ስብሐቲሁ ዘነገሩነ አበዊነ ወይ
ቤሉነ እምግብጽ አውፅአሙ ለአበዊነ እግዚአብሔር
ወይእዜሰ ኀደገነ እግዚአብሔር ወአግብአነ ውስተ እደ
ምድያም ።

ጌዴዎንም አሌቱ ጌታየ ! እሺ (ይሁን) ፣ ነገር ግን እግ
ዚአብሔር ከኛ ጋራ ካለ ይህች ሁሉ መከራ ለምን አገኘ
ችን ፤ እግዚአብሔር አባቶቻችንን ከግብጽ አወጣቸው ብ
ለው አባቶቻችን የነገሩን ተአምራትስ ሁሉ ወዴት አለ ፤
አሁን ግን እግዚአብሔር ተለየን በምድያም እጅም ጣለን
አለው ። ዘዳ፡ ፴፩ ፲፯ ። ኢያ፡ ፶፱ ፩ ።

፲፬ ወነፀሮ መልአከ እግዚአብሔር ወይቤሎ ሑር በኃይል
ክ ወታድኅኖሙ ለእስራኤል እምእደ ምድያም ወናሁ
ፈነውኩከ ።

እግዚአብሔር የላከው መልአክም እየው እስራኤልን
ከምድያም እጅ ታድናቸዋለህና ከሠራዊትህ ጋር ሂድ
እነሆ ላክሁህ አለው ። ኢያ፡ ፩ ፱ ። ፩ ሳሙ፡ ፲፪ ፲፩ ።

፲፭ ወይቤሎ ጌዴዎን አሆ እግዚኦ በምንት አድኅኖሙ
ለእስራኤል ፣ ናሁ አእላፍየኒ ውኑዳን በውስተ ምናሴ
ወአነኒ ንኡስ በውስተ ቤተ አቡየ ።

ጌዴዎንም አሌቱ ! እሺ ይሁን እነሆ በነገደ ምናሴ ዘን
ድ ወገኖቼ ጥቂቶች ናቸው እኔም በአባቴ ወገን ትንሽ
ነኝ እስራኤልን በምን አድናቸዋለሁ ፤ አለው ።

፲፮ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር እስመ እግዚአብሔር
ሀሎ ምስሌከ ወትቀትሎሙ ለምድያም ከመ አሐዱ ብእሲ ።

እግዚአብሔር የላከው መልአክም ፣ እግዚአብሔር
ካንተ ጋራ በረድኤት አለና ፣ የምድያምን ሰዎች እንደ
አንድ ሰው ታጠፋቸዋለህ አለው ። ዘፀ፡ ፫ ፲፪ ።

፲፯ ወይቤሎ ጌዴዎን እመ ረከብኩ ሞገሰ ቅድመ አዕይን
ቲከ ግበር ሊተ ተአምረ ከመ አንተ ውእቱ ዘትትናገር
ምስሌየ ።

ጌዴዎንም በፊትህ በለሟልነትን ካገኘሁ ከኔ ጋራ የም
ትናገር አንተ እንደ ሆንክ ምልክት አድርግልኝ አለው ።
ዘፀ፡ ፬ ፩ ፣ ፫ ፲፪ ።

፲፰ ኢትሑር እምዝየ እስከ እገብእ ኀቤከ ወአመጽእ
መሥዋዕትየ ወእሠይም ቅድሜከ ፣ ወይቤሎ አነ ውእቱ
ወእጸንሐከ እስከ ትገብእ ።

ወዳንተ እስክመለስ ድረስ ከዚህ አትሂድ መሥዋዕቱን
አምጥቼ በፊትህ ላኑር አለው ፣ መልአኩም እኔ ነኝ እስክ
ትመለስ ድረስ እጠብቅሃለሁ አለው ። ዘፍ፡ ፲፰ ፫ ።

፲፱ ወሖረ ጌዴዎን ወገብረ ማሕስአ ጠሊ ወዳፍንተ ናእት
ወአንበረ ውእተ ሥጋ ውስተ ከፈር ወወደየ ደሞ ውስተ
መቅጹት ወወሰደ ሎቱ ኀበ ዕፅ ወሰገደ ሎቱ ።

ጌዴዎንም ሄዶ አንድ የፍየል ጠቦት የቂጣም እንጐቻ
አዘጋጀ ፣ ያንንም ሥጋ በአንቀብ አኖረ ፣ ደሙንም በድስት
ውስጥ ጨመረ ወደ ዕንጨቱም ወሰደለት ለሱም ሰገደለት ።

፳ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር ንሣእ ሥጋሁ ወኅብ
ስተ ናእት ወሢም ላዕለ ውእቱ ኰኵሕ ወከዐው ደሞ ወገ
ብረ ከማሁ ።

እግዚአብሔር የላከው መልአክ የአንድ እንበሳ ሥጋ
ውን የቂጣውን እንጐቻ ወስደህ በደንጊያ ላይ አኑር ፣
ደሙንም አፍስ አለው ፣ እንዳለውም አደረገ ።

፳፩ ወአልዐለ መልአከ እግዚአብሔር በትሮ ወለከፎ ለውእቱ ሥጋ ወለውእቱ ናእት ወነደት እሳት እምይእቲ ኰኵሕ ወበልዐቶ ለውእቱ ሥጋ ወለውእቱ ናእት ፡ ወሖረ መልአከ እግዚአብሔር እምአዕይንቲሁ ።

የእግዚአብሔርም መላክተኛ በትሩን አንሥቶ ያነን ቂጣና ያነን ሥጋ ነካው ከዚያችም ድንጊያ እሳት ወጥታ ያነን ሥጋና ያነን ቂጣ በላችው የእግዚአብሔርም መልአክ ከዓይኖቹ ተሠወረ ። ዘሌዋ፡ ፱ ፳፬ ።

፳፪ ወአእመረ ጌዴዎን ከመ መልአከ እግዚአብሔር ውእቱ ወይቤ ጌዴዎን አአኰተከ እግዚአ እስመ ርኢኩ መልአከ እግዚአብሔር ገጸ በገጽ እመውት ።

ጌዴዎንም እግዚአብሔር የላከው መልአክ እንደሆነ አወቀ ፡ ጌዴዎን አቤቱ ! አመሰግንሃለሁ የእግዚአብሔርን መልአክ ፊት ለፊት አይቻለሁና እሞታለሁ አለ ።

፳፫ ወይቤሎ እግዚአብሔር ሰላም ለከ ኢትፍራህ ወኢትመውት ።

እግዚአብሔርም ፍቅር አንድነት ላንተ ይሁን ፡ (አይዞህ) አትፍራ አትሞትም አለው ። ዳን፡ ፲ ፲፱ ።

፳፬ ወነደቀ ጌዴዎን በሀየ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር ወሰመዮ ሰላመ እግዚአብሔር እስከ ዛቲ ዕለት ወእንዘ ዓዲሁ ሀለወ ውስተ ኤፍራታ አቡሁ ለኢያዝሪ ።

ጌዴዎንም በዚያ ለእግዚአብሔር መሠውያን ሠርቶ ስሙን እስከዚህች ቀን ድረስ የእግዚአብሔር ፍቅር አንድነት የተደረገበት አለው ይኸውም የተደረገው የኢያዝሪ አባት ገና በኤፍራታ ሳለ ነው ። ዘፍ፡ ፲፮ ፲፬ ።

፳፭ ወእምዝ በይእቲ ሌሊት ይቤሎ እግዚአብሔር ንሣእ ላሕመ መግዝአ ዘአቡከ ወካልአ ላሕመ ዘሰብዐቱ ዓመት ወንሥት ምሥዋዖ ለበዓል ዘአቡከ ወምስለ ዘላዕሌሁ ስብር ፤

ከዚህ በኋላ በዚያች ሌሊት እግዚአብሔር ያባትህን አንድ ገች ሰባት ዓመት የሆነውም ሁለተኛ በሬን አምጣ ያባትህን የጣኦቱን መሠውያ አፍልሰህ በላዩ ያለውንም ምስል ስበረው ። ዘፀ፡ ፴፬ ፲፫ ። መሳ፡ ፫ ፮ ።

፳፮ ወንድቅ በቱ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር አምላክከ ዘአስተርአየከ በውስተ ደብር ዘማእከ ዘበዝንቱ ደወል ወንሥኣ ውእተ ካልአ ላሕመ ወግበሮ መሥዋዕተ በውእቱ ዕፀ ዘሰበርከ ።

በዚህ አውራጃ ባለ በማእከ ተራራ ለታየህ ለፈጣሪህ እግዚአብሔር መሠውያን ሥራለት ያነንም ሁለተኛ በሬ አምጥተህ በዚያ በሰበርከው ዕንጨት ላይ ሠዋው አለው ። ዘዳግ፡ ፮ ፰ ።

፳፯ ወነሥአ ጌዴዎን ዐሠርተ ወሠለስተ አደወ እምአግብርቲሁ ወገብረ በከመ ይቤሎ እግዚአብሔር ፡ ወእምዝ ሰበ ፈርሀ ቤተ አቡሁ ወሰብአ ሀገሩ በዊአ መዓልተ ወሌሊተ ይበውእ ።

ጌዴዎንም አገልጋዮቹ ዓሥራ ሦስት ሰው ይዞ እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ ፡ ከዚህ በኋላ ቀን መግባትን ያገሩን ሰዎችና ያባቱን ወገኖች ቢፈራ ሌሊት ይገባ ነበር ። ዮሐ፡ ፫ ፪ ።

፳፰ ወጌሡ በጽባሕ ሰብአ ሀገሩ ወረከብዎ ንሡተ ለምሥዋዐ በዓል ወምስል ዘላዕሌሁ ስቡር ወላሕም መግዝእ ግቡር በቱ መሥዋዕተ በውእቱ ምሥዋዕ ዘነደቀ ።

የአገሩም ሰዎች በጧት ገስግሰው በሄዱ ጊዜ የጣኦቱን መሠውያ ፈርሶ በላዩም ያለ ምስል ተሰብሮ በዚያ በሠራው መሠውያ ላይ ሌላ በሬ ተሠውቶበት አገኙት ።

፳፱ ወተባሀሉ በበይናቲሆሙ መኑ ገብረ ዘንተ ግብረ ፡ ወኀሠሡ ወሐተቱ ወይቤሉ ጌዴዎን ወልደ ዮአስ ገብረ ዘንተ ግብረ ።

እስበሳቸውም ይህንን ሥራ የሠራ ማነው ፤ ተባበሉ ያደረገውንም ፈለጉ መረመሩ ፡ ይህንን የሠራ የዮአስ ልጅ ጌዴዎን ይሆናል አሉ ።

፴ ወይቤልዎ ሰብአ ሀገር ለዮአስ አምጽእ ወልደከ ይቅትልዎ እስመ ነሠተ ምሥዋዐ በዓል ወሰበረ ምስለ ዘላዕሌሁ ።

የአገሩም ሰዎች ዮአስን የጣኦቱን መሠውያ አፍርሷልና በላዩም ላይ ያለ ምስልን ሰብሯልና ይገድሉት ዘንድ ልጅህን አምጣ አሉት ።

፴፩ ወይቤሎሙ ዮአስ ለሰብእ እለ ይቀውሙ ላዕሌሁ አንትሙ ይእዜ ትትቤቀሉ ሎቱ ለበዓል ፡ አው አንትሙኑ ታድኅንዎ ከመ ትቅትሉ ዘገፍዖ ወእመሰ አምላክ ውእቱ እስከ ይጸብሕ ለይሙት ዘገፍዖ ወይትበቀሎ ለሊሁ ለዘነሠተ ምሥዋዒሁ ።

ዮአስም በጠላትነት የተነሡበትን ሰዎች አሁን ለጣኦቱ በቀሉን የምትመልሱለት እናንተ ናችሁን ፤ የበደለውን ትገድሉለት ዘንድ ወይስ የምታድኑት እናንተ ናችሁን ፤ ፈጣሪስ ከሆነ የበደለው ሰው እስከነጋ ድረስ ይሙት ፡ መሠውያውንም ያፈረሰውን ሰው እሱ ይበቀለው አላቸው ።

፴፪ ወሰመያ ለይእቲ ዕለት ዐውደ በዓል እስመ ነሠተ ምሥዋዖ ።

መሠውያውን አፍርሶበታልና ያችን ቀን የጣኦቱ ሽንገ የተደረገበት ቀን አላት ። ፩ ሳሙ፡ ፲፪ ፲፩ ፡ ፪ ፲፩ ፳፩ ።

፴፫ ወኵሉ ምድያም ወአማሌቅ ወደቂቀ ጽባሕ ተጋብኡ ላዕሌሁ ወዐደዉ ወኀደሩ ውስተ ቈላተ ኢይዝራኤል ።

አማሌቅና የምድያም ሰዎች ሁሉ በምሥራቅ ያሉ ልጆችም በሱ ላይ ተሰብስበው ወደሱ ተሻገሩ በኢይያዝራኤል አውራጃም አደሩ ። ኢያ፡ ፲፯ ፲፮ ። መሳ፡ ፮ ፫ ።

፴፬ ወአጽንዖ መንፈሰ እግዚአብሔር ለጌዴዎን ወነፍኀ ቀርነ ወወውዐ አብያዚር በድኅሬሁ ።

ጌዴዎንንም የእግዚአብሔር መንፈስ ረድኤት አጸናው ነጋሪትንም መታ ፡ አብያዚርም በኋላው ሁኖ ደነፋ ።

፴፭ ወፈነወ መላእክተ ውስተ ኵሉ ምናሴ ወአውየወ ውእቱኒ እምድኅሬሁ ወፈነወ መላእክተ ውስተ አሴር ወውስተ ዛብሎን ወንፍታሌም ወዐርጉ ወተቀበልዎሙ ።

ወደ ነገደ ምናሴም ሁሉ መልእክተኞችን ላከ ፡ እሱም ከኋላው ሁኖ ደነፋ ወደ ነገደ ዛብሎን ወደ ነገደ ንፍታሌምም መልእክተኞችን ላከ፡ ወጥተውም ተቀበሏቸው ።

፴፮ ወይቤሎ ጌዴዎን ለእግዚአብሔር እመ ታድኅኖሙ
ለእስራኤል በእዴየ በከመ ትቤ ፣ ናሁ አነ እሰፍሕ ፀምረ
ብዙተ ውስተ ዐውድ ።
፴፯ ወእምከመ ወረደ ጠል ውስተ ፀምር በሕቲቱ ወኵሉ
ምድር ይቡስ አአምር እንከ ከመ ታድኅኖሙ ለእስራኤል
በእዴየ በከመ ትቤ ፣ ወኮነ ከማሁ ።
፴፰ ወጌሠ ጌዴዎን በሳኒታ ወዐፀሮ ለውእቱ ፀምር ወወ
ፅአ ማይ እምውእቱ ፀምር ምልአ ዐይገን ።
፴፱ ወይቤሎ ጌዴዎን ለእግዚአብሔር ኢትትመዐዕ በመዓትከ
ላዕሌየ ወእንግርከ ካዕበ አሐተ ነገረ ፣ ፀምር ይኩን ይቡስ
እንተ በሕቲቱ ወውስተ ኵሉ ምድር ይረድ ጠል ።
፵ ወገብረ ከማሁ እግዚአብሔር በይእቲ ሌሊት ፣ ወኮነ
ይቡሰ ፀምር በሕቲቱ ወውስተ ኵሉ ምድር ወረደ ጠል ።

## ምዕራፍ ፯ ።

፩ ወጌሠ ሮብዓም ዘውእቱ ጌዴዎን ወኵሉ ሕዝብ ዘምስ
ሌሁ ወኀደሩ ውስተ ምድረ አሮኤድ ወትዕይንቶሙ ለም
ድያም ወለአማሌቅ እመንገለ መስዕ እምሥዋዕ ዘአንበሬም
ውስተ ቈላ ።
፪ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለጌዴዎን ብዙኅ ሕዝብ ዘምስ
ሌከ ከመ ዘኢይከል አግብኦቶሙ ለምድያም ውስተ እዴ
ሆሙ ከመ ኢይትመክሑ እስራኤል ላዕሌየ ወኢይበሉ
እዴነ አድኀነትነ ።
፫ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለጌዴዎን ንግሮሙ ለሕዝብ
ወበሎሙ ዘይፈርህ እምኔክሙ ወፈራህ ለይግባእ እም
ኀበ ሕዝብ ።
፬ ወተመይጡ እምድረ ገለአድ ወገብኡ እምሕዝብ
ክልኤቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ወተርፉ እልፍ ።
፭ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለጌዴዎን ዓዲ ብዙኅ ሕዝብ
አውርዶሙ ኀበ ማይ ወአመክሮሙ ለከ በህየ ወእለ አነ
እቤለከ እሙንቱ ይሑሩ ምስሌከ ወአውረዶሙ ኀበ
ማይ ለሕዝብ ።
፮ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለጌዴዎን ኵሎ ዘሰትየ በል
ሳኑ እማይ ከመ ዘይሰቲ ከልብ አቅም እንተ በሕቲቱ ወ
ኵሎ ዘአስተብረከ በብረኪሁ ከመ ይስተይ አቅም እንተ
በሕቲቱ ።
፯ ወኮነ ኍልቆሙ ለእለ ሰትዩ በልሳኖሙ ሠለስተ ምእ
ት ፣ ወእለሰ ተርፉ ሕዝብ አስተብረኩ በብረኪሆሙ ከመ
ይስተዩ ማየ ።
፰ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለጌዴዎን በእሉ ሠለስቱ ም
እት ብእሲ እለ ከመዝ ሰትዩ አድኀንክሙ ወአገብኦሙ
ለምድያም ውስተ እዴከ ወኵሉ ሕዝብ ይእትዉ ውስተ
አብያቲሆሙ ።
፱ ወይንሥኡ ምስሌሆሙ ሕዝብ ስንቀ ወአቅርንቲሆሙ
ወለኵሉ ሰብአ እስራኤል ፈንዎሙ ውስተ አብያቲሆሙ
ይእትዉ ወለእልክቱሰ ሠለስቱ ምእት ብእሲ አቅሞሙ
ምስሌከ ወትዕይንተ ምድያም መትሕቶሙ ውስተ ቈላ ።

ጌዴዎንም እግዚአብሔርን አድናቸዋለሁ እንዳልክ
እስራኤልን በእጄ ታድናቸው እንደሁ እነሆ እኔ በደበበይ
የተበዘተ ጸጕርን እዘረጋለሁ ።
ጠል በምድር ላይ ሳይወርድ በጠጕሩ ላይ ብቻ ቢወ
ርድ አድናቸዋለሁ እንዳልክ እስራኤልን በእጄ እንድታ
ድናቸው ያን ጊዜ አውቃለሁ አለው እንዳለውም ሆነ ።
ጌዴዎንም በማግሥቱ ማልዶ ሂዶ ያነን ጠጕር ጠመ
ቀው ፣ ከዚያም ጠጕር አንድ መንቀል ውኃ ወጣ ።
ጌዴዎን እግዚአብሔርን በቍጣህ አትቈጣኝ ፣ ዳግ
መኛ አንድ ጊዜ ልናገር በጠጕሩ ላይ ብቻ ሳይወርድ ጠል
በምድር ሁሉ ላይ ይውረድ አለው ። ዘፍ፣ ፲፰ ፴፪ ።
እግዚአብሔርም በዚያች ሌሊት እንዳለው አደረገ ፣
ጠጕሩ ብቻ ደረቅ ሁኖ ጠል በምድር ሁሉ ላይ ወረደ ።

## ምዕራፍ ፯ ።

ሮብዓምም ማልዶ ሄደ ይኸውም ጌዴዎን ነው ከሱ ጋር
ያሉ ወገኖቹም ሁሉ ሄዱ ፣ አሮኤድ በሚባልም አገር ሰፈ
ሩ ፣ የአማሌቅና የምድያም ሠራዊትም በእንበሬም ቈላ
መሠውያ ቀኝ ሰፈሩ ። መሳ፣ ፮ ፴፪ - ፴፫ ።
እግዚአብሔርም ጌዴዎንን እጃችን (ሥልጣናችን) አዳ
ነችን ብለው በኔ እንዳይመኩ የምድያምን ሰዎች በእጃ
ቸው መጣል እንደማልችል ካንተ ጋራ ያሉ ሕዝብ ብዙ
ናቸው አለው ። ዘፀ፣ ፳ ፱ ። ዘዳ፣ ፳ ፲፯ ።
እግዚአብሔር ጌዴዎንን እንዲህ አለው ፤ ከናንተ የሚ
ፈራ የሚደነግጥ ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይመለስ ብለህ
ለሕዝቡ ንገራቸው አለው ።
ሕዝቡም ከገለዓድ ተመለሱ ፣ ከሕዝቡ ሁለት እልፍ
ከሁለት ሺሕ ተመልሰው እልፍ ሰዎች ቀሩ ።
እግዚአብሔር ጌዴዎንን ገና ብዙ ሕዝብ አሉ ፣ ወደ
ውኃ አውርደህ በዚያ ፈትናቸው እኔ ይሂዱ የምልህ ሰዎ
ች እነሳቸው ካንተ ጋራ ይሂዱ አለው ፣ ሕዝቡንም ወደ
ውኃ አወረዳቸው ። ኢሳ፣ ፰ ፳፩ ። መዝ፣ ፲፯ ፫ ፳፯ ፪ ።
እግዚአብሔር ጌዴዎንን ውሻ በምላሱ ጠለፍ ጠለፍ
አድርጎ እንዲጠጣ ከውኃው በምላሱ ጠለፍ ጠለፍ አድርጎ
የሚጠጣውን ሁሉ ለብቻው አቁመው ውኃን ይጠጣ ዘንድ
በጕልበቱ የተንበረከከውንም ሁሉ ለብቻው አቁመው
አለው ።
በምላሳቸው ጠለፍ ጠለፍ አድርገው የጠጡ ሰዎች
ቍጥራቸው ሦስት መቶ ሆነ ፣ የቀሩት ሕዝብ ግን ውኃ
ይጠጡ ዘንድ በጕልበታቸው ተንበረከኩ ።
እግዚአብሔርም ጌዴዎንን እንደዚህ (በእጃቸው ውኃ
በጠጡት) በነዚህ ሦስት መቶ ሰዎች አድናችኋለሁ የምድ
ያምንም ሰዎች በእጅህ እጥላቸዋለሁ ሕዝቡም ሁሉ ወደ
ቤታቸው ይመለሱ አለው ።
ሕዝቡን ስንቃቸውን ከነሳቸው ጋር ይውሰዱ መለከቶ
ቻቸውንም ይውሰዱ ወደ ቤታቸውም ይገቡ ዘንድ የእስ
ራኤልን ወገን ሁሉ አሰናብታቸው እለዚህ ሦስት መቶ
ሰዎች ግን ካንተ ጋር አቈያቸው አለው ፣ የምድያምም
ሠራዊት በበታቻቸው በቈላ ሰፍረው ነበር ።

| | | |
|---|---|---|
| ፱ | ወእምዝ በይእቲ ሌሊት ይቤሎ እግዚአብሔር ተንሥእ ወረድ ፍጡነ እምዝየ ውስተ ትዕይንት እስመ አግባእክዎ ውስተ እዴከ ። | ከዚህ በኋላ በዚያች ሌሊት እግዚአብሔር ምድያምን በእጅህ ጥያቸዋለሁና ከዚህ ተነሥተህ ፈጥነህ ወደ ሰፈር ውረድ አለው ፤ ዘፍ፡ ፵፮ ፪ ፡ ፫ ። መሳ፡ ፯ ፪፡ ፫ ፳፰ ። |
| ፲ | ወእመሰ ትፈርህ በሕቲትከ ወሪደ ረድ አንተ ወፉራን ቍልዔከ ውስተ ትዕይንት፤ ወአጽምእዎሙ ዘይትናገሩ ወእምዝ ይጸንዓ እደዊከ ። | ብቻህን መውረድ ብትፈራ ግን ብላቴናህ ፉራንና አንተ ወደ ሰፈር ወርዳችሁ የሚናገሩትን አድምጧቸው ከዚህ በኋላ እጆችህ (ለመወርወር ቃልህ ለመምከር) ይጸናሉ አለው ። |
| ፲፩ | ወወረደ ውእቱ ወፉራን ቍልዔሁ ውስተ አሐዱ ደብር ዘኀምሳ እምትዕይንት ። | እሱም ከብላቴናው ከፉራን ጋር ከሰፈሩ አንድ ወገን የአምሳ አለቃ ወደ ሰፈረበት ወረደ ። |
| ፲፪ | ወምድያም ወአማሌቅ ወኵሎሙ ደቂቀ ጽባሕ ኀዱራን እሙንቱ ውስተ ቈላት ከመ አንበጣ ብዝኆሙ ወአግማሊሆሙ ዘአልቦ ኍልቍ እለ ከመ ኆፃ ዘከንፈረ ባሕር እሙንቱ ብዝኆሙ ። | የአማሌቅና የምድያም ሰዎች በምሥራቅ ያሉም ልጆች ሁሉ እንደ አንበጣ በዝተው እነሳቸው በቈላ ሰፍረው ነበር ፤ ግመሎቻቸውም ብዛታቸው በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ ስፍር ቍጥር የላቸውም ነበር ። ኢ.ያ፡ ፲፩ ፱ ። |
| ፲፫ | ወቦአ ጌዴዎን ወናሁ አሐዱ ብእሲ ይነግሮ ለካልኡ ሕልሞ ወይቤሎ ሐለምኩ ሕልመ ወእሬኢ ኅብስተ ሰገም ታንኰረኵር ውስተ ትዕይንተ ምድያም ወቀተለታ ወአውደቀታ ወገፍትዓታ እምላዕሉ ወወድቀት ትዕይንት ። | ጌዴዎንም ወደ ሰፈር ገባ ፤ እነሆም አንድ ሰው ለባልንጀራው ሕልም አየሁ ፤ የገብስ እንጀራ ወደ ምድያም ሰፈር ተንከባልላ ወርዳ ፈጽማ ስታጠፋት ሰፈሬቱም ስትጠፋ አየሁ ብሎ ሕልሙን ሲነግረው ። |
| ፲፬ | ወአውሥአ ካልኡ ወይቤሎ ኢኮነ ዝንቱ እንበለ ኵናተ ጌዴዎን ወልደ ዮአስ ብእሲ እስራኤላዊ ወአግብኦሙ እግዚአብሔር ለምድያም ውስተ እዴሁ ወለኵሉ ትዕይንቶሙ ። | ባልንጀራውም ከእስራኤል የተወለደ ሰው የዮአስ ልጅ የጌዴዎን ጦር ነው እንጂ ይህ ነገር ሌላ አይደለም የምድያምንም ሰዎች ሠራዊቶቻቸውንም ሁሉ እግዚአብሔር በእጁ ጣላቸው ብሎ ሲመልስለት ሰማ ። |
| ፲፭ | ወእምዝ ሰበ ሰምዐ ጌዴዎን ፍካሬ ሕልሙ ወዘከመ ነገሮ ሕልሞ ሰገደ ለእግዚአብሔር ወገብአ ውስተ ትዕይንተ እስራኤል ወይቤሎሙ፤ ተንሥኡ እስመ አግብኦሙ እግዚአብሔር ውስተ እዴነ ለትዕይንተ ምድያም ። | ከዚህ በኋላ ጌዴዎን የሕልሙን ትርጓሜንና ሕልሙንም እንደ ነገረው በሰማ ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰገደ ፤ ወደ እስራኤልም ሰፈር ተመልሶ የምድያምን ሰዎች እግዚአብሔር በእጃችን ጥሏቸዋልና ተነሡ አላቸው ። |
| ፲፮ | ወከፈሎሙ ለሠለስቱ ምእት ብእሲ ኀበ ሠለስቱ ሠራዊት ወወሀቦሙ ቀርነ ለኵሎሙ ውስተ እደዊሆሙ ወመሳብከተ ፅሩቃተ ፤ ወመኃትወ ውስተ ማእከለ ውእቱ መሳብክት ። | ሦስት መቶውን ሰዎች ሦስት ሠራዊት አድርጎ ከፈላቸው ፤ ለሁሉም በእጃቸው መለከት ሰጣቸው ፤ ባዶ የሆኑ ማሰሮዎችንም ሰጣቸው ፤ በነዚያም ማሰሮች ውስጥ መብራት ነበር ። ዘፍ፡ ፲፬ ፲፭ ። መሳ፡ ፮ ፳ ፡ ፲፬ ፱ ። |
| ፲፯ | ወይቤሎሙ እምኔየ ርእዩ ወከማሁ ግበሩ ፤ ወናሁ አነ እበውእ ውስተ ማእከለ ትዕይንት ወዘከመ ገበርኩ ግበሩ ። | እኔን ተመልከታችሁ እንደዚሁ አድርጉ ፤ እነሆ እኔ ወደ ሰፈሩ መከከል እገባለሁ እኔ እንደ ማደርገው አድርጉ ። |
| ፲፰ | ወእነፍኅ ቀርነ አነ ወኵሉ እለ ምስሌየ ወንፍኁ ቀርነ አንትሙኒ በዐውደ ትዕይንት ወበሉ ኃይል ዘእግዚአብሔር ወኲናት ዘጌዴዎን ። | እኔ መለከት እነፋለሁ ፤ ከኔ ጋር ያሉ ሰዎችም ሁሉ ይነፋሉ ፤ እናንተም በሰፈሩ ዙርያ መለከት ንፉ ፤ ኃይል የእግዚአብሔር ጦር የጌዴዎን ነው ፤ በሉ አላቸው ። |
| ፲፱ | ወቦአ ጌዴዎን ወምእት ብእሲ ምስሌሁ ውስተ አሐዱ ኅብረ ትዕይንት በቀዳሚት ሰዓት ዘመንፈቀ ሌሊት እንበለ ይንቅሑ ሰብአ መዓቅብ ወነፍኁ ቀርነ ወነጽሑ እልክተ መሳብክተ ዘውስተ እደዊሆሙ ። | ጌዴዎንም ወደ ሰፈር ገባ ፤ ከሱ ጋር ያሉ መቶ ሰዎችም ከሌሊቱ እኩሌታ በመጀመርያው ሰዓት ዘብ የሚጠብቁ ሰዎች ሳይነቁ ከሰፈሩ ወደ አንድ ወገን ገብተው መለከት ነፉ ፤ በእጃቸው ያሉ እነዚያንም ማሰሮች ከእጃቸው ጣሉ ። |
| ፳ | ወነፍኁ ቀርነ እልክቱ ሠለስቱ ሠራዊት ወነጽሑ መሳብክቲሆሙ ወአልዓሉ መኃትዊሆሙ ዘውስተ እደዊሆሙ ዘጸጋም ወዘውስተ እደዊሆሙ ዘየማን ቀርን ዘበቱ ይነፍሑ ወጸርኁ ወይቤሉ፤ ኲናት ዘእግዚአብሔር ወዘጌዴዎን ። | እነዚያም ሦስቱ ወገን ሠራዊት መለከት ነፉ ፤ ማሰሮቻቸውንም ጣሉ ፤ በግራ እጃቸው ያሉ መብራቶቻቸውንም ከፍ ከፍ አደረጉ ፤ በቀኝ እጃቸውም የሚነፉበት መለከት ነበር ፤ ይህ የጌዴዎንና የእግዚአብሔር ሰልፍ ነው ብለው ጮኹ ። |
| ፳፩ | ወቆሙ ኵሎሙ በበመካናቲሆሙ በውስተ ዐውደ ትዕይንት ወጐዩ ኵሉ ትዕይንት ወደንገፁ ። | ሁሉም በሰፈሩ ዙርያ በየቦታቸው ቆሙ ፤ ሠራዊትም ሁሉ ደንግጠው ሸሹ ። ዘፀ፡ ፲፬ ፲፫ ፤ ፲፯ ፳፱ ። |
| ፳፪ | ወነፍኁ ሠለስተ ምእተ አቅርንተ ወአግብአ እግዚአብሔር መጥባሕተ ብእሲ ላዕለ ካልኡ በውስተ ኵሉ ትዕይንት ወጐዩ ትዕይንቶሙ እስከ በሴጣ ወእስከ አቤልሚሁላ ወውስተ ገባአን ። | ሦስት መቶ መለከቶችንም ነፉ ፤ እግዚአብሔር በሰፈሩ ሁሉ ያንዱን ሰው ሰይፍ ወዳንዱ መለሰ ሠራዊቶቻቸውም እስከ አቤልሚሁላና እስከ በሴጣ ፤ እስከ ገበያንም ድረስ ሸሹ ። |

፳፫ ወአውየዉ ሰብአ እስራኤል እምንፍታሌም ወእምአ
ሴር ወእምኵሉ ምናሴ ወዴገንዎሙ ለምድያም ።

፳፬ ወፈነወ ጌዴዎን መልእክተ ውስተ ኵሉ ደወለ ኤፍ
ሬም እንዘ ይብል ረዱ ተቀበልዎሙ ለምድያም ወር
ከብዎሙ በኀበ ማይ እስከ ቤታራ ወዮርዳኖስ፤ ወአውየዉ
ኵሉ ሰብአ ኤፍሬም ወቀደምዎሙ ኀበ ማይ እስከ ቤታራ
ወዮርዳኖስ ።

፳፭ ወአኀዝዎሙ ለክልኤቱ መላእክተ ምድያም ለሄሬብ
ወለዜብ ወቀተልዎ ለሄሬብ በሴሬን ወለዜብ ቀተልዎ በኢ
ያሬቅ፤ ወዴገንዎሙ ለምድያም ወአምጽኡ አርእስቲሆሙ
ለሄሬብ ወለዜብ ኀበ ገዴዎን እማዕዶተ ዮርዳኖስ ።

የእስራኤልም ወገኖች ከአሴር ነገድና ከንፍታሌም ነገድ ከምናሴም ነገድ ሁሉ ተጯጩኸው የምድያምን ሰዎች ተከትለው አሳደዱዋቸው ። መሳ፡ ፮ ፴፭ ።

ጌዴዎንም ወርዳችሁ የምድያምን ሰዎች ተቀበሏቸው እስከ ዮርዳኖስና እስከ ቤታራ ድረስም ሂዳችሁ በውኃው አጠገብ ተገናኙዋቸው ብሎ ወደ ኤፍሬም ነገድ አውራጃ ሁሉ መልእክትን ላከ፤ የኤፍሬምም ነገድ ሁሉ ተጯጩኸው እስከ ዮርዳኖስና እስከ ቤታራ ድረስ ቀደሟቸው ። ኢያ፡ ፲፯ ፴፫ ።

ሁለቱን የምድያም አለቆች ዜብንና ሄሬብን ያዙዋቸው፤ ሄሬብን በሴሬን ገደሉት፤ ዜብንም በኢያሬቅ ገደሉት፤ የምድያምንም ሰዎች ተከትለው፤ የዜብንና የሄሬብን ቸብቸቦቻቸውን ቈርጠው ከዮርዳኖስ ማዶ ወደ ጌዴዎን አመጡ ።

## ምዕራፍ ፰ ።

፩ ወይቤልዎ ሰብአ ኤፍሬም ምንት ውእቱ ዝንቱ ነገር
ዘገበርከ ላዕሌነ ከመ ኢትጸውዐነ አመ ሖርከ ትትቃተ
ሎሙ ለምድያም፤ ወቀሠፍዎ ምስሌሁ ዐቢየ ተስናነ ።
፪ ወይቤሎሙ ምንተ ገበርኩ ይእዜ ከመዝ አንትሙ
ኢትኄይሱኑ ቈጽለ ኤፍሬም እምቀሥመ አብያዜር ።

፫ አኮኑ ውስተ እዴክሙ አግብአሙ እግዚአብሔር ለመ
ላእክተ ምድያም ለሄሬብ ወዜብ ወምንተ ክህልኩ ገቢረ
ከማክሙ፤ ወእምዝ ኀደግዎ እንከ ወአዕረፈት ነፍሶሙ
እምኔሁ ሶበ ይቤሎሙ ዘንተ ቃለ ።
፬ ወመጽአ ጌዴዎን ኀበ ዮርዳኖስ ወዐደወ ውእቱ ወአ
ልክቱ ሠለስቱ ምእት ብእሲ እለ ምስሌሁ ወእንበዙ ሰበ
ርኀቡ ።
፭ ወይቤሎሙ ለሰብአ ሰኮት ሀብዎሙ እክለ ለሕዝብ እለ
ምስሌየ እስመ ርኅቡ ወአንሰ እተልዎሙ ለዜብሄል ወለስ
ልማና ነገሥተ ምድያም ።
፮ ወይቤልዎ መላእክተ ሰኮት በኑ እዴሆሙ ለዜብሄል
ወስልማና ይእዜ ውስተ እዴከ ከመ ነሀቦሙ እክለ ለሠ
ራዊትከ ።
፯ ወይቤሎሙ ጌዴዎን እከ ከመዝ እምከመ አግብአሙ እግ
ዚአብሔር ለዜብሄል ወለስልማና ውስተ እዴየ እሰቅል ሥጋ
ክሙ ውስተ ዐቀበት ዘገዳም ወውስተ ክልኤ አርቆሚን።
፰ ወዐርገ እምህየ ውስተ ፋኑኤል ወይቤሎሙ ከመዝ
ወይቤልዎ ሰብአ ፋኑኤል በከመ ይቤልዎ ሰብአ ሰኮት ።
፱ ወይቤሎሙ ለሰብአ ፋኑኤል ሶበ ገባእኩ በዳኅን እነ
ሥቶ ለዝንቱ ማኅፈድ ።
፲ ወዜብሄልስ ወስልማና ውስተ ቀርቀር ወትዕይንቶሙኒ
ምስሌሆሙ ወየአክሉ እልፈ ወኀምስ ምእተ ኵሎሙ እለ
ተርፉ እምኵሉ ትዓይኒሆሙ ለደቂቀ ጽባሕ ወእለሰ ወድቁ
ዐሠርቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ብእሲ እለ ይሰውሩ ኩናተ ።
፲፩ ወዐርገ ጌዴዎን ፍኖተ እለ ይነብሩ ውስተ አዕጻዳት
ጽባሒውያን እለ መንገለ ናቤት ላዕለ ዘብሄል ወስልማና
ወቀተለ ትዕይንቶሙ እንዘ ይትአመኑ ።

የኤፍሬም ነገድ የምድያምን ሰዎች ትወጋቸው ዘንድ በሄድክ ጊዜ እንዳትጠራን በኛ ያደረግኸው ይህ ነገር ምንድር ነው፤ ብለው ከሱ ጋር ጽኑ ጸብን ተጣሉ ።

እንዲህ ትሉኝ ዘንድ አሁን ምን አደረግሁ ከኤፍሬም ወይን ቃርሚያ የአብያዜር ወይን መከር (ከአብያዜር መዝመት የናንተ አለመዝመት) አይሻልምን!

የምድያምን አለቆች ሄሬብንና ዜብን እግዚአብሔር በእጃችሁ የጣላቸው አይደለምን! እንደናንተ ማድረግ ምን ተቻለኝ፤ አላቸው፤ ከዚህ በኋላ ተዉት ይህን ነገር በነገራቸው ጊዜ ሰውነታቸው እሱን ከመጣላት ሀረፈች ።

ጌዴዎንም ወደ ዮርዳኖስ መጥቶ ተሻገረ፤ ከሱ ጋራ ያሉ እነዚያም ሦስት መቶ ሰዎች ተሻገሩ፤ በተራቡም ጊዜ አእምሯቸውንም አጡ ። መሳ፡ ፯ ፯ ።

የሰኮትንም ሰዎች ከኔ ጋራ ያሉ ወገኖች ተርበዋልና እኽል ስጡዋቸው፤ እኔ ግን የምድያምን ነገሥታት ስልማናንና ዜብሄልን እከተላቸዋለሁ አላቸው ።

የሰኮትም አለቆች ለሠራዊትህ እኽል እንሰጣቸው ዘንድ በውኑ የስልማናና የዜብሄል እጆች በእጅህ ተይዘዋልን፤ አሉት ። ፩ ሳሙ፡ ፳፭ ፲፩ ።

ጌዴዎን ነገሩ እንዲህ አይደለም ስልማናንና ዜብሄልን በእጄ የጣላቸው እንደሆነ በምድረ በዳ ባለ ተራራ ላይ በሁለት መንታ ባላ ሥጋችሁን እሰቅላለሁ አላቸው ።

ከዚያም ወደ ፋኑኤል ወጥቶ እንዲህ አላቸው! የፋኑኤልም ሰዎች የሰኮት ሰዎች እንዳሉት መለሱለት ።

የፋኑኤልን ሰዎች በደህና በተመለስኩ ጊዜ ይህን ግምብ አፈርሰዋለሁ አላቸው ። መሳ፡ ፰ ፲፯ ።

ስልማናና ዜብሄል ግን ከሠራዊቶቻቸው ጋራ በቀርቀር (በገምጃ) ነበሩ፤ ከምሥራቅ ከሉ ሰዎች ሠራዊት የቀሩት ሁሉ አሥራ አምስት ሺሕ ይሆናሉ፤ የጠፉት ግን ሰጦር የደረሱ ሃያ እልፍ ከሁለት ሺሕ ናቸው ።

ጌዴዎንም በናቤት ያሉ በምሥራቅ ሰዎች በሉበትበት በሚኖሩ ሰዎች መንገድ ወደ ዜብሄልና ወደ ስልማና መጥቶ ተዘልለው ሳሉ ሠራዊታቸውን አጠፋ ።

፲፪ ወጐዩ ዜብሄል ወስልማና ወዴገኖሙ ወተለዎሙ ወአኀዘሙ ለክልኤሆሙ ነገሥተ ምድያም ለዜብሄል ወለስልማና ወለኵሉ ትዕይንቶሙ ቀጥቀጦሙ ጌዴዎን ።

ዜብሄልና ስልማናም ሸሹ ፤ ተከትሎም ሁለቱን የምድያምን ነገሥታት ስልማናንና ዜብሄልን ያዛቸው ሠራዊቶቻቸውንም ጌዴዎን አጠፋቸው ።

፲፫ ወተመይጠ ጌዴዎን ወልደ ዮአስ እምፀብእ እምዐቀበ አሩስ ።

የዮአስ ልጅ ጌዴዎንም ከአሩስ አቀበት ከሰልፍ ተመለሰ ። መኀ፡ ፰፫ ፲፩ ።

፲፬ ወአኀዘ አሐደ ወልደ እምሰብአ ሰኮት ወሐተቶ ወአጽሐፎሙ ለመላእክተ ሰኮት ወለሊቃናቲሃ ሰብዓ ወሰብዐቱ ብእሲ ።

ከሱኮት ሰዎች አንድ ብላቴና ይዞ መረመረው ፤ ሰባ ሰባቱን ሽማግሌዎችንም አስቈጠራቸው ።

፲፭ ወበጽሐ ኀበ መላእክተ ሰኮት ወይቤሎሙ ነዮሙ ዜብሄል ወስልማና እለ በሙ ተፀየርክሙኒ ወትቤሉኒ በኑ እዴሆሙ ለዜብሄል ወስልማና ይእዜ ውስተ እዴከ ከመ ንሁብሙ እክለ ለእለ ርኅቡ ሰብእከ ።

ወደ ሱኮት አለቆችም በደረሰ ጊዜ ለተራቡ ሠራዊትህ እኽልን እንሰጣቸው ዘንድ ስልማናና ዜብሄል በውኑ አሁን በእጅህ አሉን ብላችሁ በነሱቸው የተገዳደራችሁባቸው ስልማናና ዜብሄል እነሆ እነዚህ ናቸው አላቸው ።

፲፮ ወነሥአሙ ለሰብአ ሰኮት ወለሊቃናቲሆሙ ወለመላእክቲሆሙ ወሰቀሎሙ ውስተ ዐቀበተ ገዳም ወውስተ በራቅኒም ወሰቀሎሙ ምስሌሆሙ ለሰብአ ሰኮት ።

የሱኮትን ሰዎች ሽማግሎቻቸውንና አለቆቻቸውን ይዞ በበራቅኒምና በምድረ በዳ ባለ ተራራ ፀጉ ባላ በለውዕንጨት ሰቀላቸው የሱኮትንም ሰዎች ከነሱቸው ጋራ ሰቀላቸው ። መሳ፡ ፰ ፱ ።

፲፯ ወነሠቶ ለማኅፈደ አናምሄል ወቀተሎሙ ለሰብአ ፋኑሄል ወለሀገሮሙኒ ።

የአናምሄልንም ግምብ አፈረሰው ፤ የፋኑሄልንም ሰዎች ከነሱቸው ጋራ አጠፋቸው ፤ አገራቸውን አጠፋ ።

፲፰ ወይቤሎሙ ለዜብሄል ወለስልማና አይቴ እደው እለ ቀተልክምዎሙ በታቦር ፤ ወይቤልዎ ከማከ እሙንቱ ፤ ወኪያከ ይመስሉ እሙንቱ ወከመ ርእየተ ገጸ ደቂቀ ነገሥት ገጾሙ ።

ስልማናንና ዜብሄልን በታቦር የገደላችኋቸው ሰዎች ማንን ይመስላሉ አላቸው ፤ እንዳንተ ያሉ ናቸው ፤ እነሱቸው አንተን ይመስላሉ ፤ መልካቸው እንደ ንጉሥ ልጆች መልክ አስተያየት ነው አሉት ።

፲፱ ወይቤሎሙ ጌዴዎን አኀውየ እሙንቱ ደቂቀ እምየ ወመሐለ ሎሙ ወይቤሎሙ ሕያው እግዚአብሔር ሶበ አሕየውክምዎሙ ከመ እምኢቀተልኩክሙ ።

ጌዴዎንም የናቴ ልጆች ወንድሞቼ ናቸው እነሱቸውን በትገድሏቸው ሕያው እግዚአብሔርን በልገደልኋችሁም ነበር ብሎ ማለላቸው ። ሩት ፫ ፲፫ ።

፳ ወይቤሎ ለዮቶር በኵሩ ተንሥእ ቅትሎሙ ወኢመልሐ መጥባሕቶ ውእቱ ሕፃን እስመ ንኡስ ውእቱ ወፈርሀ ።

የበኩር ልጁ ዮቶርን ተነሥተህ ግደላቸው አለው ፤ ያም ብላቴና ሕፃን ስለሆነ ፈርቷልና ሰይፉን አልመዘዘም ።

፳፩ ወይቤልዎ ዜብሄል ወስልማና ተንሥእ አንተ ወተራከበነ እስመ ከመ ብእሲ ውእቱ ኀይልከ ።

ስልማናና ዜብሄልም ኃይልህ እንደ አርበኛ ሰው ኃይል ነውና አንተ ተነሥተህ ተገናኘን (ግደለን) አሉት ።

፳፪ ወተንሥአ ጌዴዎን ወቀተሎሙ ለዜብሄል ወለስልማና ፤ ወነሥአ በዝግናተ ዘውስተ ክሳዳተ አግማላቲሆሙ ።

ጌዴዎንም ተነሥቶ ስልማናንና ዜብሄልን ገደላቸው በግመሎቻቸው አንገት የነበረ ዝርግፋቸውን ወሰደ ።

፳፫ ወይቤልዎ ሰብአ እስራኤል ለጌዴዎን ተመልአክ ለነ አንተ ወደቂቅከ እስመ አድኀንከነ እምእዴሆሙ ለምድያም ።

የእስራኤልም ሰዎች ከምድያም ሰዎች እጅ አድነኸናልና አንተ ከልጅህ ጋራ ገዢ ሁነን አሉት ።

፳፬ ወይቤሎሙ ጌዴዎን ኢይትመለአክ አንሰ ለክሙ ወወልድየኒ ኢይትመለአክ ለክሙ ፤ እግዚአብሔር ይትመለአክ ለክሙ ።

ጌዴዎንም እግዚአብሔር ገዢ ይሁናችሁ እንጂ እኔስ ገዢ አልሆናችሁም ልጄም ገዢ አይሆናችሁም አላቸው። ዘፍ፡ ፲፮ ፲ ፤ ፳፭ ፲፫ ፤ ፴፯ ፳፭ ።

፳፭ ወይቤሎሙ ጌዴዎን እስእል እምኔክሙ ስእለተ ወሀቡኒ ብእሲ ብእሲ አእኑገ ዘወርቅ ዘሰለበ እስመ ብዙኀ አእኑግ በሙ እስመ እስማዔላውያን እሙንቱ ።

ጌዴዎንም ከናንተ ልመናን እለምናለሁ እነሱ እስማኤላውያን (ነጋድያን) ስለ ነበሩ ብዙ ጉትቻ ነበራቸውና አንዱም አንዱም ሰው የዘረፈውን የወርቅ ጉትቻ ስጡኝ አላቸው ።

፳፮ ወይቤሉ ውሂበ ንሁብ ወሰፍሐ ልብሶ ወገደፉ ብእሲ ብእሲ አእኑገ ዘሰለበ ።

እነሱም መስጠትን እንሰጣለን አሉት ፤ እሱም ልብሱን ዘረጋና አንዱም አንዱም ሰው የዘረፈውን ጉትቻ ጣለ ።

፳፯ ወኮነ ድልወተ ወርቀ አእኑጊሁ ዘሰአሎሙ ዐሠርተ ወተስዓተ ምእተ በሰቅል ወርቁ እንበለ አውጻባት ወበዝግናት ወኤፎት ወመዋጥሕ ዘሜላት ዘላዕለ ነገሥተ ምድያም ወእንበለ ሐብላተ ወርቅ ዘውስተ ክሳዳተ አግማላቲሆሙ ።

የለመናቸው የወርቁ ጉትቻ ሚዛን ከዝርግፋቸውና ከቀለበታቸው ከንፏቸውም የምድያም ነገሥታት ከሚለብሱት ከነጭ ሐር መጐናጸፊያቸው በግመሎቻቸው አንገት ካለ ከሥሉሳቸው በቀር ወርቁ በሚዛን ዓሥራ ዘጠኝ መቶ ሆነ ።

፳፰ ወገብረ ሎቱ ጌዴዎን ምስለ ወአቀሞ ውስተ ሀገሩ ውስተ ኤፍራታ ወዘመወ በቱ ኵሉ እስራኤል ወተለውዎ

ጌዴዎንም ምስል አሠርቶ በአገሩ በኤፍሬታ አቆመው እስራኤልም ሁሉ በሱ ሳቱ ፤ እሱንም አመለኩት በጌዴ

በሀየ ወከኖ ጌጋየ ለጌዴዎን ወለቤቱ ።
፳፰ ወተትሕቱ ምድያም በቅድሜሆሙ ለእስራኤል ወኢ
ደገሙ እንከ አልዕሎ ርእሶሙ ወአዕረፈት ምድር አርብዓ
ዓመተ በመዋዕለ ጌዴዎን ።
፳፱ ወሖረ ሮብዓም ወልደ ዮአስ ወነበረ ውስተ ቤቱ ።
፴ ወቦ ለጌዴዎን ሰብዓ ደቂቅ እለ ወፅኡ እምሐቌሁ
እስመ ብዙኃት አንስትያሁ ።
፴፩ ወዕቀብቱ ዘውስተ ሰቂማስ ወለደት ሎቱ ወልደ ወሰ
መየ ስሞ አቤሜሌክ ።
፴፪ ወሞተ ጌዴዎን ወልደ ዮአስ በሀገረ ሲናት ወተቀብረ
ውስተ መቃብረ አቡሁ ዮአስ በኤፍራታ ወአብያዜር ።

፴፫ ወእምዝ ሶበ ሞተ ጌዴዎን ተመይጡ ደቂቀ እስራኤል
ወተለውዎ ለበዓሊም ወተከየዱ ምስሌሁ ለበዓሊም ከመ
ይኩኖሙ አምላኮሙ ።
፴፬ ወኢተዘከርዎ ለእግዚአብሔር አምላኮሙ ዘአድኀ
ኖሙ እምእደ ኵሉ ፀሮሙ እለ ዐውዶሙ ።
፴፭ ወኢገብሩ ምሕረተ ምስለ ቤተ ሮብዓም ዘውእቱ ጌዴ
ዎን በኵሉ ሠናይት እንተ ገብረ ምስለ እስራኤል ።

ምዕራፍ ፱ ።

፩ ወሖረ አቤሜሌክ ወልደ ሮብዓም ውስተ ሰቂማ ኀበ
አኀወ እሙ ወተናገሮሙ ለኵሎሙ አዝማደ ቤተ እሙ ።

፪ ወይቤሎሙ ተናገርዎሙ ሊተ ለሰብአ ሰቂማ ወበል
ዎሙ ምንት ይኄይሰክሙ ሰብዓኑ ብእሲ ይኰንኑክሙ
ኵሎሙ ደቂቀ ሮብዓም ፣ አው አሐዱ ብእሲ ይኰንንክሙ
ወተዘከሩ ከመ ሥጋክሙ ወዐጽምክሙ አነ ።
፫ ወተናገሩ ሎቱ አኀወ እሙ ምስለ ኵሉ ሰብአ ሰቂማ
ኵሎ ዘንተ ነገረ ወሜጥዎ ለልበሙ ኀበ አቤሜሌክ ወይ
ቤሉ እኁነ ውእቱ ።
፬ ወወሀብዎሙ ሰብዐ ብሩረ እምቤተ በዓል ወተዓሰበ
በን አቤሜሌክ እደወ ሐቃልያነ ወመደንግፃነ ወሖሩ ወተ
ለውዎ ።
፭ ወበአ ውስተ ቤተ አቡሁ ኤፍራታ ወቀተሎሙ ለአ
ኀዊሁ ለደቂቀ ሮብዓም ሰብዓ ብእሲ በአሐቲ እብን ወተ
ርፈ ኢዮአታም ወልደ ሮብዓም ዘይንእስ እስመ ተኀብአ ።
፮ ወተጋብኡ ኵሎሙ ሰብአ ሰቂማ ወኵሉ ቤተ መሐ
ሎን ወሖሩ ወአንገሥዎ ሎሙ ለአቤሜሌክ ንጉሠ በኀበ
ዕፀ በላኖን እንተ ውስተ ሰቂማ ።
፯ ወዜነውዎ ለኢዮአታም ወሖረ ወቆመ ውስተ ርእሰ
ደብረ ገሪዛን ወጸርሐ ወበከየ ወይቤሎሙ ስምዑኒ ሰብአ
ሰቂማ ወይስማዕክሙ እግዚአብሔር ።
፰ ወሖሩ ዕፀው ያንግሡ ሎሙ ንጉሠ ወይቤልዎ ለዕፀ
ዘይት ንግሥ ንግሢ ለነ ።
፱ ወትቤሎሙ ዕፀ ዘይት እኅድግኑ ቅብዕየ ዘሰብሐ እግ
ዚአብሔር በላዕሌየ ወእኁለ እመሕየው ወእሑር እንግሥ
ላዕለ ዕፀው ።

ዎንና በወገኖቹም ኃጢአት በደል ሆነባቸው ።
የምድያም ሰዎች በእስራኤል ፊት ተዋረዱ ፣ ዳግመ
ኛም ራሳቸውን ከፍ ከፍ አላደረጉም ፣ በጌዴዎንም ዘመን
ምድር አርባ ዘመን ዐረፈች ። መሳ፣ ፫ ፲፩ ።
የዮአስ ልጅ ሮብዓምም(ጌዴዎን) ሂዶ በቤቱ ተቀመጠ።
ሚስቶቹ ብዙ ነበሩና ለጌዴዎን ከአብራኩ የተከፈሉ
ሰባ ልጆች ነበሩት ። መሳ፣ ፱ ፪ - ፭ ።
በሰቂማስ ያለች ዕቁባቱም ወንድ ልጅ ወለደችለት ፣
ስሙንም አቤሜሌክ አለው ። ኢያ፣ ፲፯ ፯ ።
የዮአስ ልጅ ጌዴዎን በሲናት አገር ሙቶ አባቱ ዮአስ
በተቀበረበት ወንድሙ አብያዜርም በተቀበረበት በኤፍ
ሬታ ተቀበረ ። ዘፍ፣ ፲፭ ፲፭ ፣ ፳፭ ፰ ።
ከዚህ በኋላ ጌዴዎን በሞተ ጊዜ ፣ የእስራኤል ልጆች
ተመልሰው በዓሊምን (ጣኦቱን) አመለኩት ፣ ፈጣሪያቸ
ውም ይሆን ዘንድ ከበዓሊም ጋራ ተማማሉ ።
የእስራኤል ልጆች በዙርያቸው ካሉ ከጠላቶቻቸው
ሁሉ እጅ ያዳናቸው እግዚአብሔርን አላሰቡትም ።
ለእስራኤል ባደረገው በጎ ሥራ ሁሉ ለሮብዓም ወገን
ወሮታ አላደረጉም ፣ ይኸውም ጌዴዎን ነው ።

ምዕራፍ ፱ ።

የሮብዓም ልጅ አቤሜሌክ ከናቱ ወንድሞች ዘንድ
ወደ ሰቂማ ሂዶ የናቱን ወገኖች ዘመዶቹንም ሁሉ ተናገ
ራቸው ። መሳ፣ ፰ ፴፩ ።
ምን ይሻላችኋል የሮብዓም ሰባ ልጆቹ ሁሉ ይገዙዋ
ችሁ ዘንድ ወይስ አንድ ሰው ይገዛችሁ ዘንድ ይሻላችሁ፤
እኔ የሥጋችሁ ቊራጭ ፣ ያጥንታችሁ ፍላጭ እንደሆንኩ
አስቡ ብላችሁ ለሰቂማ ሰዎች ንገሩልኝ አላቸው ።
የናቱም ወንድሞች ከሰቂማ ሰዎች ሁሉ ጋራ ይህንን
ነገር ተነጋግረው ልቡናቸውን ወደ አቤሜሌክ መለሱለት
ወንድማችን ነው አሉ ። ዘፍ፣ ፳፱ ፲፭ ። ኢያ፣ ፳፬ ፰ ።
ከጣኦቱም ቤት አውጥተው ሰባ ብር ሰጡት ፣ አቤሜ
ሌክ በዚያው በሰባውም ብር የሚያስደነግጡ ሰዎችንና
ወንበዴዎችን ገዛ ተከትለዉትም ሄዱ ።
ወደ አባቱ ወደ ኤፍሬታ ገብቶ ወንድሞቹን ሰባው
የሮብዓም ልጆች በአንድ ደንጊያ ላይ ገደላቸው ፣ የሮብ
አም ታናሽ ልጅ ኢዮአታም ግን ተሠውሮ ነበርና ተረፈ።
የመሐሎን ወገኖች ሁሉና የሰቂማ ሰዎች ሁሉ ተሰብ
ስበው ሂደው በሰቂማ ባለ በወይራ ዕንጨት አጠገብ አቤ
ሜሌክን አነገሡት ። ኢያ፣ ፳፬ ፲፩ ። መሳ፣ ፱ ፳ ።
ለኢዮአታምም ነገሩት ፣ እሱም ሂዶ በገሪዛን ተራራ
ራስ ላይ ቁሞ ጮኾ አለቀሰ ፣ የሰቂማ ሰዎች እግዚአብሔር
ይስማችሁ ስሙኝ አላቸው ። ዘዳ፣ ፲፩ ፳፱ ።
ዕንጨቶች ንጉሥን ያነግሡ ዘንድ ተሰብስበው ሂደው
ዕፀ ዘይትን ነዪ ንገሺልን አሏት ።
ዕፀ ዘይትም ሂጂ ለዕንጨቶች እነግሥ ዘንድ ለእግዚ
አብሔር መብራት ለሰው ቀባት መሆኔን ልተውን፤ አለ
ቻቸው ። መሳ፣ ፱ ፲፩ - ፲፫ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይቤልዋ ለበለስ ንዒ ንግሢ ለነ ። | ፲ | በለስንም ነዪ ንገሺልን አሏት ፤ ። |
| ወትቤሎሙ በለስ እኅድግኑ ምጥቀትየ ወፍሬየ ቡሩክ ወእሑር እንግሥ ለዕፀው ። | ፲፩ | በለስም ሂጄ ለዕንጨቶች እነግሥ ዘንድ ርዝመቴንና የከበረ ፍሬዬን ልተውን፣ አለቻቸው ። |
| ወይቤልዎ ኵሉ ዕፀው ለወይን ነዓ ንግሥ ለነ ። | ፲፪ | ዕንጨቶች ሁሉ ወይንን ና ንገሥልን፣ አሉት ። |
| ወይቤሎሙ ወይን እኅድግኑ ወይንየ ወትፍሥሕትየ ዘበኀበ እግዚአብሔር ወዘበኀበ እጓለ እመሕያው ወእሑር እንግሥ ለዕፀው ። | ፲፫ | ወይንም ሂጄ ለዕንጨቶች እነግሥ ዘንድ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለሰው ትፍሥሕት መሆኔን ልተውን፣ አላቸው ። መዝ፡ ፻፫ ፲ ። |
| ወይቤልዎ ዕፀው ለራምኖን ንዒ አንቲ ንግሢ ለነ ። | ፲፬ | ዕንጨቶች እሾታ (ዶግን) ነዪ አንቺ ንገሺልን አሏት ። |
| ወትቤሎሙ ዕፀ ራምኖን ለዕፀው እመ በአማን ታነግሡኒ በጽድቅ ላዕሌክሙ ንዑ ታጽልሉ ታሕተ ጽላሎትየ ወእመ ኢ.ወፅአት እሳት እምራምኖን ወትብልዖ ለአርዘ ሊባኖስ ። | ፲፭ | ዶግን ዕንጨቶችን በውነት በናንተ ላይ ታነግሡኝ በጥላዬ ታርፉ ዘንድ ኑ ከእሾታ (ከዶግ) እሳት ወጥታ ዋንዛ ዘግባን ብትበላው ታያላችሁ አለቻቸው ። |
| ወይእዜኒ እመ በአማን በጽድቅ ገበርክሙ ወአንገሥክምዎ ለአቤሜሌክ በከመ ገበርክሙ ምስለ ሮብዓም ወምስለ ቤቱ ወእመ በከመ ዕሤተ እዴሁ ገበርክሙ ሎቱ ። | ፲፮ | አሁንም በእውነት ከደረጋችሁት አቤሜሌክን ከነገሣችሁት ከሮብዓምና ከወገኖቹም ጋራ እንዳደረጋችሁ እንዳደረገውም መጠን ለርሱ አድርጋችሁ እንደሆነ ። |
| በከመ ተቃተለ አቡየ ለክሙ ወገደፈ ነፍሶ በቅድሜክሙ ወአድኃነክሙ እምእደ ምድያም ። | ፲፯ | አባቴ እንደ ተዋጋላችሁ በፊታችሁም ሰውነቱን ለሞት አሳልፎ እንደሰጠላችሁ ከምድያምም ሰዎች እጅ እንዳዳናችሁ ዋጋውን ብትከፍሉት የተባረካችሁ ሁኑ ። |
| ወአንትሙሰ ተንሣእክሙ ላዕለ ቤተ አቡየ ወቀተልክሙ ደቂቆ ሰብአ ብእሴ በላዕለ እሐቲ እብን ወአንገሥክምዎ ለአቤሜሌክ ወልደ ዕቅብቱ ላዕለ ሰብአ ሰቂሞን እስመ እኁክሙ ውእቱ ። | ፲፰ | እናንተ ግን በአባቴ ወገን ተነሥታችሁ ሰባውን ልጆቹን በአንዲት ደንጊያ ላይ ገደላችኋቸው፤ ወንድማችሁ ነውና የቁባቱን ልጅ አቤሜሌክን በሰቂሞን ሰዎች ላይ አነገሣችሁት ። መሳ፡ ፱ ፮፡ ፰ ፴፩ ፱ ፫ ። |
| ወእመሰ በጽድቅ ወበርትዕ ገበርክሙ ምስለ ሮብዓም ወቤቱ በዛቲ ዕለት ቡሩካነ ኩኑ አንትሙ ወተፈሥሑ በአቤሜሌክ ወውእቱኒ ይትፈሣሕ ብክሙ ። | ፲፱ | በዚች ቀን ለወገኖቹና ለሮብዓም በሚገባና በእውነትስ ወሮታን ከደረጋችሁ እናንተ የተባረካችሁ ሁኑ፤ በአቤሜሌክም ደስ ይበላችሁ፤ እሱም በናንተ ደስ ይበለው ። |
| ወእመአከሰ ትፃእ እሳት እምአቤሜሌክ ወትብልዖሙ ለሰብአ ሰቂሞን ወለቤተ መሐሎን ወትፃእ እሳት እምሰብአ ሰቂሞን ወእምቤተ መሐሎን ወትብልዖ ለአቤሜሌክ ። | ፳ | እንዲህ ባይሆን ግን ከአቤሜሌክ እሳት (ጦር) ወጥታ የመሐሎን ወገኖችና የሰቂሞንን ወገኖች ትብላቸው (ታጥፋቸው) ከመሐሎን ወገኖችና ከሰቂሞን ሰዎችም ጦር ወጥታ አቤሜሌክን ታጥፋው አላቸው ። መሳ፡ ፱ ፲፭ ። |
| ወጐየ ኢዮአታም ወሮጸ ውስተ ፍኖት ወአምሠጠ ውስተ ራራ ወነበረ ህየ እምገጸ አቤሜሌክ እኁሁ ። | ፳፩ | ኢዮአታም (ይህን ተናግሮ) ሸሽቶ ወደ ጐዳናው ሮጠ ወደ ራራም (አራራት) ሂዶ አመለጠ፤ ከወንድሙ ከአቤሜሌክ ፊት ሸሽቶ በዚያው ተቀመጠ ። ዘኍ፡ ፳፩ ፲፮ ። |
| ወተመልአከ አቤሜሌክ ለቤተ እስራኤል ሠለስተ ዓመተ ። | ፳፪ | አቤሜሌክም በእስራኤል ወገን ላይ ሦስት ዓመት ገዢ ሆነ ። |
| ወፈነወ እግዚአብሔር ጋኔነ እኩየ ማእከለ አቤሜሌክ ወማእከለ ሰብአ ሰቂሞን ወክሕድዎ ሰብአ ሰቂሞን ለቤተ አቤሜሌክ ። | ፳፫ | እግዚአብሔርም በሰቂሞን ሰዎችና በአቤሜሌክ መከከል ክፉ በለጋራን አስነሣ፤ የሰቂሞን ሰዎች የአቤሜሌክን ወገን ከዱት ። |
| ከመ ይግበእ ኃጢአት ዘሰብዓ ደቂቀ ሮብዓም ወደሞሙ ወይትፈደዩ ለአቤሜሌክ እኁሆሙ ዘቀተሎሙ ወላዕለ ሰብአ ሰቂሞን እለ አጽንዕዋ ለእዴሁ ከመ ይቅትሎሙ ለአኀዊሁ ። | ፳፬ | የሰበው የሮብዓም ልጆች የደማቸውና የኃጢአታቸው ፍዳ ወደነሱ ይመለስ ዘንድ የገደላቸው ወንድማቸው አቤሜሌክንም የፍዳውን ዋጋ ይከፍለው ዘንድ ወንድሞቹንም ይገድላቸው ዘንድ እጁን ባጸኑዋት በሰቂሞን ሰዎች ፍዳውን ያመጣባቸው ዘንድ ከዱት ። |
| ወአንበሩ ሎቱ ሰብአ ሰቂሞን ማዕገተ ውስተ አርእስተ አድባር ወየሀይዱ ኵሎ ዘየኀልፍ ፍኖተ እንተ ላዕሌሆሙ፤ ወዜነውዎ ለአቤሜሌክ ። | ፳፭ | የሰቂሞንም ሰዎች በተራራዎች ራሶች ላይ ከባቢ ጦር አኖሩለት፤ በነሳቸው ጐዳና የሚሄደውን ሰው ሁሉ ይቀሙ ነበር፤ ይህንም ለአቤሜሌክ ነገሩት ። |
| ወመጽአ ጋድ ወልደ አቤድ ወአኀዊሁ ውስተ ሰቂማ ወነብሩ ምስሌሁ ሰብአ ሰቂማ ። | ፳፮ | የአቤድ ልጅ ጋይም ከወንድሞቹ ጋራ ወደ ሰቂሞን መጣ፤ የሰቂሞንም ሰዎች ከነሱ ጋራ አንድ ሆኑ ። |
| ወወፅኡ ሐቅለ ወቀሠሙ አዕፃዳተ ወይኖሙ ወእኬዱ | ፳፯ | ወደ ምድረ በዳ መጥተው የወይናቸውን አዝመራ |

ወገብሩ በዓለ ወበኡ ቤተ አምላኮሙ ወበልዑ ወሰትዩ
ወረገምዎ ለአቤሜሌክ ።
፳፰ ወይቤ ጋድ ወልደ አቤድ መኑ ውእቱ አቤሜሌክ ፡
ወመኑ ውእቱ አቤሜሌክ ወልደ ሴኬም ከመ ንትቀነይ
ሎቱ ፡ አኮኑ ውእቱ ወልደ ሮብዓም ወዜቡል ዐቃቢሁ ወገ
ብሩ ወሰብአ ኤሞር አቡሁ ለሴኬም ወለምንት ንትቀነይ
ሎቱ ንሕነ ።
፳፱ ወመኑ እምአግብአ ለዝንቱ ሕዝብ ውስተ እዴየ ወአ
ፍልሶ ለአቤሜሌክ ወእበሎ ለአቤሜሌክ አብዝኅ ኃይለከ
ወፃእ ።
፴ ወሰምዐ ዜቡል መልአከ ሀገር ዘይቤ ጋድ ወልደ አቤ
ድ ወተምዐ መዐተ ።
፴፩ ወፈነወ መላእክተ ኀበ አቤሜሌክ ምስለ አምኃ እንዘ
ይብል ናሁ ጋድ ወልደ አቤድ ወአኃዊሁ መጽኡ ውስተ
ሰቂማ ወናሁ ይትቃተልዋ ለሀገር በእንቲአከ ።
፴፪ ወይእዜኒ ተንሥእ በሌሊት አንተ ወሕዝብ ዘምስሌከ
ወዕግት ውስተ ሐቅል ፡ ወበጽባሕ ጊዜ ይሠርቅ ፀሐይ
ጊሥ ወሩዳ ለሀገር ።
፴፫ ወመጽአ ውእቱ ወሕዝብ ዘምስሌሁ በሌሊት ወዐገ
ትዋ ለሰቂማ አርበዕቱ ሠራዊት ።
፴፬ ወሶበ ጸብሐ ወፅአ ጋድ ወልደ አቤድ ወቆመ ኀበ ኆ
ኅተ አንቀጸ ሀገር ወተንሥአ አቤሜሌክ ወሕዝብ ዘምስ
ሌሁ እምኀበ የዐግቱ ።
፴፭ ወርእየ ጋድ ወልደ አቤድ ሕዝበ ወይቤሎ ለዜቡል
ናሁ ሕዝብ ይወርድ እምርእሰ ደብር ፡ ወይቤሎ ዜቡል
ጽላሎተ አድባር ትሬኢ አንተሰ ከመ ሰብእ ።
፴፮ ወደገመ ዓዲ ጋድ ብሂሎቶ ወይቤሎ ናሁ ሕዝብ ይወ
ርድ እመንገለ ባሕር ኀበ ኅንብርተ ምድር ወአሐዱ ሠርዌ
ይመጽእ እምፍኖተ አም እንጻሮ ።
፴፯ ወይቤሎ ዜቡል አይቴ ውእቱ ይእዜ ዝክቱ አፉከ ዘ
ትቤ መኑ ውእቱ አቤሜሌክ ከመ ንትቀነይ ሎቱ አኮኑ ዝን
ቱ ውእቱ ሕዝብ ዘተዐየርከ ፃእ ይእዜ ወተቃተሎ ።
፴፰ ወወፅአ ጋድ እምቅድሜሆሙ ለሰብአ ሰቂማ ወተቃ
ተሎ ለአቤሜሌክ ።
፴፱ ወዴገኖ አቤሜሌክ ወጐየ እምቅድመ ገጹ ወወድቁ
ብዙኃን ወተቃተሉ እስከ አንቀጸ ሀገር ።
፵ ወነበረ አቤሜሌክ ውስተ አሬማ ወአውፅኦሙ ዜብል
ለጋድ ወለአኀዊሁ ወከልአሙ ነቢረ ውስተ ሰቂማ ።
፵፩ ወእምዝ በሳኒታ ወፅአ ሕዝብ ውስተ ገዳም ወዜነ
ውዎ ለአቤሜሌክ ።
፵፪ ወነሥአ ሕዝበ ወከፈሎሙ ኀበ ሠለስቱ ሠራዊት
ወዐገተ በሙ ወሶበ ይኔጽር ናሁ ሕዝብ ይወፅእ እምሀገር
ወተንሥአ ላዕሌሆሙ ወቀተሎሙ ።
፵፫ ወአቤሜሌክሰ ወሠራዊት ዘምስሌሁ ቆሙ ዲቃ ኀበ
ኆኅተ አንቀጸ ሀገር ፡ ወእልክቱሰ ክልኤቱ ሠራዊት ተዘ
ርዉ ውስተ ኵሉ ገዳም ወቀተልዎሙ ።

ለቀመው አበራዩ በዓልንም አደረጉ ፡ ወደ ጣኦታቸውም
ቤት ገብተው በሉ ጠጡ ፡ አቤሜሌክንም ረገሙት ።
የአቤድ ልጅ ጋድም አቤሜሌክ ማነው ፤ እንገዛለት
ዘንድ የሴኬም ልጅ አቤሜሌክ ምንድር ነው ፤ የሮብዓም
ልጅ አይደለምን ፤ ራስ ጠባቂው በለሚሉስ ዜቡል አይደ
ለምን ፤ የሴኬም አባት የኤሞር ወገኖችስ ምንድር ናቸው ፤
እኛ ለሱ ለምን እንገዛለታለን ፤፡ ዘፍ፡ ፴፬ ፪ - ፮ ።
አቤሜሌክን አጠፋው ዘንድ ሠራዊትህን አብዝተህ
ውጣ እለው ዘንድ ይህንን ወገን በእጄ ማን በጣለልኝ
ነበር ፤ አለ ። ፪ ሳሙ ፲፭ ፬ ።
የአገር አለቃ ዜቡልም የአቤድ ልጅ ጋድ የተናገረ
ውን ሰምቶ ቍጣን ተቈጣ ። መሳ፡ ፲ ፮ ።
እንዲህም ብሎ ከእጅ መንሻ ጋራ (በተንኰል) ወደ
አቤሜሌክ መልእክተኞችን ላከ ፡ እነሆ የአቤድ ልጅ ጋ
ድና ወንድሞቹ ወደ ሰቂማ መጡ ፡ እነሆ ስላንተም ከተ
ማይቱን ይወጉዋታል ።
አሁንም ከንተ ጋራ ካሉ ወገኖች ጋር ሁነህ ተነሥተህ
በምድረ በዳ ከበበው ፤ ጧት ፀሐይ በወጣ ጊዜ ድረስበ
ቸው ማለዳም ገስግስህ ከተማይቱን ከበባት አለው ።
እሱም መጣ ፡ ከሱ ጋራ ያሉም ወገኖች በሌሊት መጥ
ተው ሰቂማን አራት ሠራዊት ከበቧት ።
በነጋም ጊዜ የአቤድ ልጅ ጋድ ወጥቶ በከተማው
በር ቆመ ፡ አቤሜሌክም ተነሣ ፡ ከሱ ጋራ ያሉ ወገኖችም
ከከበቡበት ተነሡ ።
የአቤድ ልጅ ጋድም ወገኖችን አይቶ ዜቡልን እነሆ
ከተራራው ራስ ሰው ይወርዳል አለው ፡ ዜቡልም አንተስ
የተራራውን ጥላ እንደሰው ሁኖ ታያለህ አለው ።
ጋድም ዳግመኛ ነገረው ፡ እነሆ ሕዝብ በባሕር አንጻር
ወደ ምድር መከከል ሲወርድ የአንድም አለቃ ሠራዊት
(ወገን) ዛፍ ካለበት ጐዳና በአፍዝዝው ሲመጣ አያለሁ
አለው ።
ዜቡልም እንገዛለት ዘንድ አቤሜሌክ ምንድር ነው ፤
ያለው ያ አፍህ አሁን ወዴት አለ ፡ የተገዳደርከው (የናቅ
ከው) ወገን ይህ አይደለምን ፤ አሁንም ወጥተህ ተዋጋው ።
ጋድም ከሰቂማ ሰዎች ፊት ወጥቶ አቤሜሌክን ተዋ
ጋው ። መሳ፡ ፱ ፳፰ - ፳፱ ።
አቤሜሌክም ተከተለው ፤ ከፊቱም ሸሸ ፡ ብዙ ሰዎች
ም ድል ተነሡ እስከ ከተማውም በር ድረስ ተዋጉ ።
አቤሜሌክ በአሬማ ተቀመጠ ፡ ዜቡልም ወንድሞቹንና
ጋድን አወጣቸው ፡ በሰቂማ መኖርንም ከለከላቸው ።
ከዚህ በኋላ በማግሥቱ ሕዝቡ ወደ ምድረ በዳ ወጥ
ተው ለአቤሜሌክ ነገሩት ።
አቤሜሌክ ሕዝቡን ወስዶ ሦስት ሠራዊት አድርጎ ከፈ
ላቸው በሠራዊቱም ከበባቸው ፡ በዩም ጊዜ እነሆ ሕዝቡ
ከከተማው ሲወጡ አየ ፡ በነሳቸውም ተነሥቶ አጠፋቸው ።
ከሱ ጋር ያሉ ሠራዊትና አቤሜሌክ ግን በከተማው
በር ደጃፍ ሸምቀው ቆመው ነበር ፡ እነዚያ ሁለቱ ሠራ
ዊት ግን በምድረ በዳ ሁሉ ተበትነው አጠፋዋቸው ።

፵፭ ወአቤሜሌክሰ ይትቃተል ምስለ ሀገር ኵላ ይእተ ዕለ
ተ ወአስተጋብኣ ለሀገር ፡ ወሕዝበሰ ዘውስቴታ ቀተለ ወዘ
ርአ ውስቴታ ጼወ ።
፵፮ ወሰምዑ ኵሎሙ ሰብአ ማኅፈደ ሰቂሞን ወቦኡ ው
ስተ ጸወኑ ቤተ በዓል ።
፵፯ ወዜነውዎ ለአቤሜሌክ ከመ ተጋብኡ ኵሉ ሰብአ
ማኅፈደ ሰቂማ ።
፵፰ ወዐርገ አቤሜሌክ ውስተ ደብረ ሄርሞን ውእቱ ወሕ
ዝብ ዘምስሌሁ ወነሥአ አቤሜሌክ ጕድበ ውስተ እዴሁ
ወገመደ ፆረ ዕፀው ወነሥአ ወፆሮ ውስተ መታክፈሁ ወይ
ቤሎሙ ለሕዝብ እለ ምስሌሁ ዘከመ ርኢክሙኒ እገብር
ከማሁ ግበሩ አንትሙኒ ፍጡነ ከመ አነ ገበርኩ ።
፵፱ ወገዘሙ እሙንቱኒ ኵሎሙ ፆሮሙ ወነሥኡ ወተለ
ውዎ ለአቤሜሌክ ወአንበሩ ኀበ ጸወን ወአውዐዩ ላዕሌ
ሆሙ ጸወኖሙ በእሳት ወሞቱ ኵሎሙ ሰብአ ሰቂማ ዘማ
ኅፈድ ወየአክሉ ዐሠርተ ምእተ ብእሲ ወአንስት ።
፶ ወሖረ አቤሜሌክ ውስተ ቴበስ ወነበሩ ላዕሌሃ ወአስ
ተጋብአዋ ።
፶፩ ወቦቱ ማኅፈድ ዐቢይ ውስተ ማእከለ ሀገር ወተጸወኑ
ህየ ኵሎሙ እደዊሆሙ ወአንስቲያሆሙ ወኵሉ ዐበይተ
ሀገር ወዐፀዉ ላዕሌሆሙ ወዐርጉ ውስተ ናሕሰ ማኅፈድ ።
፶፪ ወሖረ አቤሜሌክ ኀበ ማኅፈድ ወተቃተልዎ ወቀርበ
አቤሜሌክ ኀበ ኆኅተ ማኅፈድ ከመ ያውዕዮ በእሳት ።

፶፫ ወወገረት አሐቲ ብእሲት ስባረ ማሕረጽ ውስተ ርእሱ
ለአቤሜሌክ ወቀጥቀጠቶ ርእሶ ወወፅአ ናላሁ ።
፶፬ ወጸውዖ ፍጡነ ለቍልዔሁ ዘይፀውር ንዋየ ሐቅሉ
ወይቤሎ ምላሕ መጥባሕተ ወቅትለኒ ከመ ኢይበሉኒ ብእ
ሲት ቀተለቶ ፡ ወወግአ ቍልዔሁ ወሞተ አቤሜሌክ ።
፶፭ ወርእዩ ሰብአ እስራኤል ከመ ሞተ አቤሜሌክ ወአ
ተዉ ኵሎሙ ውስተ አብያቲሆሙ ።
፶፮ ወፈደዮ እግዚአብሔር ለአቤሜሌክ እኪተ እንተ ገብ
ረ ላዕለ ቤተ አቡሁ ዘቀተለ ሰብዓ አኀዊሁ ።
፶፯ ወኵሎ እኪቶሙ ለሰብአ ሰቂማ ፈደዮሙ እግዚአብ
ሔር ላዕለ ርእሶሙ ወበጽሐሙ መርገመ ኢዮአታም ወ
ልደ ሮብዓም ።

አቤሜሌክ ግን ቀኑን ሁሉ ከአገሩ ሰዎች ጋራ ይዋጋ
ነበር ፡ አገሪቱንም እጅ አደረጋት ፡ በውስዋ ያሉ ወገኖ
ችንም አጠፋ ፡ ጨውም (ድኝ) ዘራባት ።
በሰቂሞን ግምብ ያሉ ሰዎች ሁሉ ሰምተው የጣኦቱ
ቤት ወዳለበት አምባ ገቡ ። መሳ፡ ፱ ፬ ፡ ፱ ፯ ።
ለአቤሜሌክም በሰቂማ ግምብ ያሉ ሰዎች ሁሉ እንደ
ተሰበሰቡ ነገሩት ።
አቤሜሌክም ወደ ሄርሞን ተራራ ወጣ ፡ ከሱም ጋራ
ያሉ ወገኖች ወጡ ፡ አቤሜሌክ በእጁ ገዠሞን ይዞ ዕንጨ
ቶችን ቈረጠ ፡ አንሥቶም በትከሻው ተሸከመው ከሱ ጋራ
ያሉ ወገኖችንም እኔ ሳደርግ እንዳያችሁኝ እናንተም ፈጥ
ናችሁ እንደዚያው አድርጉ አላቸው ።
እነሱም ሁሉ ሸክማቸውን ቈርጠው ተሸከሙ አቤሜ
ሌክንም ተከትለው በአምባው አኖሩ ፡ አምባቸውንም በነ
ሳቸው ላይ አቃጠሉ ፡ በግምቡ ያሉ የሰቂማ ሰዎችም ሁሉ
ሞቱ ፡ ወንዶችም ሴቶችም አንድ ሺሕ ይሆናሉ ።
አቤሜሌክም ወደ ቴበስ ሄደ ፡ (ወጣ) በዚያም ተቀመጡ
እጅም አደረጓት ።
በከተማው መካከል ታላቅ ግምብ ነበረበት ፡ ወንዶ
ችም ሴቶችም ሁሉ በአገር ያሉ መኳንንትም ሁሉ በዚያ
ተጠጉ ፡ በሩንም ዘግተው ግምብ ወዳለበት ሰገነት ወጡ ።
አቤሜሌክም ግምብ ወዳለበት ሰገነት ሄደ ፡ እነሱም
ተዋጉት ፡ አቤሜሌክም በእሳት ያቃጥለው ዘንድ ወደ ግ
ምቡ ደጃፍ ቀረበ ።
አንዲት ሴት በወፍጮ ስባሪ አቤሜሌክን ራሱን መታ
ችው ፡ ራሱን ቀጠቀጠችው ፡ ናላውም ተበጠበጠ ።
መሣሪያውን የሚሸከም ጋሻ ዣግሬውን ፈጥኖ ጠርቶ
ሴት ገደለችው እንዳይሉኝ ሰይፍህን መዝዘህ ግደለኝ አለ
ው ፡ ጋሻ ዣግሬውም በሰይፍ ወጋው አቤሜሌክም ሞተ ።
የእስራኤል ወገኖች አቤሜሌክ እንደ ሞተ አይተው
ሁሉም ወደ ቤቶቻቸው ገቡ ።
በአባቱ ወገኖች ያደረገውን ሰባ ወንድሞቹን የገደለ
ውን ፈንታ እግዚአብሔር አቤሜሌክን ክፉ ነገርን ከፈለው ።
የሰቂማንም ሰዎች ፍዳቸው ሁሉ እግዚአብሔር
በራሳቸው የሮብዓም ልጅ የኢዮአታም ርግማንም ደረ
ሰባቸው ።

## ምዕራፍ ፲ ።

፩ ወቆመ እምድኅረ አቤሜሌክ ዘያድኅኖሙ ለእስራኤል
ቶላ ወልደ ፎሓ ወልደ እኁሁ ለአቡሁ ብእሲ እምይሳኮር
ወውእቱሰ ይነብር ውስተ ሣምር ውስተ ደብረ ኤፍሬም ።
፪ ወኰነኖሙ ለእስራኤል ዕሥራ ወሠለስተ ዓመተ ወ
ሞተ ወተቀብረ ውስተ ሣምር ።
፫ ወቆመ እምድኅሬሁ ኢያእር ገለአዳዊ ወኰነኖሙ ለእ
ስራኤል ዕሥራ ወክልኤተ ዓመተ ።
፬ ወቦ ሠላሳ ወክልኤቱ ደቂቅ ወይጼዐኑ ላዕለ ሠላሳ
ወክልኤቱ አእዱግ ወቦሙ ሠላሳ ወክልኤቱ አህጉር
ወሰመዮሙ ደብራተ ኢያእር እስከ ዮም ወሀለዋ ውስተ
ገለአድ ።

## ምዕራፍ ፲ ።

ከአቤሜሌክ በኋላ እስራኤልን የሚያድናቸው የይሳ
ኮር ነገድ የሚሆን ያባቱ የወንድም ልጅ የፎሐ ልጅ ቶላ
ተነሣ ፡ እሱም በኤፍሬም ዕጣ ባለች በሣምር ይኖር ነበር ።
እስራኤልን ሃያ ሦስት ዓመት ገዛቸው ሞተ በሣ
ምርም ተቀበረ ።
ከሱም በኋላ የገለዓድ ሰው ኢያእር ተነሣ ፡ እሱ እስ
ራኤልን ሃያ ሁለት ዓመት ገዛቸው ።
፡ ሠላሳ ሁለት ልጆች ነበሩት ፡ እነሱም በሠላሳ ሁለት
አህዮች ላይ ይቀመጡ ነበር ፡ ሠላሳ ሁለት መንደሮችም
ነበሩዋቸው ፡ እስከ አሁንም ድረስ የኢያእር አውራጃዎች
ብሎ ጠራቸው ፡ እነዚህም በገለዓድ ውስጥ ያሉ ናቸው ።

፭ ወሞተ ኢያእር ወተቀብረ ውስተ ፊሞ ።

፮ ወደገሙ ደቂቀ እስራኤል ገቢረ እከይ ቅድመ እግዚአብሔር ወአምለክዎሙ ለበዓሊም ወለአስጣሮት ወለአማልክተ ሶርያ፡ ወለአማልክተ ሲዶና፡ ወለአማልክተ ሞአብ ወለአማልክተ ደቂቀ አሞን፡ ወለአማልክተ ኢሎፍሊ ወኀደግዎ ለእግዚአብሔር ወኢተቀንዩ ሎቱ ።

፯ ወተምዐ መዐተ እግዚአብሔር ላዕለ እስራኤል ወአግብኦሙ ውስተ እደ ኢሎፍሊ ወውስተ እዴሆሙ ለደቂቀ አሞን ።

፰ ወሣቀዩዎሙ ወአጠቅዎሙ ለደቂቀ እስራኤል በማዕዶተ ዮርዳኖስ በምድረ አሞሬዎን በገለአድ ።

፱ ወዐደዉ ደቂቀ አሞን ዮርዳኖስ ይትቃተልዎሙ ለይሁዳ ወለብንያም ወለቤተ ኤፍሬም ወተሣቀዩ ደቂቀ እስራኤል ጥቀ ።

፲ ወግዐሩ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር ወይቤሉ አበስነ ለከ እስመ ኀደግናከ ለአምላክነ ወአምለክናሆሙ ለበዓሊም ።

፲፩ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል አኮኑ ግብጽ ወአሞሬዎን ወደቂቀ አሞን ወሞአብ ወኢሎፍሊ ወሲዶና ወምድያም ወአማሌቅ ሣቀዩክሙ ወገዐርክሙ ኀቤየ ወአድኀንኩክሙ እምእዴሆሙ ።

፲፫ ወአንትሙሰ ኀደግሙኒ ወአምለክሙ በዕዳነ አማልክተ በበይነ ዝንቱ ኢያድኀነክሙ ።

፲፬ ሑሩ ወጽርሑ ኀበ አማልክት እለ ኀረይክሙ ለክሙ ወያድኅኑክሙ በመዋዕለ ምንዳቤክሙ ።

፲፭ ወይቤልዎ ደቂቀ እስራኤል ለእግዚአብሔር አበስነ ረስየነ ዘከመ ትፈቅድ በቅድሜከ ወባሕቱ እግዚኦ አድኅነነ በዛቲ ዕለት ።

፲፮ ወአሰሰሉ አማልክተ በዕድ እማእከሎሙ ወአምለክዎ ለእግዚአብሔር ወኢ[...]መርዎ ወአንበዘ እም[...] ሥቃይ ደቂቀ እስራኤል ።

፲፯ ወፀርኑ ደቂቀ አሞን ወኀደሩ ውስተ ገለአድ ወወፅኡ ደቂቀ እስራኤል ወኀደሩ ውስተ ደብረ መስፋ ።

፲፰ ወተባሀሉ መላእክተ ሕዝበ ገለአድ በበይናቲሆሙ መኑ ብእሲ ዘይእኅዝ ይትቃተሎሙ ለነ ለደቂቀ አሞን ወይኩን ርእሰ ለኵሉ እለ ይነብሩ ውስተ ገለአድ ።

## ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ ወዮፍታሔ ገለአዳዊ ጽኑዕ ወኀያል ወወልደ ብእሲት ዘማ ውእቱ ወወለደቶ ለዮፍታሔ እምገለአድ ።

፪ ወወለደት ሎቱ ለገለአድ ብእሲቱ አግአዚት ደቂቀ ወልህቁ ደቂቃ ለይእቲ ብእሲት ወአውፅእዎ ለዮፍታሔ ወይቤልዎ ኢትወርስ ውስተ ቤተ አቡነ እስመ ወልደ ካልእት ብእሲት አንተ ።

፫ ወሐረ ዮፍታሔ እምገጸ አኀዊሁ ወነበረ ውስተ ምድረ ጦብ ወይበውኡ ኀበ ዮፍታሔ ሰብእ ነዳያን ወየሐውሩ ምስሌሁ ።

ኢያእርም ሙቶ በፊሞ ተቀበረ ።

የእስራኤልም ልጆች ዳግመኛ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራን ሠሩ፡ በከዋክብቶችና በሰው አምሳል የተሠሩ ጣኦታትን የሲዶናና የሶርያን ጣኦታት የአሞን ልጆችና የሞዓብ ጣኦታትን የኢሎፍሊንም ጣኦታት አመለኳቸው እግዚአብሔርን ተዉት፡ አላተገዙለትም ።

እግዚአብሔርም በእስራኤል ልጆች ላይ ተቈጥቶ በአሞን ልጆች እጅና በኢሎፍላውያን ልጆች እጅ ጣላቸው።

በእስራኤል ልጆች መከራ አጸኑባቸው፡ በዮርዳኖስ ማዶ በገለዓድ በአሞሬዎን አገር አስጨነቋቸው (አጠቋቸው)፡ ዘፀ፡ ፲፭ ፯ ። መሳ፡ ፱ ፭ ።

የአሞንም ልጆች የብንያም ወገኖችንና የይሁዳ ወገኖችን የኤፍሬምንም ወገኖች ይወጉዋቸው ዘንድ ዮርዳኖስን ተሻገሩ፡ የእስራኤልም ልጆች እጅግ ተሠቃዩ ።

የእስራኤል ልጆች ፈጣሪያችን አንተን ትተን በሰው አምሳል የተሠራ ጣኦቱን አምልከናልና አንተን በደልን ብለው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ ። መሳ፡ ፫ ፱ ።

እግዚአብሔርም የእስራኤልን ልጆች አሞሬዎንና ግብጽ የሞዓብና የአሞን ልጆች ሲዶናና ኢሎፍሊ፡ አማሌቅና ምድያም መከራ አጽንተውባችሁልና ወደኔ ጮኻችሁ እኔም ከእጃቸው አዳንኳችሁ ።

እናንተ ግን እኔን ትታችሁ ልዩ የሆኑ ጣኦታትን አመለካችሁ፡ ስለዚህ ነገር አላድናችሁም ።

ለናንተ ወደ መረጣችኋቸው ጣኦታት ሂዱችሁ ጩኹ እነሱ በመከራችሁ ቀን ያድኑዋችሁ አላቸው ።

የእስራኤልም ልጆች እግዚአብሔርን በድለናል በፊትህ አንተ እንደ ወደድከ አድርገን፡ ነገር ግን አቤቱ፥ በዚች ቀን አድነን አሉት ። ፩ ሳሙ፡ ፩ ፳፫ ።

ልዩ የሆኑ ጣኦታትን ከመካከላቸው አስወግደው እግዚአብሔርን አመለኩት፡ ደስም አሰኙት፡ የእስራኤል ልጆች ከመከራው የተነሣ አእምሮአቸውን አጥተው ጮኹ።

የአሞን ልጆች ወጥተው በገለዓድ ሰፈሩ፡ የእስራኤልም ልጆች ወጥተው በመሴፋ ተራራ ሰፈሩ ።

የገለዓድ ወገኖች አለቆች እርስበርሳቸው ከአሞን ልጆች፥ ጋራ ይዋጋልን ዘንድ በገለዓድ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ አለቃ ይሆነን ዘንድ መዋጋትን የሚጀምር ሰው ማነው፧ ተባባሉ።

## ምዕራፍ ፲፩ ።

የገለዓድ ሰው ዮፍታሔን ጽኑ ኃይለኛ ነበር፡ እሱም የጋለሞታ ልጅ ነው፡ ዮፍታሔን በገለዓድ ወልዳዋለች ።

ለገለዓድ ሚስቱ ልጆች ወልዳለት ነበር፡ የዚያችም ሴት ልጆች አደጉ፡ እነሱም አንተ የልዩ ሴት ልጅ ነህና የአባታችንን ርስት አትወርስም ብለው ዮፍታሔን አወጡት (አባረሩት) ።

ዮፍታሔም ከወንድሞቹ ፊት ሂዶ በጦብ አገር ተቀመጠ፡ ለዮፍታሔ ድኾች ሰዎች እሱን ተከትለው እያገለገሉት ከሱ ጋራ ይኖሩ ነበር ። መሳ፡ ፲፩ ፭ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወእምድኅረ መዋዕል ተቃተልዎሙ ደቂቀ አሞን ለእስራኤል ። | ፬ | ከዚያም ወራት በኋላ የአሞን ልጆች እስራኤልን ወጉዋቸው ። |
| ወሖሩ ሊቃናተ ገለአድ ይንሥእዎ ለዮፍታሔ እምድረ ጦፍ ። | ፭ | የገለዓድም ሽማግሌዎች ዮፍታሔን ከጦፍ አገር ያመጡት ዘንድ ሄዱ ። መሳ፣ ፲ ፲፰ ። |
| ወይቤልዎ ለዮፍታሔ ነዓ ኩነነ መስፍነ ወንትቃተሎሙ ለደቂቀ አሞን ። | ፮ | ዮፍታሔን ና አለቃ ሁነን፤ የአሞንን ልጆች እንውጋቸው አሉት ። |
| ወይቤሎሙ ዮፍታሔ ለሊቃናተ ገለአድ አኮኑ አንትሙ ጸላእክሙኒ ወአውፃእክሙኒ እምነ ቤተ አቡየ ወአውፃእክሙኒ እምኀቤክሙ ለምንት እንከ መጻእክሙ ኀቤየ ይእዜ ሶበ ተመንደብክሙ ። | ፯ | ዮፍታሔም የገለዓድን አለቆች እናንተ ጠልታችሁኝ ከአባቴ ቤት ከናንተም ለይታችሁ ያወጣችሁኝ አይደለምን፤ አሁን ብትጨነቁ እንግዲህ ለምን ወደኔ መጣችሁ፤ አላቸው ። ዘፍ፣ ፳፮ ፳፯ ። |
| ወይቤልዎ ሊቃናተ ገለአድ ለዮፍታሔ አኮ ከመዝ መጻእነ ኀቤከ ከመ ትሑር ምስሌነ ወትትቃተል ለነ ምስለ ደቂቀ አሞን ወትኩነነ ርእሰ ለኵሉ እለ ይነብሩ ውስተ ገለአድ ። | ፰ | የገለዓድም ሽማግሎች ዮፍታሔን እንዲህ አይደለም ከኛ ጋራ ሂደህ ከአሞን ልጆች ጋራ ትዋጋልን ዘንድ በገለዓድም ለምንኖር ሰዎች ሁሉ አለቃ ትሆነን ዘንድ ወዳንተ መጣን አሉት ። |
| ወይቤሎሙ ዮፍታሔ ለሊቃናተ ገለአድ እመ ትነሥኡኒ አንትሙ ከመ እትቃተሎሙ ለደቂቀ አሞን እምከመ አግብኦሙ እግዚአብሔር ቅድሜየ አነ እከውነክሙ ርእሰ ። | ፱ | ዮፍታሔም የገለዓድን ሽማግሎች የአሞንን ልጆች እወጋቸው ዘንድ እናንተ ከወሰዳችሁኝ እግዚአብሔር በፊቴ ከጣላቸው በኋላ እኔ አለቃ እሆናችኋለሁ አላቸው ። |
| ወይቤልዎ ሊቃናተ ገለአድ ለዮፍታሔ እግዚአብሔር ስምዕነ በማእከሌነ ከመ በከመ ትቤ ከማሁ ንገብር ። | ፲ | የገለዓድም ሽማግሎች ዮፍታሔን አንተ እንዳልከ እንደዚያው እንድናደርግ እግዚአብሔር በመካከላችን ምስክር ነው አሉት ። ኤር፣ ፵፪ ፭ ። |
| ወሖረ ዮፍታሔ ምስለ ሊቃናተ ገለአድ ወሤምዎ ሕዝብ ሎሙ ርእሰ ከመ ይኩኖሙ መስፍነ ወነገረ ዮፍታሔ ኵሎ ቃሎ ቅድመ እግዚአብሔር በመሴፋ ። | ፲፩ | ዮፍታሔም ከገለዓድ ሽማግሎች ጋር ሄዶ ሕዝቡም አለቃ ይሆናቸው ዘንድ ለነሳቸው አለቃ አድርገው ሾሙት ዮፍታሔም በመሴፋ በእግዚአብሔር ፊት ስለትን ሁሉ ተሳለ ። |
| ወፈነወ ዮፍታሔ መላእክተ ኀበ ንጉሦሙ ለደቂቀ አሞን እንዘ ይብል ምንት ብከ ምስሌየ ከመ ትምጻእ ትትቃተለኒ ውስተ ብሔርየ ። | ፲፪ | ዮፍታሔም ልትወጋኝ ወደ አገሬ ትመጣ ዘንድ ከኔ ጋራ ምናለህ፤ ብሎ ወደ አሞን ልጆች ንጉሥ መልእክተኞችን ላከ ። |
| ወይቤ ንጉሦሙ ለደቂቀ አሞን ለእለ ለአከ ዮፍታሔ እስመ ነሥኡ እስራኤል ምድርየ አመ የዐርጉ እምግብጽ እምዐርኖን እስከ ኢያቦቅ ወእስከ ዮርዳኖስ ወይእዜኒ አግብእ ሊተ በሰላም፣ ወገብኡ እለ ለአከ ዮፍታሔ ኀቤሁ ለዮፍታሔ ። | ፲፫ | የአሞንም ልጆች ንጉሥ ዮፍታሔ ለላካቸው ሰዎች እስራኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ ከአርኖን እስከ ኢያቦቅ፣ እስከ ዮርዳኖስም ድረስ አገሬን ወስደውብኛልና አሁንም በፍቅር አገሬን መልስልኝ በሉት አላቸው፣ ዮፍታሔም የላካቸው ሰዎች ወደ ዮፍታሔ ተመለሱ ። |
| ወፈነወ ዳግመ ዮፍታሔ ሐዋርያተ ኀበ ንጉሦሙ ለደቂቀ አሞን ። | ፲፬ | ዮፍታሔም ዳግመኛ ወደ አሞን ልጆች ንጉሥ መልእክተኞችን ላከ ። |
| ወይቤሉ ከመዝ ይቤ ዮፍታሔ ኢነሥኡ እስራኤል ምድረ ሞአብ ወምድረ ደቂቀ አሞን አመ ዐርጉ እምግብጽ፤ | ፲፭ | ዮፍታሔ እስራኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ የአሞንን ልጆች አገርና የሞዓብን ልጆች አገር አልወሰዱም አላ አሉ ። |
| አላ ሖሩ እስራኤል ውስተ ገዳም እስከ ባሕረ ኤርትራ ወበጽሑ እስከ ቃዴስ ። | ፲፮ | እስራኤል እስከ ኤርትራ ባሕር ድረስ በምድረ በዳ ተጕዘው ወደ ቃዴስ ደረሱ እንጂ በሉት አላቸው ። |
| ወፈነወ እስራኤል ሐዋርያተ ኀበ ንጉሠ ኤዶም እንዘ ይብል አኅልፈኒ እንተ ምድርከ፣ ወአበየ ንጉሠ ኤዶም፣ ወኀበኒ ንጉሠ ሞአብ ለአከ ወአበየ ወነበረ እስራኤል ውስተ ቃዴስ ። | ፲፯ | እስራኤልም በአገርህ አሳልፈኝ ብሎ ወደ ኤዶም ንጉሥ መልእክተኞችን ላከ፣ የኤዶም ንጉሥም እምቢ አለ፣ ወደ ሞዓብ ንጉሥም ላከ፣ እምቢ አለ፣ እስራኤልም በቃዴስ ተቀመጠ ። ዘዳ፣ ፩ ፵፮ ። ዘኁ፣ ፳፩ ፬ ። |
| ወኀለፉ እንተ ገዳም ወዖዱ ምድረ ኤዶም ወምድረ ሞአብ ወበጽሑ መንገለ ጽባሒሁ ለምድረ ሞአብ ወኀደሩ ውስተ ማዕዶተ አርኖን ወኢቦኡ ውስተ ደወለ ሞአብ እስመ አርኖን ይእቲ ደወሎሙ ለሞአብ ። | ፲፰ | በምድረ በዳም አለፉ፣ የአሞንን አገርና የኤዶምን አገር ዞረው ከሞዓብ አገር ምሥራቅ አንጻር ደርሰው በአርኖን ማዶ ሰፈሩ እንጂ ወደ ሞዓብ ወሰን አልገቡም፣ አርኖንም የሞዓብ ወሰናቸው ናት ። ዘዳ፣ ፪ ፩-፰ ። |
| ወፈነወ እስራኤል ሐዋርያተ ኀበ ሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን አሞራዊ ወይቤሎ እስራኤል አኅልፈኒ እንተ ምድርከ እስከ ብሔርየ ። | ፲፱ | እስራኤልም ወደ አሞራዊ ወደ ሐሴቦን ንጉሥ ወደ ሴዎን መልእክተኞችን ልኮ እስከ አገሬ ድረስ በአገርህ አሳልፈኝ አለው ። ዘኁ፣ ፳፩ ፳፪ ። ዘዳ፣ ፪ ፳፮ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወአበየ ሴዎን አኅልፎቶሙ ለእስራኤል እንተ ደወሉ ወአስተጋብአ ሴዎን ሕዝቦ ወኀደረ ውስተ ኢያሴር ወተቃተሎሙ ለእስራኤል ። | ፳ | ሴዎንም እስራኤልን በአውራጃው ማሳለፍን እምቢ አለ ፣ ሠራዊቱንም ሰብስቦ በኢያሴር ሰፈረ ፣ እስራኤልንም ተዋጋቸው ። ዘኍ፣ ፳፩ ፳፫ ። ኢያ፣ ፫ ፲፰ ። |
| ወአግብአሙ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ለሴዎን ወለኵሉ ሕዝቡ ውስተ እዴሆሙ ለእስራኤል ወቀተልዎሙ ወተዋረስዎሙ እስራኤል ኵሎ ምድሮሙ ለአሞሬዎን እለ ይነብሩ ውስተ ይእቲ ምድር ። | ፳፩ | የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔርም ወገኖቹን ሁሉና ሴዎንን በእስራኤል እጅ ጣላቸው ፣ እስራኤልም እነሳቸውን አጥፍተው በዚያች አገር የሚኖሩ የአሞሬዎንን አገር ሁሉ ወረሱዋቸው ። ዘኍ፣ ፳፩ ፳፬ ። ዘዳ፣ ፪ ፴፫ - ፴፬ ። |
| ወተዋረሱ ኵሎ ደወሎሙ እምአርኖን እስከ ኢያቦቅ ወእምገዳም እስከ ዮርዳኖስ ። | ፳፪ | ከአርኖን እስከ ኢያቦቅ ከምድረ በዳም እስከ ዮርዳኖስ ድረስ አውራጃቸውን ሁሉ ወረሱ ። |
| ወይእዜኒ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል አሰሰሎሙ ለአሞሬዎን እምቅድመ ገጾሙ ለእስራኤል ወአንተኑ ትትዋረስ በአብሬትከ ። | ፳፫ | አሁንም የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር አሞሬዎንን ከእስራኤል ፊት አስወገዳቸው ፣ አንተ በፈንታህ ትወርሳለህን ። |
| አከኑ ከሞስ አምላክከ ዘአውረሰከ ኪያሁ ዳእሙ ትትዋረስ፡ ወኵሎ ዘአውረሰነ እግዚአብሔር አምላክነ ቅድሜነ ኪያሁ ንትዋረስ ። | ፳፬ | ፈጣሪህ ከሞስ ያወረሰህን ብቻ የምትወርስ አይደለምን፤ እኛስ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በፊታችን ያወረሰንን ሁሉ እሱን የምንወርስ አይደለምን፤። |
| ወይእዜኒ ቦኑ አንተ ትኄይስ እምባላቅ ወልደ ሰፎር ንጉሠ ሞአብ ቦኑ በኢሰ ተበአሰ ምስለ እስራኤል አው ፀብአ ተጻብአሙ ለቤተ እስራኤል በሐሴቦን ወበአዋልዲሃ ፣ ወበያዜር ወበአዋልዲሃ ፣ ወበኵሉ አህጉር ዘኀበ አርኖን ሠለስተ ምእተ ዓመተ ለምንት ኢያድኅንዎሙ በዝንቱ መዋዕል ። | ፳፭ | አሁንም ከሞዓብ ንጉሥ ከሰፎር ልጅ ከባላቅ አንተ ትበልጣለህን፤ በውኑ እሱ ከእስራኤል ጋራ ጠብን ተጣላን፤ ወይስ በሐሴቦን በጥቃቅን አገሮቿም በያዜር በጥቃቅን አገሮቿም ፣ በአርኖን ባሉ አገሮችም ሁሉ የእስራኤልን ወገኖች ሰልፍ አድርጎ ተዋጋቸውን፤ በነዚህ በሦስት መቶ ዘመኖች ለምን አላዳኑዋቸው ። |
| ወአነኒ ኢአበስኩከ ለከ ወአንተሰ ኢትገብር እኪተ ምስሌየ ከመ ትትቃተለኒ ወይፍታሕ እግዚአብሔር ዘውእቱ ይፈትሕ ዮም ማእከለ ደቂቀ እስራኤል ወማእከለ ደቂቀ አሞን ። | ፳፮ | እኔም አንተን አልበደልኩህም ፣ አንተም ትዋጋኝ ዘንድ ከኔ ጋራ ክፉ ነገርን አታድርግ ፣ አሁንም የሚፈርድ እሱ እግዚአብሔር በአሞን ልጆች መከከልና በእስራኤል ልጆች መከከል ይፍረድ አለው ። ዘፍ፣ ፲፮ ፭ ። |
| ወአበዮሙ ንጉሠ ደቂቀ አሞን ወኢሰምዐ ቃለ ዮፍታሔ ዘለአከ ሎቱ ። | ፳፯ | የአሞን ልጆች ንጉሥም እምቢ አላቸው ፣ የላከለት የዮፍታሔንም ቃል አልሰማም ። |
| ወመጽአ መንፈሰ እግዚአብሔር ላዕለ ዮፍታሔ ወዐደወ እምድረ ገለአድ ዘምናሴ እመሴፋ ዘገለአድ ውስተ ማዕዶቶሙ ለደቂቀ አሞን ። | ፳፰ | የእግዚአብሔር መንፈስ ረድኤትም በዮፍታሔ አደረበት ፣ የመሴፋ አውራጃ ከምትሆን ከምናሴ ዕጣ ከገለዓድ ወደ አሞን ልጆች ማዶ ተሻገረ ። መሳ፣ ፫ ፲ ። |
| ወበፅዐ ዮፍታሔ ብፅዐተ ለእግዚአብሔር ወይቤ ለእመ አግብኦሙ ለደቂቀ አሞን ውስተ እዴየ ዘመጽአ ወወፅአ እምኆኅተ ቤትየ ወተቀበለኒ ሶበ ገባእኩ በዳኅን እምኀበ ደቂቀ አሞን ለእግዚአብሔር እሬስዮ መሥዋዕተ ። | ፳፱ | ዮፍታሔም ለእግዚአብሔር ስለትን ተሳለ ፣ እግዚአብሔር የአሞንን ልጆች በእጄ ቢጥላቸው ከአሞን ልጆች ሰልፍ በደኅና በተመለስኩ ጊዜ ከቤቴ ደጃፍ ወጥቶ የተቀበለኝን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አደርገዋለሁ አለ ። |
| ወዐደወ ዮፍታሔ ኀበ ደቂቀ አሞን ይትቃተሎሙ ወአግብአሙ እግዚአብሔር ውስተ እዴሁ ። | ፴ | ዮፍታሔም ይዋጋቸው ዘንድ ወደ አሞን ልጆች ተሻገረ ፣ እግዚአብሔርም በእጁ ጣላቸው ። |
| ወቀተሎሙ እምአሮኤር እስከ ይበጽሕ ውስተ ኤሞኢት ዕሥራ አህጉር እስከ አቤል አዕፃደ ወይን ዐቢየ ቀትለ ጥቀ ወገረሩ ደቂቀ አሞን ቅድመ ደቂቀ እስራኤል ። | ፴፩ | ከአሮኤር ጀምሮ ኤሞኢት እስኪደርስ ድረስ አጠፋቸው ፣ እነዚህም ሃያ አህጉር ናቸው ፣ የወይን ቦታ እስከሚሆን እስከ አቤል ድረስ እጅግ ጽኑ ሰልፍ አድርጎ አጠፋቸው ፣ የአሞንም ልጆች በእስራኤል ፊት ተገዙ ። |
| ወአተወ ዮፍታሔ ውስተ መሴፋ ውስተ ቤቱ ወናሁ ወለቱ ወፅአት ወተቀበለቶ ምስለ ከበሮ ወመሰንቆ ወይእቲ ባሕቲታ ሎቱ እንተ ያፈቅራ ወአልቦ ባዕድ ውሉድ ዘእንበሌሃ ኢ ወልድ ወኢ ወለት ። | ፴፪ | ዮፍታሔም በመሴፋ ወዳለ ቤቱ በገባ ጊዜ እነሆ የሚወዳት ልጁ መሰንቆንና ከበሮን ይዛ ተቀበለችው ፣ ለሱም ልጁ ብቻ ነበረች ፣ ከሷ በቀር ሌላ ወንድም ሴትም ልጅ አልነበረውም ። መሳ፣ ፲፩ ፲፩ ። ፩ ሳሙ፣ ፲፰ ፮ ። |
| ወሶበ ርእያ ሰጠጠ አልባሲሁ ወይቤ አሌ ሊተ ወለትየ አዕቀጽክኒ ወፅዱበ ኮንክኒ ውስተ አዕይንትየ ወአንሰ ፈታሕኩ አፉየ ኀበ እግዚአብሔር በእንቲአኪ ወኢይክል ዐሊዎቶ ። | ፴፫ | ባያትም ጊዜ ልብሱን ቀደደ ፣ ወዮልኝ ልጄ፤ አሰናከልሽኝ በፊቴም ጭንቅ ሆንሽብኝ ፣ እኔ አንቺን እሠዋለሁ ብዬ በእግዚአብሔር ዘንድ ስለት ተስያለሁና የተሳልሁትን ማስቀረት አልችልም አለ ። ዘፍ፣ ፴፬ ፲፫ ። |

፴፮ ወትቤሎ አበ ለእመ በእንቲአየ ፈታሕከ አፉከ ኀበ እግዚአብሔር ረስየኒ በከመ ወፅአ እምአፉከ እስመ ገብረ ለከ እግዚአብሔር በቀለ እምፀርከ እምደቂቀ አሞን ።

፴፯ ወትቤሎ ለአቡሃ ረሲ ሊተ ዘንተ ቃለ አብሐኒ ክልኤተ አውራኀ እሑር ወእዕርግ ውስተ አድባር ወእብኪ ላዕለ ድንግልናየ ምስለ ክልአትየ ።

፴፰ ወይቤላ ሖሪ ፡ ወፈነዋ ክልኤተ አውራኀ ወሖረት ይእቲ ወክልአቲሃ ወበከየት ላዕለ ድንግልናሃ ምስለ ክልአቲሃ በውስተ አድባር ።

፴፱ ወእምድኅረ ኀልቀ ክልኤቱ አውራኅ ገብአት ኀበ አቡሃ ወገብረ ዮፍታሔ ብፅዓቲሁ ዘበፅዐ ወይእቲሰ ኢተአምር ብእሴ ፡ ወኮነት ዛቲ ሕግ ውስተ እስራኤል በበዓመት ።

፵ ወለለ መዋዕለ ዕለታ የሐውራ አዋልደ እስራኤል ይበክያሃ ለወለተ ዮፍታሔ ገለአዳዊ ረቡዐ መዋዕለ ለለዓመት ።

ምዕራፍ ፲፪ ።

፩ ወተጋብኡ ደቂቀ ኤፍሬም ወመጽኡ ውስተ ሴፌና ወይቤልዎ ለዮፍታሔ ለምንት ሖርከ ትትቃተሎሙ ለደቂቀ አሞን ወኢጸዋዕከነ ከመ ንሑር ምስሌከ ናውዒ ቤተከ በላዕሌከ በእሳት ።

፪ ወይቤሎሙ ዮፍታሔ ብእሲ ግፉዕ አነ ወሕዝብየ ወደቂቀ አሞን ሣቀዩነ ጥቀ ወጸራሕነ ለክሙ ወኢያድኀንክሙነ እምእዴሆሙ ።

፫ ወሰበ ርኢኩ ከመ አልቦ ዘያድኅን አግባእክዋ ለነፍስየ ውስተ እዴየ ወዐደውኩ ኀበ ደቂቀ አሞን ወአግብኦሙ እግዚአብሔር ቅድሜየ ፡ ወለምንት ዐረግሙ ኀቤየ ዮም ትትቃተሉኒ ።

፬ ወአስተጋብአሙ ዮፍታሔ ለኵሎሙ ሰብአ ገለአድ ወተቃተሎሙ ለሰብአ ኤፍሬም ወቀተልዎሙ ሰብአ ገለአድ ለኤፍሬም እስመ ይቤልዎሙ ድኁናነ ኤፍሬም ።

፭ ወበጽሕዎሙ በማእከለ ምናሴ ሰብአ ገለአድ በውስተ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘኤፍሬም ወእምዝ ሶበ ይቤሉ ድኁናነ ኤፍሬም ንዕዱ ይቤልዎሙ ሰብአ ገለአድ አንትሙኑ በኑ እምኤፍሬም አንትሙ ወይቤሉ ኢኮነ ።

፮ ወይቤልዎሙ በሉ መምኀፃን ፡ ወአበዩ ብሂለ መምኀፃን ፡ ወአኀዝዎሙ ወቀተልዎሙ በውስተ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ወወድቁ እምኤፍሬም ይእተ አሚረ አርባዕቱ እልፍ ወፅሥራ ምእት ።

፯ ወኮነኖሙ ለእስራኤል ዮፍታሔ ገለአዳዊ ሰብዓተ ዓመተ ፡ ወሞተ ወተቀብረ ውስተ ሀገሩ ገለአድ ።

፰ ወኮነኖሙ ለእስራኤል እምድኅሬሁ ሐሴቦን ዘእምነ ቤተ ልሔም ዘይሁዳ ።

፱ ወወለደ ሠላሳ ደቂቀ ወሠላሳ አዋልደ ወአስተዋሰበን አፍአ ፡ ወሠላሳ አንስተ ነሥአ ለደቂቁ እምአፍአ ፡ ወኮነኖሙ ለእስራኤል ሰብዓተ ዓመተ ።

አባቴ አፌን አሠዋለሁ ብለህ ወደ እግዚአብሔር ከተሳልክ እግዚአብሔርም ከጠላቶችህ ከአሞን ልጆች በቀልን አድርጎልኻልና በአንደበትህ እንደተሳልክ ሠዋኝ አለችው ።

አባቷንም ይህንን ነገር አድርግልኝ ሁለት ወር እሰናብተኝ ፡ ወደ ተራራ ወጥቼ ከጓደኞቼ ጋራ ስለድንግልናዬ ላልቅስ አለችው ። ዘፀ ፬ ፳፯ ።

ይሁን ሂጂ አላት ፡ ሁለት ወርም አሰናበታት ፡ እሷም ሂዳ ከጓደኞቿ ጋራ ከተራራ ላይ ወጥታ ስለድንግልናዋ አለቀሰች ። ዘሌዋ፡ ፲፰ ፴ ። መሳ፡ ፲፩ ፴፩ ።

ሁለት ወር ከተፈጸመ በኋላ ወደ አባቷ ተመለሰች ፡ ዮፍታሔም የተሳለው ስለቱን አደረገ (ፈጸመ) ፡ እሷ ግን ከወንድ አልደረሰችም ነበር ፡ በእስራኤልም ዘንድ በየዓመቱ ይህች ሥርዓት ሆነች ። ኤር፡ ፲ ፫ ፡ ማር ፲፩ ።

ለገለዓድ ሰው ለዮፍታሔ ልጅ በዓመት አራት ቀን ያለቅሱላት ዘንድ የእስራኤል ልጆች በዓመት በዓመት (ከሞተችበት ቀን) ያለቅሱ ነበር ። ዘፍ፡ ፳፱ ፳፫ ።

ምዕራፍ ፲፪ ።

የኤፍሬም ልጆች ወደ ሴፌና ተሰብስበው መጥተው ዮፍታሔን የአሞንን ልጆች ትዋጋቸው ዘንድ ለምን ሄድክ ከንተ ጋራ እንሄድ ዘንድ ለምን አልጠራኸንም ፤ ቤትህን በላይህ ላይ እናቃጥልብኻለን አሉት ።

ዮፍታሔም እኔ የተበደልኩ ሰው ነኝ ፡ ወገኖቼም የተበደሉ ናቸው ፡ የአሞን ልጆች ፈጽመው መከራ አጸኑብን ለናንተም ጮኽንላችሁ ከእጃቸው አላዳናችሁንም ።

የሚያድንም እንደሌለ በየሁ ጊዜ ሰውነቴን በእጄ አሳልፌ ለሞት ሰጥቼ ወደ አሞን ልጆች ተሻገርኩ ፡ እግዚአብሔርም በፊቴ ጣላቸው ፤ አሁን ትዋጉኝ ዘንድ ለምን ወደኔ መጣችሁ ፤ አላቸው ። ፩ ሳሙ፡ ፲፱ ፭ ።

ዮፍታሔም የገለዓድን ሰዎች ሰብስቦ ተዋጋቸው ፡ የገለዓድ ሰዎች የኤፍሬምን ሰዎች አጠፉዋቸው ፡ ከኤፍሬም ወገኖች የዳኑ ብለዋቸዋልና ።

የኤፍሬም ዕጣ በምትሆን በዮርዳኖስ ማዶ የገለዓድ ሰዎች በምናሴ ዕጣ በምትሆን መካከል ደረሱባቸው ፡ ከዚህ በኋላ ከኤፍሬም ወገኖች የዳኑት እንሻገር ባሉ ጊዜ የገለዓድ ሰዎች በውኑ እናንተ ከኤፍሬም ወገኖች አይደላችሁምን ፤ ብለዋቸዋልና አይደለንም አሉ ።

እግዚአብሔር መማጠኛ ይሁንልን በሉ አሏቸው ፡ እግዚአብሔር መማጠኛ ይሁነን ማለትን እምቢ አሉ ፡ ይዘውም በዮርዳኖስ ማዶ አጠፉዋቸው ፡ የዚያን ጊዜ ከኤፍሬም ወገኖች አራት እልፍ ከሁለት ሺሕ ሰዎች ሞቱ ።

የገለዓዱ ዮፍታሔ እስራኤልን ሰባት ዓመት ገዛቸው (ከዚህ በኋላ) ሙቶ በአገሩ በገለዓድ ተቀበረ ።

ከሱ በኋላ የይሁዳ ዕጣ ከምትሆን ከቤተ ልሔም የተወለደ ሐሴቦን እስራኤልን ገዛቸው ።

(እሱም) ሠላሳ ወንዶች ልጆች ፡ ሠላሳ ሴቶች ልጆችን ወለደ ሠላሳውን ሴቶች ልጆቹን ወደ ውጪ ዳረ ፡ ለሠላሳው ወንዶች ልጆቹም ከውጭ አገር ሠላሳ ሴቶችን አመ

፲ ወሞተ ሐሴቦን ወተቀብረ ውስተ ቤተ ልሔም ።
፲፩ ወኮነኖሙ እምድኅሬሁ ለእስራኤል ኤሎም ዘብሎናዊ ዓሠርተ ዓመተ ።
፲፪ ወሞተ ኤሎም ዘብሎናዊ በሴሎም ወቀበርዎ ውስተ ምድረ ዘብሎን ።
፲፫ ወኮነኖሙ ለእስራኤል እምድኅሬሁ ሉበን ወልደ ኤሎም ኤፍራታዊ ።
፲፬ ወተወልዱ ሉቱ አርባዓ ደቂቅ ወሠላሳ ደቂቀ ደቂቁ ወይጼዕኑ ላዕለ ሰብዓ አእዱግ፡ ወኮነኖሙ ለእስራኤል ሰመንተ ዓመተ ።
፲፭ ወሞተ ሉበን ወልደ ኤሎም ኤፍራታዊ ወቀበርዎ ውስተ ኤፍራታ ውስተ ኤፍሬም ውስተ ደብረ ረንቅ ።

ምዕራፍ ፲፫ ።

፩ ወደገሙ ደቂቀ እስራኤል ገቢረ እኩይ ቅድመ እግዚአብሔር ወአግብኦሙ ውስተ እደ ኢሎፍሊ አርባዓ ዓመተ ።
፪ ወሀለወ ብእሲ ዘእምነ ሦራሕ ዘእምነገደ ዳን ወስሙ ማኑሄ ወብእሲቱሰ መካን ይእቲ ወኢትወልድ ።
፫ ወአስተርአያ መልአከ እግዚአብሔር ለብእሲቱ ወይቤላ ናሁ መካን አንቲ ወኢወለድኪ ወትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ።
፬ ወይእዜኒ ተዓቀቢ ወኢትስተዪ ወይነ ወሜሰ ወኢትብልዒ ኵሎ ዘርኩሰ፡ እስመ ናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ።
፭ ወኢይለክፎ ርእሶ ሐፂን እስመ ቅዱስ ውእቱ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር ውእቱ ሕፃን እምከርሠ እሙ ወውእቱ ይእኅዝ ያድኅኖሙ ለእስራኤል እምእደ ኢሎፍሊ ።
፮ ወሖረት ይእቲ ብእሲት ወነገረቶ ለምታ ወትቤሎ ብእሲ እግዚአብሔር መጽአ ኀቤየ ወርእየቱ ከመ ርእየተ መልአከ እግዚአብሔር ወግሩም ውእቱ ጥቀ ወተስእልክዎ እምአይቴ ውእቱ፡ ወኢያይድዓኒ ስሞ ።
፯ ወይቤለኒ ናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ወይእዜኒ ኢትስተዪ ወይነ ወሜሰ ወኢትብልዒ ኵሎ ዘርኩሰ እስመ ናዝራዊ ውእቱ ሕፃን ለእግዚአብሔር እምከርሠ እሙ እስከ አመ ይመውት ።
፰ ወሰአለ ማኑሄ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ እግዚኦ ብእሴ እግዚአብሔር ዘፈነውከ ኀቤነ ለይምጻእ ኀቤነ ወያለብወነ ምንተ ንገብር ለውእቱ ሕፃን ዘይትወለድ ።
፱ ወሰምዐ እግዚአብሔር ቃሎ ለማኑሄ ወመጽአ መልአከ እግዚአብሔር ኀበ ብእሲቱ ዓዲ ዳግመ እንዘ ትነብር ውስተ ገዳም ወኢሀለወ ማኑሄ ምታ ምስሌሃ ።
፲ ወሮጸት ብእሲቱ ወአፍጠነት ወነገረቶ ለምታ ወትቤሎ ናሁ አስተርአየኒ ዝኩቱ ብእሲ ዘመጽአ ኀቤየ ቀዲሙ ።

ጣ፡ እስራኤልንም ሰባት ዓመት ገዛቸው ።
ሐሴቦንም ሙቶ በቤተ ልሔም ተቀበረ ።
ከሱም በኋላ ከዛብሎን ወገን የተወለደ ኤሎም እስራኤልን ዓሥር ዓመት ገዛቸው ።
ከዛብሎን ወገን የተወለደ ኤሎምም በሴሎም ሙቶ በዛብሎን ዕጣ (ጕድር) ቀበሩት ። ዘፍ፡ ፵፩ ፵፫ ።
ከሱም በኋላ የኤፍሬታው ሰው የኤሎም ልጅ ሉበን እስራኤልን ገዛቸው ። ፪ ሳሙ፡ ፳፫ ፴ ።
ለሱም አርባ ልጆች ተወለዱለት፡ የልጅ ልጆቹ ሠላሳ ነበሩ፡ በሰባ አህዮች ይቀመጡ ነበር፡ እስራኤልንም ስምንት ዓመት ገዛቸው ። ኢዮብ ፲፰ ፲፱ ። ኢሳ፡ ፲፬ ፳፪ ።
የኤፍራታው ሰው (የኤሎም ልጅ) ሉበንም ሙቶ የኤፍሬም ዕጣ በምትሆን በኤፍራታ ግምብ (ረንቅ) በለበት ተራራ ቀበሩት ። መሳ፡ ፫ ፲፫ - ፳፯ ።

ምዕራፍ ፲፫ ።

የእስራኤል ልጆች ዳግመኛ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራን ሠሩ፡ እግዚአብሔርም አርባ ዘመን በኢሎፍላውያን እጅ ጣላቸው ። መሳ፡ ፬ ፩ ፲፭ ፳፡ ፫ ፴፩ ።
ከዳን ወገን ከሚሆን ከሦራሕ የተወለደ ስሙ ማኑሄ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፡ ሚስቱ ግን መካን ነበረች፡ ልጅም አልወለደችም ነበር ። ኢያ፡ ፲፭ ፴፫ ።
ከእግዚአብሔር የተላከው መልአክ ለሚስቱ ታያት፡ እነሆ አንቺ መኻን ነሽ ልጅንም አልወለድሽም፡ ትፀንሻለሽ፡ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ አላት ።
አሁንም ተጠንቀቂ የማር ጠጅና የወይን ጠጅ አትጠጪ፡ ለመሥዋዕት የማይሆንም ሁሉ አትብዪ፡ እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽና ።
ያም ሕፃን ከናቱ ማኅፀን ከተወለደ ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ገንዘቡ ነውና፡ በራሱ ላይ ምላጭ አይድረስበት፡ እሱም እስራኤልን ከኢሎፍላውያን እጅ ሊያድናቸው ይጀምራል አላት ። ዘኍ፡ ፮ ፭ ። መሳ፡ ፲፮ ፲፯ ።
ያችም ሴት ሂዳ ለባሏ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደኔ መጣ፡ መልኩም እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነው፡ እጅግም የሚያስፈራ ነው፡ ከየትም እንደመጣ ጠየቅሁት፡ ስሙንም አልነገረኝም ብላ ነገረችው ።
እነሆ ትፀንሻለሽ፡ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ፡ አሁንም የማርና የወይን ጠጅ አትጠጪ፡ ያም ልጅ ከናቱ ማኅፀን ከተወለደ ጀምሮ እስኪሞት ድረስ ለእግዚአብሔር የተለየ አገልጋዩ (ናዝራዊ) ነውና፡ ለመሥዋዕት የማይሆነውን ሁሉ አትብዪ አለኝ ብላ ነገረችው ።
ማኑሄም አቤቱ! የላክኸው የእግዚአብሔር ሰው (ነቢይ) ወደኛ ይምጣ፡ ለዚያ ለሚወለደው ልጅ ምን እናደርግ ዘንድ ልብ ያስደርገን ብሎ ወደ እግዚአብሔር ለመነ ።
እግዚአብሔርም የማኑሄን ልመና ሰምቶ፡ እግዚአብሔር የላከው መልአክ በምድረ በዳ ሳለች አሁን ዳግመኛ ወደ ሚስቱ መጣ፡ ባሏ ማኑሄ ግን ከሷ ጋር አልነበረም ።
ሚስቱም ሩጣ ሂዳ ቀድሞ ወደኔ የመጣ ያ ሰው እነሆ ታየኝ ብላ ፈጥና ለባሏ ነገረችው ።

፲፩ ወተንሥአ ማኑሄ ወተለዋ ለብእሲቱ ወሖረ ኀበ ውእ
ቱ ብእሲ ወይቤሎ አንተኑ ውእቱ ዝክቱ ብእሲ ዘተናገርከ
ምስለ ብእሲትየ ወይቤሎ ውእቱ መልአክ አነ ውእቱ።
፲፪ ወይቤሎ ማኑሄ ይእዜ ሶበ በጽሐ ቃልከ ምንት ውእ
ቱ ነገሩ ለውእቱ ሕፃን ወግብሩ።
፲፫ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር ለማኑሄ እምኵሉ ዘእ
ቤላ ለብእሲትከ ተዓቀቡ።
፲፬ እምኵሉ ዘይወፅእ እምወይን ኢትብላዕ ወወይነ
ወሜሰ ኢትስተይ ወኵሎ ርኩሰ ኢትብላዕ ወኵሎ ዘአዘ
ዝክዋ ተዓቀቡ።
፲፭ ወይቤሎ ማኑሄ ለመልአከ እግዚአብሔር ናጌብረከ
ወንገብር ለከ ማሕስአ ጠሊ ቅድሜከ።

፲፮ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር ለማኑሄ እመሰ አገበ
ርከኒ ኢይበልዕ እንከ እክለከ ወእመሰ ለእግዚአብሔር ገበ
ርከ መሥዋዕተ ግበር ሎቱ።
፲፯ ወይቤሎ ማኑሄ ለመልአከ እግዚአብሔር መኑ ስምከ
ከመ አመ በጽሐ ቃልከ ንሰብሕከ።
፲፰ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር ለምንት ዝንቱ ዘት
ሴአል ስምየ መድምም ውእቱ።
፲፱ ወነሥአ ማኑሄ ማሕስአ ጠሊ መሥዋዕተ ወአዕረገ
ዲበ ኰኵሕ ለእግዚአብሔር ዘይገብር መድምመ።

፳ ወርእይዎ ማኑሄ ወብእሲቱ ሶበ ዐርገ ነድ እማእከለ
ምሥዋዕ ውስተ ሰማይ።
፳፩ ወዐርገ መልአከ እግዚአብሔር በነደ ምሥዋዕ ውስተ
ሰማይ ወማኑሄ ወብእሲቱ ርእይዎ ወወድቁ በገጾሙ ው
ስተ ምድር።
፳፪ ወኢደገመ እንከ መልአከ እግዚአብሔር አስተርእዮ
ቶሙ ለማኑሄ ወለብእሲቱ፡ ወይእተ ጊዜ አእመረ ማኑሄ
ከመ መልአከ እግዚአብሔር ውእቱ።
፳፫ ወይቤላ ማኑሄ ለብእሲቱ ሞተ ንመውት እስመ ርኢ
ናሁ ለመልአከ እግዚአብሔር።
፳፬ ወትቤሎ ብእሲቱ ሶበሰ ፈቀደ ይቅትለነ እግዚአብ
ሔር እምኢተመጠወ እምእዴነ መሥዋዕተነ ወቍርባነ
ወእምኢያለበወነ ኵሎ ዘንተ ወበከመሰ መዋዕሊሁ ሶም
ኢያስምዐነ ዘንተ።

፳፭ ወወለደት ወልደ ይእቲ ብእሲት ወሰመየቶ ስሞ ሶም
ሶን፡ ወባረከ እግዚአብሔር ወልህቀ ውእቱ ሕፃን።
፳፮ ወአኀዘ መንፈሰ እግዚአብሔር ይሖር ምስሌሁ ውስ
ተ ትዕይንተ ዳን ማእከለ ሦራኅ ወማእከለ እስታሔል።

ምዕራፍ ፲፬።

፩ ወወረደ ሶምሶን ውስተ ቴምናታ ወርእየ ብእሲተ በቴ
ምናታ እምአዋልደ ኢሎፍሊ ወአደመቶ ቅድሜሁ።

፪ ወዐርገ ወነገሮሙ ለአቡሁ ወለእሙ ወይቤሎሙ ርኢ

ማኑሄም ሚስቱን ተከትሎ ወደዚያ ሰው ሄደ፡ ከሚ
ስቴ ጋራ የተነጋገርህ ያ ሰው አንተ ነህን፤ አለው፡ ያም
መልአክ አዎን እኔ ነኝ አለው።
ማኑሄም አሁን ቃልህ በደረሰ ጊዜ የዚያ ልጅ ነገሩ
ምንድር ነው፤ ሥራውስ ምንድር ነው፤ አለው።
እግዚአብሔር የላከው መልአክም ማኑሄን ለሚስትህ
ከነገርኋት ሁሉ ተጠበቁ። መሳ፡ ፲፫ ፬።
ከወይን የሚገኘውን ሁሉ አትብላ፡ የወይን ጠጅንና
የማር ጠጅንም አትጠጣ፡ መሥዋዕት የማይሆነውንም
ሁሉ አትብላ፡ ያዘዝኋትንም ሁሉ ጠብቁ አለው።
ማኑሄም ከእግዚአብሔር የተላከውን መልአክ ግድ
እንልኽለን፡ በፊትህ አንድ የፍየል ጠቦት እንረድልህ፤
አለው። ዘፍ፡ ፲፰ ፭። መሳ፡ ፮ ፲፰።
ከእግዚአብሔር የተላከው መልአክም ማኑሄን ግድም
ብትለኝ እንጀራህን አልበላም፡ ለእግዚአብሔር
መሥዋዕት ታደርግ እንደሆነ ግን ለሱ አድርግለት አለው።
ማኑሄም ከእግዚአብሔር የተላከውን መልአክ ቃልህ
በደረሰ ጊዜ እንድናመሰግንህ ስምህ ማነው፤ አለው።
ከእግዚአብሔር የተላከው መልአክም ስሜ ድንቅ
ነውና ስሜን የምትጠይቅ ለምንድር ነው፤ አለው።
ማኑሄም አንድ የፍየል ጠቦት እምጥቶ ድንቅ ተአም
ራትን ለሚያደርግ ለእግዚአብሔር በአለት ላይ መሥዋ
ዕትን ሠዋ። መሳ፡ ፮ ፲፱፡ ፲፫ ፲፯ - ፲፰።
እሳቱ ከመሠውያው መከከል ወደ ሰማይ በወጣ ጊዜ
ሚስቱና ማኑሄ አዩት።
ከእግዚአብሔር የተላከው መልአክም በመሠውያው
ላይ ያለውን እሳት ተረግጦ ወደ ሰማይ ዓረገ፡ ሚስቱና
ማኑሄም አይተዉት በምድር ላይ በግንባራቸው ተደፉ።
የእግዚአብሔር መልአክ ለሚስቱና ለማኑሄ እንግዲህ
ዳግመኛ አልታያቸውም በዚያን ጊዜም ማኑሄ ከእግዚአብ
ሔር የተላከ መልአክ እንደሆነ ዓወቀ። መሳ፡ ፮ ፳፪።
ማኑሄም ሚስቱን የእግዚአብሔርን መልአክ አይ
ተናልና እንሞታለን አላት። ዘፀ፡ ፴፫ ፳። ዘዳ፡ ፭ ፳፮።
ሚስቱም እግዚአብሔር ይገድለን ዘንድ ቢወድ የሠ
ዋነውን መሥዋዕታችን ያቀረብነውን ቍርባናችንን ከእጃ
ችን ባልተቀበለን ነበር፡ ይህንም ሁሉ ነገር ልብ ባላስደረ
ገንም ነበር፡ የምንሞትበትንስ ቀን ቢደርስ ይህን ባላሰ
ማን ነበር አለችው። መሳ፡ ፲፫ ፲፯ - ፲፱።
ያችም ሴት ወንድ ልጅ ወለደች፡ ስሙንም ሶምሶን
አለችው፡ እግዚአብሔርም ባረከው ያም ልጅ አደገ።
የእግዚአብሔርም መንፈስ ረድኤት በእስታሔል መከ
ከልና በሦራህ መከከል ባለ በዳን ሰፈር ከሱ ጋራ ይኖር
ጀመረ። ዘፍ፡ ፵፩ ፳። ኢያ፡ ፲፭ ፴፫።

ምዕራፍ ፲፬።

ሶምሶን ወደ ቴምናታ ወረደ፡ በቴምናታም ከኢሎፍ
ላውያን ልጆች ወገን የምትሆን አንዲት ሴት አየ፡ በፊ
ቱም ደስ አለችው። ዘፍ፡ ፴፰ ፲፪። ኢያ፡ ፲፱ ፵፫።
ወጥቶም ለናቱና ላባቱ በቴምናታ ከኢሎፍላውያን

ኵ ብእሲተ በቴምናታ እምአዋልደ ኢሎፍሊ ወይእዜኒ ንሥእዋ ሊተ ብእሲተ ።

ልጆች ወገን የምትሆን አንዲት ሴት አየሁ፤ አሁንም እሷን አጋቡኝ ብሎ ነገራቸው ። ዘፍ፡ ፳፩ ፳፩ ።

፫ ወይቤልዎ አቡሁ ወእሙ ቦኑ አልቦ እምአዋልደ አኃዊከ ወበውስተ ኵሉ ሕዝብየ ብእሲት ከመ ትሑር አንተ ወትንሣእ ብእሲተ እምአዋልደ ኢሎፍሊ ቈላፋን ።

እናትና አባቱም ሂደህ ቈላፋን (ያልተገረዙት) ከሆኑ ከኢሎፍላውያን ልጆች ወገን የምትሆን ሴትን ታገባ ዘንድ በውኑ ከወንድሞችህ ልጆች በወገኖቼስ ሁሉ ዘንድ ሴት የለችምን፤ አሉት ።

፬ ወይቤሎ ሶምሶን ለአቡሁ ኪያሃ ዳእሙ ንሥኡ ሊተ እስመ አደመተኒ ውስተ አዕይንትየ ።

ሶምሶንም አባቱን በሬቴ ደስ አሰኝታኛለችና እሷን ብቻ አጋቡኝ አለው ። ዘፍ፡ ፳፬ ፫ ። ፩ ሳሙ፡ ፲፯ ፳፮ ።

፭ ወኢያእመሩ አቡሁ ወእሙ ከመ እምኀበ እግዚአብሔር ውእቱ እስመ በቀለ ይፈቅድ ውእቱ እምኢሎፍሊ ወበእማንቱ መዋዕል ኢሎፍሊ ይቀንይዎሙ ለእስራኤል ።

እሱ ከኢሎፍላውያን በቀልን ይመልስ ይወዳልና፤ እናቱ አባቱ ግን ከእግዚአብሔር እንደሆነ አላወቁም፤ በዚያም ወራት ኢሎፍላውያን እስራኤልን ይገዙዋቸው ነበር ። ኢያ፡ ፲፩ ፳ ። መሳ፡ ፲፫ ፩ ።

፮ ወወረዱ ሶምሶን ወአቡሁ ወእሙ ውስተ ቴምናታ ወተግኅሠ ውስተ ዐፀደ ወይን ዘቴምናታ ወናሁ አንበሳ ተቀበሎ እንዘ ይጥሕር ።

እናት አባቱና ሶምሶንም ወደ ቴምናታ ወረዱ፤ በቴምናታም ወዳለ ወደ ወይን በታ ገባ፤ እነሆም አንበሳ እያገሳ ተቀበለው ። መሳ፡ ፲፫ ፲፬ ። ሕዝ፡ ፲፱ ፪ ።

፯ ወመጽአ መንፈሰ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ወነጽሖ ከመ ዘይነጽሕ ማሕስአ ጠሊ ወከመ ወኢምንት ኮነ ውስተ እዴሁ ወኢያይድዖ ለአቡሁ ወለእሙ ዘገብረ ።

የእግዚአብሔርም መንፈስ ረድኤት አደረበት የፍየል ጠቦትን እንሥተው እንዲጥሉ እንሥቶ ጣለው፤ በእጁም እንደ ኢምንት ሆነ ያደረገውንም ላባቱና ለናቱ አልተናገረም ። መሳ፡ ፲፩ ፲፱፤ ፫ ፲፤ ፲፫ ፲፬ ።

፰ ወዐርጉ ወተናገሩ በእንተ ብእሲቱ ወአደመቶ ቅድሜሁ ለሶምሶን ።

ወደ ቤት ገብተው የሚስቱን ነገር ተናገሩ፤ ሶምሶንም በሬቱ ደስ አሰኘችው ።

፱ ወተመይጠ እምድኅረ መዋዕል ከመ ይንሥኣ ወተግኅሠ ከመ ይርአዮ ለገዝከቱ በድነ አንበሳ ወናሁ ንህብ ውስተ አፉሁ ለውእቱ አንበሳ ኅደረ ወበ መዓር ።

ከዚያም ቀን በኋላ ያችን ሴት ያገባት ዘንድ ተመለሰ የዚያን የአንበሳውን ሬሳ ያይ ዘንድ ከመንገዱ ፈቀቅ አለ፤ እነሆም በዚያው በአንበሳው አፍ ንብ ማር ሠርቶ አገኘው።

፲ ወነሥአ ወበልዐ ወሖረ ወእንዘ የሐውር ይበልዕ ወበጽሐ ኀበ አቡሁ ወእሙ ወወሀቦሙ ወበልዑ ወኢይድዖሙ ከመ እምአፈ አንበሳ አውፅአ ለውእቱ መዓር ።

ከዚያም ወስዶ በልቶ ሄደ፤ ሲሄድም ይበላ ነበር፤ ወደ እናቱና ወደ አባቱም ደርሶ ማሩን ሰጣቸው እነሳቸውም በሉ፤ ነገር ግን ያንን ማር ከአንበሳው አፍ እንዳወጣው አልነገራቸውም ።

፲፩ ወወረደ አቡሁ ኀበ ይእቲ ብእሲት ወነበረ ህየ ሶምሶን ሰቡዐ መዋዕለ እስመ ከማሁ ይነብሩ ወራዙት ።

አባቱም ወደዚያች ሴት ወረደ፤ ጐልማሶች እንደዚሁ ይቀመጡ (ያደርጉ) ነበርና፤ ሶምሶንም ሰባት ቀን በዚያ ተቀመጠ ።

፲፪ ወእምዝ ሶበ ፈርህዎ ሤሙ ላዕሌሁ ክልኤተ ሠላሳ እደ ወ ወነበሩ ምስሌሁ ።

ከዚህ በኋላ በፈሩት ጊዜ የሚጠብቁት ሠላሳ ሰዎችን በሱ ላይ ሾሙበት ከሱም ጋራ ተቀመጡ ።

፲፫ ወይቤሎሙ ሶምሶን እሜስል ለክሙ አምሳለ ወእመ አይዳዕክሙኒ አምሳልየ በእላንቱ ሰቡዕ መዋዕል ዘበዓል ወረከብክሙ እሁበክሙ ሠላሳ ሰንዱናተ ወሠላሳ አልባሰ ።

ምሳሌን (እንቆቅልሽ) እመስልላችኋለሁ በዓል በማደርግባቸው በነዚህ በሰባቱ ቀኖች ምሳሌዬን ብትነግሩኝ፤ ምሳሌዬንም ብታገኙዋት ሠላሳ ቀሚስ፤ ሠላሳ መጐናጸፊያ እሰጣችኋለሁ አላቸው ። ዘፍ፡ ፳፱ ፳፯ ።

፲፬ ወእመሰ ስእንክሙ አይድዖትየ ትሁቡኒ አንትሙ ሊተ ሠላሳ ሰንዱናተ ወሠላሳ አልባሰ ወይቤልዎ መስል አምሳሊከ ወንስማዕ ።

ምሳሌዬን መንገር ባትችሉ ግን እናንተ ለኔ ሠላሳ ቀሚስ፤ ሠላሳ መጐናጸፊያ ትሰጡኛላችሁ አላቸው፤ እነሱም ምሳሌህን መስል እንሰማህ አሉት ።

፲፭ ወይቤሎሙ እምኀ በላዒ ወፅአ መብልዕ፤ ወእምኀ ጽኑዕ ወፅአ ጥዑም፤ ወስእኑ አይድዖቶ አምሳሊሁ እስከ ሠሉስ መዋዕል ።

እርሱም ከሚበላ መብል ወጣ፤ ከብርቱም የሚጣፍጥ ተገኘ አላቸው፤ እስከ ሦስት ቀን ድረስ ምሳሌውን መንገር ተሳናቸው ።

፲፮ ወእምዝ አመ ራብዕት ዕለት ይቤልዋ ለብእሲቱ አስፍጢዮ ለምትኪ ወይንግርኪ አምሳሊሁ ከመ ኢናውዒ ክሙ በእሳት ለኪ ወለቤተ አቡኪ አው ከመ ታንድዩነ ጸዋዕክሙነ ።

ከዚህ በኋላ በአራተኛይቱ ቀን የሶምሶንን ሚስት ባልሽ ሶምሶንን አባብሊልን ያለዚያም ያባትሽን ወገኖችና አንችን በእሳት እንዳናቃጥላችሁ ምሳሌውን (እንቆቅልሹን) ይንገርሽ፤ ወይስ ታደኸዩን ዘንድ ጠራችሁንን፤ አሏት ።

፲፯ ወበከየት ላዕሌሁ ብእሲቱ ለሶምሶን ወትቤሎ ጸላእከኒ ወኢታፈቅረኒ እስመ አምሳሊከ ዘመሰልከ ለደቂቀ ሕዝብየ

የሶምሶንም ሚስት አለቀሰችበት፤ ለወገኖቼ ልጆች መስለህ የነገርካቸውን ምሳሌ ለኔ አልነገርከኝም፥ና ጠልተ

ኢነገርክኒ ሊተ ወይቤላ ሶምሶን ናሁ ለአቡየ ወለእምየ ኢነገርክዎሙ ለኪኑ እነግረኪ ።

፲፰ ወበከየት ላዕሌሁ ሰቡዐ መዋዕለ ዘበዓል ፣ ወእምዝ አመ ሳብዕት ዕለት ነገራ ሰበ አሥርሐቶ ወአይድዐቶሙ ለደቂቀ ሕዝብ ።

፲፱ ወይቤልዎ እሙንቱ እደው አመ ሳብዕት ዕለት እንበለ ይዕርብ ፀሐይ ምንት ይጥዕም እመዓር ወምንት ይጸንዕ እምአንበሳ ፣ ወይቤሎሙ ሶምሶን ሰበ ኢያስራሕክምዋ ለእጐልትየ እምኢረከብክምዋ ለአምሳልየ ።

፳ ወሠረጸ መንፈሰ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ወወረደ ውስተ አስቀሎና ወቀተለ ሠላሳ ብእሴ ወሰለበሙ አልባሲሆሙ ወወሀበሙ ለእለ አይድዕዎ አምሳሊሁ ፣ ወተምዐ መዐተ ሶምሶን ወአተወ ቤተ አቡሁ ።

፳፩ ወነበረት ብእሲተ ሶምሶን ምስለ መጋቤ መርዓሁ ከልኡ ።

ምዕራፍ ፲፭ ።

፩ ወእምድኅረ መዋዕል አመ ማእረረ ሥርይ ሐወጻ ስምሰን ለብእሲቱ ወአምጽአ ላቲ ማሕስአ ጠሊ ወይቤ እበእ ኀበ ብእሲትየ ውስተ ጽርሕ ፣ ወከልኦ አቡሃ በዊአ ኀቤሃ ።

፪ ወይቤሎ አቡሃ እስመ ትቤ ጸላእክዋ ወወሀብክዋ ለካልእከ ፣ ወበሕቱ ነያ እኅታ እንተ ትንእሳ ወትሤንያ ትኩንከ ህየንቴሃ ።

፫ ወይቤ ሶምሶን ንጹሕ አነ ምዕረ እምኢሎፍሊ ፣ እስመ አነ እገብር እኪተ ላዕሌክሙ ።

፬ ወሖረ ሶምሶን ወአኀዘ ሠለስተ ምእተ ቈናጽለ ወነሥአ መኑተወ ወአሰረ ውስተ አዝናቢሆሙ ወወደየ አሐደ ማኅቶተ ማእከለ ክልኤቱ አዝናቢሆሙ ።

፭ ወአኅተወ እሳተ ውስተ ውእቱ መኅትው ወፈነዎሙ ውስተ ክላስስት ዘኢሎፍሊ ፣ ወአውዐዩ ሰዊተ ወክምረ ዘተዐፅደ ዘይቀውም ወዘውጡሕ ወአዕፃዳተ ወይን ወዘይት ።

፮ ወይቤሉ ኢሎፍሊ ፣ መኑ ገብረ ዘንተ ፣ ወይቤልዎሙ ሶምሶን ሐሙሁ ለቴምናታዊ እስመ ሄድዎ ብእሲቶ ወወሀብዋ ለካልኡ ፣ ወዐርጉ ኢሎፍሊ ወአውዐዩ ቤተ አቡሃ ወኪያሃኒ በእሳት ።

፯ ወይቤሎሙ ሶምሶን ፣ እመሰ ገበርክሙ ዘንተ ኢይፈቅድ በቀልየሰ እምአሐዱ ለኵልክሙ እምረስይኩ ።

፰ ወዘበጠሙ ሶምሶን ውስተ አቍያጽ እገሪሆሙ ወከነ ዐቢይ ቀትል ፣ ወወረደ ሶምሶን ወነበረ ውስተ ፈለግ ውስተ በዐተ ኤጣም ።

፱ ወዐርጉ ኢሎፍሊ ወኀደሩ ላዕለ ይሁዳ ወነበሩ ኀበ መንከሰ አድግ ።

፲ ወይቤልዎሙ ኵሉ ሰብአ ይሁዳ ለምንት ዐረግሙ ላዕሌነ ወይቤሉ ኢሎፍሊ ከመ ንእስሮ ለሶምሶን ዐረግነ ወንግበሮ በከመ ገብረነ ።

፲፩ ወወረዱ ሠላሳ ምእት ብእሲ እምይሁዳ ኀበ በዓተ ኰኵሕ ዘኤጣም ፣ ወይቤልዎ ለሶምሶን ኢተአምርኑ ከመ

ኸኖል አትወደኝም አለችው ፣ ሶምሶንም እነሆ ለናቴና ላባቴ ያልነገርሁትን ላንቺ እነግርሻለሁን፤ አላት ።

በዓል በሚያደርግባቸው በሰባቱ ቀኖች አለቀሰችበት ከዚህ በኋላ በዘበዘበችው ጊዜ በሰባተኛይቱ ቀን ነገራት ፣ እሷም ለወገኖቿ ልጆች ነገረቻቸው ።

እነዚያም ሰዎች በሰበተኛይቱ ቀን ፀሐይ ሳይገባ ፣ ከማር የሚጣፍጥ ፣ ከአንበሳስ የሚበረታ (የሚፀና) ምን አለ፤ አሉት ፣ ሶምሶንም ሚስቴን ባትዘበዝቧት ምሳሌዬን ባላገኛችኋት ነበር አላቸው ።

የእግዚአብሔር መንፈስ ረድኤት አደረበት ፣ ወደ አስቃሎና ወርዶ ሠላሳ ሰዎች ገድሎ ልብሳቸውን ገፍፎ ምሳሌውን ለነገሩት ሰዎች ሰጣቸው ፣ ሶምሶንም ተቈጥቶ ወዳባቱ ቤት ተመለሰ ። ዘፍ፡ ፵፭ ፳፪ ። መሳ፡ ፫ ፲ ፣ ፩ ፲፱ ።

የሶምሶንም ሚስት ከሁለተኛው ከሥር ሚዜው ጋራ ተቀመጠች ።

ምዕራፍ ፲፭ ።

ከዚያ ቀን በኋላ የሥንዴ አዝመራ በደረሰበት ወራት ሶምሶን ሚስቱን ጐበኘት አንድ የፍየል ጠቦትንም አመጣላት ፣ ከሚስቴ ዘንድ ወደ ጫጉላው ቤት ልግባ አለ ፣ አባቷም ወደሷ መግባትን ከለከለው ።

አባቷ ጠላኋት ብለኸልና ለሥር ሚዜህ አጋባኋት ፣ ነገር ግን እነሆ ታናሽ እኅቷ አለች ፣ በመልክም ከሷ ትበልጣለች፤ ስለሷ ፈንታ ሚስት ትሁንህ አለው ።

ሶምሶንም እኔ በናንተ ክፉ ነገር አደርጋለሁና ከኢሎፍላውያን እኔ አንድ ጊዜ ንጹሕ ነኝ አለ ።

ሶምሶን ሂዶ ሦስት መቶ ቀበሮችን ያዘ፡ መብራት (ችቦ) አምጥቶ ብጅራታቸው አሰረ፤ በሁለቱ ጅራቶቻቸው መካከል አንድ ዳበት (ችቦ) አደረገ ። መሳ፡ ፯ ፲፮ ።

በዚያም ዳበት እሳት አቃጥሎ ወደ ኢሎፍላውያን አዝመራ ሰደዳቸው ፣ የታጨደውን ክምርና እሸቱን የተከመረውንና የቆመውንም የዘይቱንና የወይኑንም በታ አቃጠሉ ። ዘፀ፡ ፳፪ ፮ ።

ኢሎፍላውያንም ይህን ያደረገ ማነው፤ አሉ ሚስቱን ቀምተው ለሥር ሚዜው ሰጥተዉበታልና የቴምናታው ሰው አማች ሶምሶን ነው አሏቸው ፣ ኢሎፍላውያንም መጥተው ያባቷን ቤት አቃጠሉ ፣ እሷንም በእሳት አቃጠሏት።

ሶምሶንም ደግ አደረጋችሁ ጠቤ ግን ከአንድ ሰው ብቻ አልነበረም ሁላችሁንም ላጠፋችሁ ነበር አላቸው ።

ሶምሶንም ጭንጭናቸውን ሰበራቸው ፣ ብርቱ ሰልፍም ተደረገ፣ ሶምሶንም ወርዶ ኤጣም በምትባል ዋሻ በወንዝ ዳር ተቀመጠ ። መሳ፡ ፲፭ ፲፩ ። ኢሳ፡ ፪ ፳፩ ።

ኢሎፍላውያንም ዘምተው በይሁዳ ሰፈሩ ፣ የአህያ ምንጋጋም በለበት በታም ተቀመጡ። ፪ ሳሙ፣ ፭ ፲፰ ፡ ፳፪።

የይሁዳም ሰዎች ሁሉ ለምን ወደኛ ወጣችሁ፤ (ዘመታችሁ) አሏቸው ፣ ኢሎፍላውያንም ሶምሶንን እናስረው ዘንድ እንዳደረገንም እናደርገው ዘንድ ወጣን አሏቸው ።

ከይሁዳም ሦስት ሺሕ ሰዎች በኤጣም ወዳለች ዋሻ ወርደው ሶምሶንን ኢሎፍላውያን እንዲገዙን አታውቅ

ኢሎፍሊ ይኴንኑነ ለምንት ከመዝ ገበርከ ላዕሌነ ፤ ወይቤ
ሎሙ ሶምሶን በከመ ገብሩ ላዕሌከሙ ከማሁ ገበርኩ
ላዕሌሆሙ ።
፲፪ ወይቤልዎ ከመ ንእስርከ ወረድነ ወናግብእከ ውስተ
እደዊሆሙ ለኢሎፍሊ ፤ ወይቤሎሙ ሶምሶን መሐሉ ሊተ
አንትሙ ከመ ኢትቀትሉኒ ወአግብኡኒ ሎሙ ወአንትሙ
ሰ ኢትትረከቡ ምስሌየ ወመሐሉ ሎቱ ።
፲፫ ወይቤልዎ አልቦ ዳእሙ ነአስረከ በማእሰር ወናገብእከ
ውስተ እደዊሆሙ ወቀቲለሰ ኢንቀትለከ ፤ ወአሰርዎ በክል
ኤቱ መፃምድ ሐዲሳት ወአውፅእዎ እምይእቲ ኰኵሕ ።
፲፬ ወበጽሐ እስከ ኀበ ዐጽመ መንከሰ አድግ ወወውዑ
ኢሎፍሊ ወተቀበልዎ ወሮጹ ኀቤሁ ፤ ወመጽአ ላዕሌሁ
መንፈሰ እግዚአብሔር ወኮኑ እልክቱ መፃምድ እለ ውስ
ተ መዝራዕቱ ከመ ሰበ ያጼኑ ኀሠረ እሳተ ወተፈትሐ ማሕ
ሚሁ እመዝራዕቱ ።
፲፭ ወረከበ ዐፅመ መንሰከ አድግ ግዱፈ ውስተ ፍኖት
ወአትሐተ እዴሁ ወተመጠውዋ ወቀተለ ባቲ ዐሠርተ ም
እተ ብእሴ ።
፲፮ ወይቤ ሶምሶን ፤ በዐፅመ መንሰከ አድግ ቀተልኩ ዐሠ
ርተ ምእተ ብእሴ ።
፲፯ ወእምዝ ሶበ አኅለቀ ነቢበ ገደፋ ለይእቲ ዐፅመ መን
ሰከ እምእዴሁ ወሰመዮ ለውእቱ መከን ቀትለ ዐፅመ
መንሰከ ።
፲፰ ወጸምአ ጥቀ ወጸርሐ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ ፤ አን
ተ አግባእከ ውስተ እደ ገብርከ ዘንተ ሕይወተ ዐቢየ ወይ
እዜሰ እመውት በጽምእ ወእወድቅ ውስተ እደዊሆሙ ለቈ
ላፋን ።
፲፱ ወአርኀወ እግዚአብሔር ንቅዐታ ለይእቲ ዐፅመ መን
ሰከ ወወፅአ እምኔሃ ማይ ወሰትየ ወገብአት ነፍሱ ወአዕ
ረፈ ፤ ወበበይነ ዝንቱ ተሰምየ ስሙ ለውእቱ መካን ነቅዐ
ዐፅመ መንከሰ እስከ ዮም ።
፳ ወኰነኖሙ ለእስራኤል በመዋዕለ ኢሎፍሊ ዕሥራ
ዓመተ ።

## ምዕራፍ ፲፮ ።

፩ ወሖረ ሶምሶን እምህየ ውስተ ጋዛ ወርእየ በህየ ብእ
ሲተ ዘማ ወቦአ ኀቤሃ ።
፪ ወነገርዎሙ ለሰብአ ጋዛ ወይቤልዎሙ ፤ መጽአ ሶም
ሶን ዝየ ፤ ወዖድዎ ወዐገትዎ ኵሉ ሌሊተ ውስተ አንቀጸ
ሀገር ፤ ወጸንሕዎ ኵላ ሌሊተ ወይቤሉ ፤ ንጸንሖ ኵላ ሌሊ
ተ ወንቀትሎ በጽባሕ ።
፫ ወኖመ ሶምሶን እስከ መንፈቀ ሌሊት ወተንሥአ ሶም
ሶን በመንፈቀ ሌሊት ወአኀዘ ለኖኀተ ሀገር ዘአንቀጽ በክ
ልኤሆን ረግዛቲሃ ወዖሮሙ ምስለ ኵሉ ሰብኡ ወተሰ
ከመ ላዕለ መትከፍቱ ፤ ወአዕረጎሙ ላዕለ ርእሰ ደብር ዘቅ
ድመ ኬብሮን ወአንበሮሙ ህየ ።
፬ ወእምድኅረ ዝንቱ አፍቀረ ብእሲተ በኀበ ፈለገ ሦሬቅ
ወስማ ደሊላ ።

ምን በኛ ለምን እንዲህ አደረግህ ፤ አሉት ፤ ሶምሶንም በና
ንተ እንዳደረጉብኝሁ እኔም በነሳቸው እንደዚያው አደረ
ግሁባቸው አላቸው ። መሳ፡ ፲፭ ፲፪ ፤ ፲፬ ፥ ፱ ።
አስረን ለኢሎፍላውያን እንሰጥህ ዘንድ ወረድን አሉ
ት ፤ ሶምሶንም እናንተ እንዳትገድሉኝ ማሉልኝ ፤ ለነሱ
ለሳሌፉችሁ ሸጡኝ እናንተ ግን እኔን በጠብ አትገናኙኝ
አላቸው ፤ እነሱም ማሉለት ።
በእግር ብረት አስረን እንሰጥሃለን እንጂ የምንተውህ
አይደለም መግደል ግን አንገድልህም አሉት ፤ በሁለትም
አዲስ ገመድ አስረው ከዚያች አለት አወጡት ።
የአህያ ምንጋጋ አጥንት ወዳለበት ቦታ ደረሰ ፤ ኢሎ
ፍላውያንም ደንፍተው ተቀበሉት ፤ ወደሱም ሮጡ ፤ በሱ
ም የእግዚአብሔር መንፈስ ረድኤት አደረበት ፤ በክንዱ
ያሉ ላመ ገመዶችም ገለባ እሳት በበላው ጊዜ እንዲያርር
አርሮ ኩምትር አሉ እስራቱም ከክንዱ ተፈታ ።
ያህያ ምንጋጋ አጥንት በጉዳና ወድቆ አገኘ ፤ እጁን
ዘቅ አድርጎ አንሳት በዚያችም ሺሕ ሰዎችን ገደለበት ።
ዘሌዋ፡ ፳፮ ፰ ። ኢያ፡ ፳፫ ፲ ። ኢሳ፡ ፩ ፯ ።
ሶምሶን በአህያ ምንጋጋ አጥንት ሺሕ ሰዎችን ገደ
ልኩ አለ ። መሳ፡ ፫ ፴፩ ።
ከዚህ በኋላ ይህን ተናግሮ በፈጸመ ጊዜ ያችን የአህያ
ምንጋጋ አጥንት ከእጁ ጣላት ፤ ያነንም ቦታ ስሙ የአህያ
ምንጋጋ አጥንት ሰልፍ የተደረገበት አለው ።
ውኃን እጅግ ተጠማ ፤ ወደ እግዚአብሔርም ለመነ ፤
ይህን ታላቅ ድኅነት በኔ በባርያህ እጅ አደረግህ አሁን ግን
በውኃ ጥም እሞታለሁ ፤ በነዚህም በቈላፋን እጅ እወድ
ቃለሁ አለ ። ዘፍ፡ ፵፰ ፳፪ ። መሳ፡ ፲፪ ፲፯ ።
እግዚአብሔርም ከዚያች ከአህያ ምንጋጋ ውኃን አፈ
ለቀለት ፤ ያነንም ጠጥቶ ነፍሱ ተመልሳለት ከውኃ ጥም
ዐረፈ ፤ ስለዚህ የዚያ ቦታ ስሙ እስከሁን ድረስ ከአህያ
ምንጋጋ ውኃ የፈለቀበት ተባለ ። መሳ፡ ፲፭ ፱ ።
በኢሎፍላውያንም ዘመን እስራኤልን ሃያ ዘመን
ገዛቸው ። መሳ፡ ፲፫ ፩ ።

## ምዕራፍ ፲፮ ።

ሶምሶን ከዚያ ወደ ጋዛ ሄደ ፤ በዚያም ጋለሞታ ሴት
አይቶ ወደርሷ ገባ ፤ (ደረሰባት) ። መሳ፡ ፲፯ ፳፩ ።
ለጋዛም ሰዎች ሶምሶን ወደዚህ መጣ ብለው ነገሩዋ
ቸው ፤ በከተማውም በር መላ ሌሊቱን ሁሉ ከበበው ሲጠ
ብቁት አደሩ ፤ ሌሊቱን ሁሉ ስንጠብቀው አድረን ሲነጋ
እንገድለው አሉ ። ዮሐ፡ ፱ ፳፱ ።
ሶምሶንም እስከ ሌሊቱ እኩሌታ ድረስ ተኛ ፤ በሌሊ
ቱም እኩሌታ ተነሥቶ በከተማው በር ያሉ የመጠበቂያ
ውን ደጃፍ ሁለቱን መቃን መድረኩን ያዘ ፤ ከሰዎቹ ሁሉ
ጋራ በትከሻው ተሸክሞ በኬብሮን አንጻር ወዳለ ተራራ
አውጥቶ በዚያ አፈሰሳቸው ።
ከዚህም በኋላ በሦራሕ ወንዝ አጠገብ ያለች ሴትን ወ
ደደ ፤ ስሟም ደሊላ ይባላል ። ዘፍ፡ ፵፱ ፲፭ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወዐርጉ ኀቤሃ መሳፍንተ ኢሉፍሊ ፣ ወይቤልዋ አስ ፍጢዮ ወአእምሪ በምንት ዓብየ ኃይሉ ወበምንት ንክሎ ወነአስሮ ከመ ናድክሞ ፣ ወንሁበኪ ንሕነ ዓሠርቱ ምእት ብእሲ ዓሠርተ ምእተ ብሩረ ። | ፭ | የኢሉፍሊ ሹማምንትም ወደርሷ ወጥተው አባብሊ ልን ፣ ጽኑ የሆነ ኃይሉ በምን ፣ እንደሆነ በምንም እንድን ችለውና እናደክመው ዘንድ በምንም እንድናስረው ዕወቂ እኛ ሺው ሰዎች ሺሕ ብር እንሰጥሻለን አሏት ። |
| ወትቤሎ ደሊላ ለሶምሶን አይድዐኒ ምንት ውእቱ ኃይ ልከ ዓቢይ ወበምንት እመ አሰሩከ ትደክም ። | ፮ | ደሊላም ሶምሶንን ኃይልህ ጽኑ መሆኑ በምን እንደ ሆነ ንገረኝ፣ በምንስ ቢያስሩህ ትደክማለህ ! አለችው ። |
| ወይቤላ ሶምሶን እመ አሰሩኒ በሰብዐቱ አውታር ሐዲ ሳት እለ አልበሙ ብትከት አደክም እንከ ወእከውን ከመ አሐዱ እምእጓለ እመሕያው ። | ፯ | ሶምሶንም በሰባት ባልደረቀ እርጥብ ጠፍሮች ቢያ ስሩኝ እደክማለሁ ከሰውም እንደ አንዱ እሆናለሁ አላት። ኢዮብ ፴ ፲፩ ፡ መዝ፡ ፲፩ ፪ ። ሕዝ፡ ፴፯ ፳፱ ። |
| ወአምጽኡ ላቲ መሳፍንተ ኢሉፍሊ ሰብዐተ አውታረ ሐዲሳተ እለ አልበሙ ብትከት ወአሰረቶ በሙ ። | ፰ | የኢሉፍሊም ሹማምንት አዲሶች የሆኑ መቁረጥ የሌ ለባቸው ሰባት አውታሮችን አመጡላት፣ በነሳቸውም አሰረችው ። |
| ወአለሰ ይጸንሕዎ ይነብሩ ውስተ ውሣጢት ወትቤሎ መጽኡከ ኢሉፍሊ ሶምሶን ፣ ወበተኮሙ ለአውንቱ አው ታር ከመ ይትበተክ ፈትል ሶበ ያጼኑ እሳተ ወኢተዐውቀ ኀይሉ ። | ፱ | የሚጠብቁት ሰዎች ግን በውስጥ ነበሩ ፣ እርሷም ሶም ሶን ! ኢሉፍላውያን መጡብህ አለችው ፣ እነዚያንም አው ታሮች ፈትል እሳት በሸተተው ጊዜ እንዲቈረጥ ቈረጣ ቸው የአውታሩም ኃይል አልታወቀም ። |
| ወትቤሎ ደሊላ ለሶምሶን ፣ ናሁ አስተሐቀርከኒ ወሐ ሰተ ተናገርከኒ ፣ ወይእዜኒ አይድዐኒ በምንት የአስሩከ ። | ፲ | ደሊላም ሶምሶንን እነሆ ሸነገልከኝ ሐሰት ነገርን ነገር ከኝ ፣ አሁንም እውነቱን ንገረኝ በምን ቢያስሩህ ነው ኃይልህ የሚደክመው ! አለችው ። |
| ወይቤላ እመ አሰሩኒ በሰብዐቱ መፃምድ እለ ኢገብሩ በሙ ግብረ አደክም እንከ ወእከውን ከመ አሐዱ እምነ እጓለ እመሕያው ። | ፲፩ | ሥራ ባልሠሩባቸው በሰባት ገመዶች ቢያስሩኝ ከዚህ በኋላ እደክማለሁ ፣ ከሰውም እንዳንዱ እሆናለሁ አላት ። መሳ፡ ፲፭ ፲፫ - ፲፬ ፣ ፲፮ ፯ - ፲፯ ። |
| ወነሥአት ደሊላ ሰብዓተ መፃምደ ሐዲሳተ ወአሰረቶ በሙ ፣ ወትቤሎ ኢሉፍሊ መጽኡከ ሶምሶን ፣ ወአለሰ ይጸ ንሕዎ ይነብሩ ውስተ ውሣጢት ወበተኮሙ እመዝራዕቱ ከመ ፈትል ። | ፲፪ | ደሊላም ሰባት አዳዲስ ገመዶች አምጥታ በነሱ አሰረች ሶምሶን ! ኢሉፍላውያን መጡብህ ! አለችው ፣ የሚጠብ ቁት ሰዎች ግን በውስጥ ነበሩ ከክንዱም እንደ ፈትል ቈረጣቸው ። |
| ወትቤሎ ደሊላ ለሶምሶን ፣ ወይእዜኒ አስተሐቀርከኒ ወሐሰተ ተናገርከኒ ወኢያይዳዕከኒ አይድዐኒ እንከሰ በም ንት የአስሩከ ። | ፲፫ | ደሊላም ሶምሶንን አሁንም ሸነገልከኝ ሐሰት ነገርን ም ነገርከኝ፣ እውነቱን አልነገርከኝም እንግዲህ እውነ ቱን ንገረኝ በምን ቢያስሩህ ኃይልህ ይደክማል ! አለችው። |
| ወይቤላ እመ ፀፈርኪዮን ለሰብዑ ቊናዝዕየ ዘርእስየ ወተከልክዮን በሰብዐቱ መታክል ውስተ አረፍት አደክም እንከ ወእከውን ከመ አሐዱ እምእጓለ እመሕያው ። | ፲፬ | በራሴ ያሉ ሰባቱን ብርንጉዎች (ጕንጕኖች) አስረሽ በኖራው ላይ በሰባት ካስማዎች ብታስመቺያቸው ከዚያ በኋላ ኃይሌ ይደክማል ፣ ከሰውም እንደ አንዱ እሆናለሁ አላት። |
| ወአኖመቶ ደሊላ ወፀፈረቶን ለሰብዑ ቊናዝዒሁ ዘር እሱ በኃይል ወተከለቶን በመታከል ውስተ አረፍት ፣ ወት ቤሎ መጽኡከ ኢሉፍሊ ሶምሶን ፣ ወነቅሐ እምንዋሙ ወነዘዐ ውእቱ መታክለ እምነ አረፍት ምስለ ቊናዝዒሁ ወኢተዐውቀ ኃይሉ ። | ፲፭ | ደሊላም አስተኝታ በራሱ ላይ ያሉ ሰባቱን ብርንጉዎ ቹን በኃይል አሰረቻቸው በኖራው ላይ በካስማ አስመታቻ ቸው ሶምሶን ኢሉፍላውያን መጡብህ ! አለችው ፣ ከእን ቅልፉም ተነሥቶ ያነን ካስማ ከብርንጉዎቹ (ከቆንዳላዎቹ) ጋራ ከኖራው (ከግድግዳው) ነቀለው ኃይሉም የሚደክም በት አልታወቀም ። መሳ፡ ፱ ፳፩ ። |
| ወትቤሎ ደሊላ ፣ እፎ ትቤለኒ አፍቀርኩኪ ወልብየ ምስሌኪ ወናሁ ሣልስከ ዝንቱ እንዘ ታስተሐቅረኒ ወኢታ የድዐኒ በምንት ውእቱ ኀይልከ ዐቢይ ። | ፲፮ | ደሊላም እውድሻለሁ ልቤም ካንቺ ጋር ነው ለምን ትለኛለህ እነሆ ስትሸነግለኝ ይህ ሦስተኛህ ነው ፣ ኃይልህ ጽኑ መሆኑ ፣ በምን እንደሆነ አልነገርከኝም ! አለችው ። |
| ወእምዝ ሰበ አሥረሐቶ በነቢብ ኵሉ ሌሊተ አጽሐ በቶ እስከ ተቈጥዐ ለሞት ። | ፲፯ | ከዚህ በኋላ መላ ሌሊቱን በነገር ባደከመችው ጊዜ ልሙት ብሎ እስኪበሳጭ ድረስ ዘበዘበችው ። |
| ወአይድዓ ኵሎ ዘውስተ ልቡ ወይቤላ መላጺ ኢለከ ፈኒ ርእስየ ፣ እስመ ናዝራዊ አነ ለእግዚአብሔር እምከርሠ እምየ ወእምከመ ተላጸይኩ የኀድገኒ ኀይልየ ወእደክም ወእከውን ከመ ኵሉ እጓለ እመሕያው ። | ፲፰ | በልቡ ያለውን ሁሉ ነገራት ፣ እኔ ለእግዚአብሔር የስ ለት ልጅ ነኝና ከናቴ ማኅፀን ከተወለድኩ ጀምሮ ምላጭ ራሴን አልነካኝም ፣ ጠጕሬን ከተላጨሁ ኃይሌ ይነሣል ፣ እደክማለሁ ፣ ከሰው እንደ አንዱ እሆናለሁ አላት ። |

፲፰ ወአእመረት ደሊላ ከመ አይድዓ ኵሉ ዘውስተ ልቡ ወለአከት ወጸውዓቶሙ ለመላእክተ ኢሎፍሊ እንዘ ትብል ንዑ አሐተ ዕርጉ እስመ አይድዐኒ ኵሉ ዘውስተ ልቡ ወዐርጉ ኀቤሃ ኵሎሙ መሳፍንተ ኢሎፍሊ ወአምጽኡ ወርቀ ምስሌሆሙ ።

፲፱ ወአኖመቶ ማእከለ ብረኪሃ ወጸውዐት ቀረጼ ወቀረጾቶን ለሳቡዐ ቌናዝወ ርእሱ ወአኀዘ ይድክም ወኀደጎ ኃይሉ ።

፳ ወትቤሎ ደሊላ መጽኡከ ኢሎፍሊ ሶምሶን፣ ወነቅሐ እምንዋሙ ወይቤ እወፅእ ወእገብር ከመ ዘልፍ ወእነጽሖሙ ወውእቱሰ ኢያእመረ ከመ ኀደጎ እግዚአብሔር ።

፳፩ ወአኀዝዎ ኢሎፍሊ ወአውፅኡ አዕይንቲሁ ወአውረድዎ ውስተ ጋዛን ወሞቅሕዎ በመዋቅሕተ ሐፂን ወአንበርዎ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ይሕርጽ ።

፳፪ ወአኀዘ ሥዕርቱ ይብቍል እምዘቀረፅዎ ።

፳፫ ወተጋብኡ መላእክተ ኢሎፍሊ ከመ ይሡዑ መሥዋዕተ ለአምላኮሙ ወከመ ይትፈሥሑ፣ ወይቤሉ አግብአ አምላክነ ለሶምሶን ፀርነ ውስተ እዴነ ።

፳፬ ወሶበ ርእይዎ ሕዝብ አእኰትዎ ለአምላኮሙ ወይቤሉ አግብአ አምላክነ ለፀርነ ውስተ እዴነ ዘአማሰና ለምድርነ ወአብዝኀ አብድንቲነ ።

፳፭ ወእምዝ ሶበ ተፈሥሑ ይቤሉ ጸውዕዎ ለሶምሶን እምነ ቤተ ሞቅሕ ይትዌነይ በቅድሜነ፣ ወጸውዕዎ ለሶምሶን እምነ ቤተ ሞቅሕ ወተሣለቁ ላዕሌሁ ወአቀምዎ ማእከለ ክልኤቱ አዕማድ ።

፳፮ ወይቤሎ ሶምሶን ለወልድ ዘይመርሖ አዕርፈኒ ወአግሥሥኒ አዕማደ እለ ዲቤሆን ይቀውም ዝንቱ ቤት ወእስምከኒ ላዕሌሆን ወገብረ ሎቱ ውእቱ ወልድ ከማሁ ።

፳፯ ወመልአ ውስተ ውእቱ ቤት እድ ወአንስት ወሀለዉ ህየ ኵሎሙ መሳፍንተ ኢሎፍሊ ውስተ ናሕሱ ወየአክሉ ሠላሳ ምእተ ጸደወ ወአንስተ ከመ ይነጽርዎ ለሶምሶን ከመ ይትዌነይ ።

፳፰ ወጸርሐ ሶምሶን ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ፣ እግዚኦ እግዚኦ ተዘከረኒ ወአጽንዐኒ አሐተ እንከ እትቤቀል በቀለ አሐተ ህየንተ ክልኤሆን አዕይንትየ እምነ ኢሎፍሊ ።

፳፱ ወአኀዘን ሶምሶን ለእልክቱ ክልኤሆን አዕማድ እለ ማእከል እለ ዲቤሆን ይቀውም ውእቱ ቤት ወገፍዖን አሐተ በየማኑ ወአሐተ በፀጋሙ ።

፴ ወይቤ ሶምሶን ለትሙት ነፍስየ ምስለ ሰብአ ኢሎፍሊ፣ ወአጠቆን በኀይሉ ወወድቀ ውእቱ ቤት ላዕለ መሳፍንተ ኢሎፍሊ ወላዕለ ኵሉ ሕዝብ ዘውስቴቱ፣ ወኮኑ እለ ሞቱ እለ ቀተለ ሶምሶን በሞቱ ፈድፋደ፣ እምእለ ቀተለ በሕይወቱ ።

፴፩ ወወረዱ አኀዊሁ ወኵሉ ቤተ አቡሁ ወፆርዎ ወነሥእዎ ወቀበርዎ ማእከለ ሦራሕ ወማእከለ ኤስታዎል ውስተ መቃብረ ማኑሄ አቡሁ፣ ወኰነኖሙ ለእስራኤል ውእቱ ዕሥራ ዓመተ ።

ደሊላም በልቡ ያለውን ሁሉ እንደነገራት አውቃ፣ በልቡ ያለውን ሁሉ ነግሮኛልና አንድ ጊዜ ኑ ብላ የኢሎፍሊን አለቆች ልካ አስጠራቻቸው የኢሎፍሊም አለቆች ሁሉ ወደሷ መጡ፣ ከነሳቸውም ጋር ወርቅን አመጡ። መሳፍ፣ ፲፫ ፭፣ ፲፮ ፭፣

እሷም በጭኖቿ መካከል አስተኛችው፣ ጠጉር የሚቈርጥ ሰውን ጠርታ ሰባቱን የራሱን ብርንጐዎች አስቈረጠቻቸው፣ እሱም ይደክም ጀመር፣ ኃይሉም ተነሣው ።

ደሊላ ሶምሶንን ኢሎፍላውያን መጡብህ፤ አለችው፣ ከእንቅልፉም ተነሥቶ ወጥቼ እንደ ወትሮ አደርጋለሁ፣ አጠፋቸውም አለሁ ቢል እንደ ወትሮው ማድረግ ተሳነው እሱ ግን እግዚአብሔር እንደ ተለየው አላወቀም ።

ኢሎፍላውያንም ይዘው ሁለት ዓይኖቹን አወጧቸው ወደ ጋዛንም አውርደው በእግር ብረት አሰሩት በግዞትም ሁኖ እኽልን ይፈጭ ነበር። ዘኍ፣ ፲፮ ፲፬ ።

ጠጕሩም ከላጩት በኋላ፣ ይበቅል (ያድግ) ጀመር ።

የኢሎፍሊም አለቆች ለጣኦታቸው መሥዋዕትን ይሠዉ ዘንድ ደስም ይላቸው ዘንድ ተሰበሰቡ፣ ፈጣሪያችን ጠላታችን ሶምሶንን በእጃችን ጣለልን አሉ ።

ሕዝቡም ባዩት ጊዜ ፈጣሪያቸውን(ጣኦታቸውን) አመሰገኑት፣ አገራችንን ያጠፋት ሬሳዎቻችንንም ያበዛ ጠላታችንን በእጃችን ጣለው አሉ ። ዳን፣ ፭ ፬ ።

ከዚህ በኋላ በልተው ጠጥተው ደስ ባላቸው ጊዜ በፊታችን ይጫወት ዘንድ ሶምሶንን ከግዞት ቤት ጥሩት አሉ፣ ሶምሶንንም ከግዞት ቤት ጠርተዉት በሱ ተዘባበቱበት በሁለት ምሰሶዎች መካከልም አቆሙት ።

ሶምሶን ያን የሚመራውን ብላቴና አሳርፈኝ ይህ ቤት የቆመባቸው ምሰሶዎችንም አስጨብጠኝ ወደነሳቸውም አስጠጋኝ አለው፣ ያም የሚመራው ብላቴና እንዳለው አደረገለት ።

በዚያች ቤት ወንዶችም ሴቶችም መልተው ነበር፣ የኢሎፍሊ ሹማምንትም ሁሉ በዚያ በሰገነት ነበሩ፣ ሶምሶንም ሲጫወት ያዩት ዘንድ የተሰበሰቡ ወንዶችም ሴቶችም ሦስት ሺሕ ይሆኑ ነበር ።

ሶምሶንም ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፣ አቤቱ! አቤቱ! አስበኝ አንዲትም ነገርንም አድምጠኝ፣ እንግዲህ ስለ ሁለቱ ዓይኖቼ ፈንታ ከኢሎፍላውያን አንዲት በቀል ልመልስ አለ።

ሶምሶን ያ ቤት በላያቸው የተደገፈባቸው በመካከል ያሉ እነዚያን ሁለት ምሰሶች ያዛቸው አንዲቱን በቀኙ አንዲቱን በግራው፣ ይዞ ገፋቸው ።

ሶምሶን ሰውነቴ ከኢሎፍሊ ሰዎች ጋራ ትሙት ብሎ በኃይሉ ነቀነቃቸው፣ ያም ቤት በውስጡ ባሉ በሕዝቡ ላይና በኢሎፍሊ ሹማምንት ላይ ወደቀባቸው፣ የሞቱትም እንዲህ ሆኑ፣ ሶምሶን በሕይወቱ ሳለ ከገደላቸው ሊሞት የገደላቸው በዙ ።

ያባቱ ወገኖች ሁሉና ወንድሞቹም ወርደው ይዘው ወሰዱት በኤስታዎስ መከከልና በሦራሕ መከከል ባለ በአባቱ በማኑሄ መቃብር ቀበሩት፣ እሱም እስራኤልን ሃያ ዘመን ገዛቸው ። ኢያ፣ ፲፭ ፴፫ ። መሳ፣ ፲፫ ፳፭ ።

## ምዕራፍ ፲፯።

፩ ወሀለወ ብእሲ ዘእምደብረ ኤፍሬም ዘስሙ ሚካ።

፪ ወይቤላ ሚካ ለእሙ፣ ዝክቱ ወርቅ ዘትቤልኒ ተሰርቀኒ ወእምሐልኪ ናሁ ወርቁ ኀቤየ ውእቱ አነ ነሣእክዎ፣ ወትቤ እሙ ቡሩክ ወልድየ ለእግዚአብሔር።

፫ ወአግብአ ውእተ ወርቀ ዐሠርተ ወአሐደ ምእተ ለእሙ፣ ወትቤ እሙ ቀድሶ ቀደስክዎ ለውእቱ ወርቅ ለእግዚአብሔር እምእዴየ ለበሕቲትየ ከመ ይትገበር ግልፎ ወስብክ ወይእዜኒ አገብኦ ለኪ ወእሁበኪዮ።

፬ ወመሀበ ውእተ ወርቀ ለእሙ ወነሥአት እሙ ውእተ ወርቀ ወመሀበት እምኔሁ ክልኤተ ምእተ ብሩረ ለዘይሰብክ ወይገብር ግልፎ ወስብከ፣ ወአንበርዎ ውስተ ቤተ ሚካ።

፭ ወለብእሲሁሰ ሚካ ሎቱ ቤተ አማልክት ወገብረ ምስለ ወተራጺነ ወመልአ እዴሁ ለአሐዱ እምደቂቁ ወኮኖ ካህነ።

፮ ወበእማንቱ መዋዕል አልቦሙ ንጉሠ ለደቂቀ እስራኤል፣ ብእሲ ብእሲ ዘአደሞ ቅድመ አዕይንቲሁ ይገብር።

፯ ወሀለወ ወልድ ዘእምቤተልሔም ዘእምሕዝበ ይሁዳ ወእምዘመደ ይሁዳ ወሌዋዊ ውእቱ ብእሲሁ ወይነብር ህየ።

፰ ወሖረ ውእቱ ብእሲ እምሀገረ ይሁዳ ወእምቤተ ልሔም ከመ ይኅድር ኀበ ረከበ ወበጽሐ ውስተ ደብረ ኤፍሬም ኀበ ቤተ ሚካ ከመ ይቢት።

፱ ወይቤሎ ሚካ እምአይቴ መጻእከ፣ ወይቤሎ ሌዋዊ አነ እምቤተ ልሔም ዘይሁዳ ወአሐውር እንበር ኀበ ረከብኩ።

፲ ወይቤሎ ሚካ ንበር ምስሌየ ወኩነኒ አበ ወካህነ ወአነ እሁበከ ዐሥሩ ኀብስተ ለለዕለትከ ወዘውገ አልባስ ወሲሳየከ።

፲፩ ወአኀዘ ውእቱ ሌዋዊ ይንበር ምስለ ውእቱ ብእሲ፣ ወኮኖ ውእቱ ወልድ ከመ አሐዱ እምደቂቁ።

፲፪ ወመልአ እዴሁ ሚካ ለውእቱ ሌዋዊ ወኮኖ ውእቱ ወልድ ካህነ ወነበረ ውስተ ቤተ ሚካ።

፲፫ ወይቤ ሚካ ይእዜ አእመርኩ ከመ አሠናየ ላዕሌየ ገቢረ እግዚአብሔር እስመ ኮነኒ ሌዋዊ ካህነ።

## ምዕራፍ ፲፰።

፩ ወበእማንቱ መዋዕል አልቦሙ ንጉሠ ለእስራኤል ወበእማንቱ መዋዕል የኀሥሡ ሎሙ ርስተ ሰብአ ዳን ኀበ ይነብሩ እስመ ኢረከቡ እስከ ይእቲ አሚር ርስተ በማእከለ እስራኤል።

፪ ወፈነዉ ደቂቀ ዳን እምሕዝበሙ ኀምስተ እደወ እመክፈልቶሙ ደቂቀ ኀይል እምነ ሦራኅ ወእስታሐል ከመ ይርአዩዋ ለምድር ወያእምርዋ፣ ወይቤልዎሙ ሑሩ ወርእዩ ለነ ምድረ ወበጽሑ ውስተ ምድረ ኤፍሬም ኀበ ቤተ ሚካ፣ ወኀደሩ ህየ እሙንቱ ኀበ ቤተ ሚካ።

## ምዕራፍ ፲፯።

በኤፍሬም ነገድ ዕጣ ስሙ ሚካ የሚባል አንድ ሰው ነበር።

ሚካ እናቱን ተሰረቀብኝ ያልሽኝ ያማልሽበት ፺ ብር እነሆ ብሩ በኔ ዘንድ አለ፣ እኔ ወስጄዋለሁ አላት፣ እናቱም ልጄ ለእግዚአብሔር የተባረክህ ሁን አለችው።

ያንን ሺሕ መቶውን ወቄት ብር ለናቱ መለሰ፣ እናቱም ያንን ብር መልክ ያለው ጣኦት ይሠራ ዘንድ ለእግዚአብሔር ከእጄ ብቻዬን ለየሁት፣ አሁንም መልሼ እሰጥሻለሁ አላት። ዘፀ፡ ፳ ፬። ዘሌ፡ ፲፱ ፬።

ያንንም ወርቅ ለናቱ ሰጣት፣ እናቱም ያንን ብር ተቀብላ ከሱ ሁለት መቶውን ብር መልክ ያለው ጣኦት ለሚሠራው ሰው ሰጠችው፣ በሚካ ቤትም አኖሩት።

ለሚካም የጣኦታት ቤት ነበረው፣ ምስልንም ሠራ፣ የጣኦቱንም ልብስ አሠራ፣ ከልጆቹም ያንዱን እጅ ቀብ ካህንም ሆነው። ዘፍ፡ ፴፩ ፲፱። ዘፀ፡ ፳፱ ፱።

በነዚያም ወራቶች ለእስራኤል ልጆች ንጉሥ አልነበራቸውም፣ አንዱም አንዱም ሰው በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር። መሳ፡ ፲፪ ፲።

የይሁዳ ነገድ ዕጣ ከምትሆን ከቤተ ልሔም የተወለደ ከይሁዳ ወገን የሚሆን አንድ ሰው ነበረ፣ ሰውየውም ካህን ነበር፣ በዚያም ይኖር ነበር። መሳ፡ ፲፱ ፩።

ያም ሰው የሚኖርበትን ስፍራ ለመሻት ከቤተ ልሔምና ይሁዳ ከሚባል አገር ሂዶ ወደ ኤፍሬም ተራራ ደርሶ በዚያ ያድር ዘንድ ወደ ሚካ ቤት ገባ።

ሚካም ከወዴት መጣህ፣ አለው፣ ያም ካህን እኔ የይሁዳ ዕጣ ከምትሆን ከቤተ ልሔም የመጣሁ ነኝ፣ ባገኘሁበት አድር ዘንድ እሄዳለሁ አለው። መሳ፡ ፲፩ ፵።

ሚካም ከኔ ጋር ተቀመጥ አባትም ካህንም ሁነኝ አለው፣ እኔም ዕለት ዕለት ዓሥር እንጀራ አፈራርቆህ የምትለብሰው ልብስንና ምግብህንም እሰጥሃለሁ አለው።

ያም ካህን ከዚያ ሰው ጋራ ይኖር ዘንድ ጀመረ፣ ያም ልጅ ከልጆቹ እንዳንዱ ሆነው። ዘፀ፡ ፪ ፳፩።

ሚካም ያንን ካህን እጁን ቀባው፣ ያም ልጅ ካህን ሆነው በሚካም ቤት ኖረ። መሳ፡ ፲፯ ፭፣ ፲፰ ፴።

ሚካ ሌዋዊ ካህን ሆኖልኛልና፣ እግዚአብሔር በጎ ነገር እንዳደረገልኝ አሁን ዓወቅሁ አለ።

## ምዕራፍ ፲፰።

በነዚያ ወራቶች ለእስራኤል ንጉሥ አልነበራቸውም በነዚያም ወራቶች እስከ ዚያች ቀን በእስራኤል መካከል ርስት አላገኙም ነበርና፣ የዳን ሰዎች የሚኖሩበትን ርስት ይፈልጉ ነበር። መሳ፡ ፲፯ ፮፣ ፩ ፴፬። ኢያ፡ ፲፱ ፵፯።

የዳንም ልጆች ከወገኖቻቸው ያችን አገር ያዩዋትና ያውቋት ዘንድ ከክፍላቸው ከእስታሐልና ከሦራሕ ሂዳችሁ ያችን አገር እዩልን ብለው ጽኑዓን የሆኑ አምስት ሰዎችን ላኩ፣ እነዚያም ወደ ደብረ ኤፍሬም ደርሰው ወደ ሚካ ቤት ገቡ፣ እነሳቸውም በዚያ በሚካ ቤት አደሩ።

፫ ወአእመርዎ ለውእቱ ወልድ ወሬዛ ሌዋዊ ወቦኡ ሀየ
ወይቤልዎ መኑ አምጽአከ ዝየ ወምንተ ትገብር በዝየ
ወምንት ብከ በዝየ ።
፬ ወይቤሎሙ ከመዝ ወከመዝ ረሰየኒ ሚካ ወዐሰበኒ
ወኮንክዎ ካህነ ።
፭ ወይቤልዎ ተሰአል ለነ ኀበ እግዚአብሔር እመ ይሤ
ርሕ ፍናዊነ እንተ ውስቴታ ነሐውር ንሕነ ።
፮ ወይቤሎሙ ውእቱ ካህን ሑሩ በሰላም ይእተ ፍኖተ
ክሙ ቅድመ እግዚአብሔር እንተ ባቲ ተሐውሩ ።
፯ ወሖሩ ኃምስቱ አደው ወበጽሑ ውስተ ሊሳ ወርእዩ
ሕዝበ እለ ውስቴታ ተአሚኖሙ ይነብሩ በሕገ ሲዶና ህዱ
እን ወዕሩፋን እንዘ ይትአመኑ ወኢይከሉ ነቢበ ቃል ውስ
ተ ምድረ ርስቱ መዝገበ ነገር እስመ ርኁቃን እሙንቱ
እምነ ሲዶና ወአልቦሙ ትኅላፍ ምስለ ሶርያ ።
፰ ወገብኡ እልክቱ ኃምስቱ አደው ኀበ አኀዊሆሙ ው
ስተ ሦራሕ ወአስታሐል ወይቤልዎሙ ምንት ያነብረክሙ ።

፱ ተንሥኡ ንሑር ላዕሌሃ እስመ በአናሃ ወአንሶሰውናሃ
ለይእቲ ምድር እስከ አጽናፊሃ፣ ወርኢነ ሕዝበ እለ ይነ
ብሩ ውስቴታ በሕገ ሲዶና፣ ወርኁቃን እሙንቱ እምነ ሲ
ዶና፣ ወአልቦሙ ትልኅፈ ነገር ምስለ ሶርያ ።
፲ ወባሕቱ ተንሥኡ ወንዕርግ ላዕሌሆሙ እስመ ርኢናሃ
ለይእቲ ምድር ሠናይት ጥቀ፣ ወአንትሙሰ አርምሙ ወኢ
ትትሀከዩ ሐዊረ ወበዊአ ከመ ትትዋረስዋ ለይእቲ ምድር ።
፲፩ ወእምከመ በእክሙ ትበጽሑ ኀበ ሕዝብ እለ ተአሚ
ኖሙ ይነብሩ ወምድርኒ ረኃብ እስመ አግብአ እግዚአብ
ሔር ውስተ እዴክሙ፣ ብሔር ዘአልቦ ዘይትኀጣእ እም
ኵሉ ቃል ዘተፈጥረ ውስተ ምድር ።
፲፪ ወተንሥኡ እምህየ እምብሔረ ዳን እምነ ሦራሕ ወአ
ስታሔል ስድስቱ ምእት ብእሲ እለ ቅኑታኒሆሙ ወይፀ
ውሩ ንዋየ ሐቅሎሙ ።
፲፫ ወዐርጉ ወኀደሩ ውስተ ቀርያታርም ዘይሁዳ ወበእንተ
ዝንቱ ተሰምየ ውእቱ መካን ትዕይንተ ዳን እስከ ዮም
መንገለ ድኅሬሃ ለቀርያታርም ።
፲፬ ወኀሊፎሙ እምህየ በጽሑ ውስተ ደብረ ኤፍሬም
ወመጽኡ እስከ ኀበ ቤተ ሚካ ።
፲፭ ወይቤልዎሙ እልክቱ ኃምስቱ አደው እለ ሖሩ ይርአ
ይዋ ለይእቲ ምድረ ሊሳ ወይቤልዎሙ ለአኀዊሆሙ ሰበ
ተአምሩ ከመ ቦቱ ውስተ ዝንቱ ቤት ምስል ወተራፊን
ወግልፎ ወሰብከ ወይእዜኒ አእምሩ ዘትገብሩ ።

፲፮ ወተግኅሡ ህየ ወቦኡ ውስተ ቤቱ ለውእቱ ወልድ
ሌዋዊ ውስተ ቤተ ሚካ ወተአምኅዎ ።
፲፯ ወእልክቱ ስድስቱ ምእት ብእሲ እንዘ ይፀውሩ ንዋየ
ሐቅሎሙ ቅኑታኒሆሙ ተጋብኡ ኀበ ኆኅተ አንቀጽ እለ
እምደቂቀ ዳን ።
፲፰ ወዐርጉ እልክቱ ኃምስቱ አደው እለ ሖሩ ቀዲሙ
ከመ ይርአዩ ምድረ ወቦኡ ወነሥኡ ዝክተ ምስለ ወግ
ልፎ ወተራፊን ወሰብከ ወዝክቱሰ ካህን ይቀውም ኀበ ኆ

ያን ካህን የሆነውን ሌዋዊ ልጅ ዐወቁት፣ ወደዚያ
ውም ገብተው ወደዚህ ማን አመጣህ፤ በዚህ ምን ታደ
ርጋለህ፤ በዚህስ ምን አለህ፤ አሉት ።
ሚካ እንዲህ እንዲህ አድርጎ ገዛኝ ቀጠረኝም ካህንም
ሆንኩት አላቸው ። መሳ፣ ፲፯ ፲ ።
እኛ የምንሄድበት ጐዳናችንን ያቀናልን እንደሆ፣
ወደ እግዚአብሔር አመልክትልን አሉት ።
ያም ካህን በእግዚአብሔር ፊት የምትሄዱበት ያችን
ጐዳናችሁን በፍቅር አንድነት ሂዱ አላቸው ።
እነዚያም አምስት ሰዎች ሄደው ወደ ሊሳ ደረሱ፣
በሲዶና ሰዎች ሥራ አምነው ጸጥ ብለው የሚኖሩ ወገኖ
ችንም አዩ፣ ከሲዶና የራቁ ነበሩና ከሶርያ ሰዎች ጋራ
መተላለፊያ አልነበራቸውም ነበርና፣ በምድር ርስት ብዙ
ነገርን መናገር አይችሉም ነበር ። መሳ፣ ፰ ፲፩ ።
እነዚያም አምስት ሰዎች ከወንድሞቻቸው ዘንድ ወደ
አስታሔልና ወደ ሦራሕ ተመልሰው፣ ምን አስቀምጧች
ኋል፤ አሏቸው ።
ገብተን በዚያች አገር እስከ ዳርቻዎቿ ድረስ ተመላ
ልሰንበታልና፣ በሲዶና ሥርዓት ጸንተው በውስጧ የሚ
ኖሩ ወገኖችንም አይተናልና እነሳቸውም ከሲዶና የራቁ
ናቸውና ከሶርያም ሰዎች ጋራ በነገር መተዛዘን የላቸውምና ።
ያችን አገር እጅግ መልከም እንደሆነች አይተናታልና
ተነሡ በነርሱ ላይ እንውጣ፣ እናንተ ግን ዝም በሉ ያችን
አገር ትወርሷት ዘንድ ሂዶ መግባትን ቸል አትበሉ ።
ከገባችሁም በኋላ ተዘልለው ወደሚኖሩ ወገኖች ትደ
ርሳላችሁ፣ አገሪቱም ሰፊ ናት፣ እግዚአብሔር በእጃችሁ
አግብቶላችኋልና አገሪቱም በዚህ ዓለም ከተፈጠረው ነገር
ሁሉ የሚታጣባት የለም አሏቸው ።
ከዚያ ከዳን አገር ከአስታሔልና ከሦራሕ ሰይፍ ሰይፍ
የታጠቁ ስድስት መቶ ሰዎች መሣሪያቸውን ይዘው ተነሡ ።
መሳ፣ ፲፰ ፲፯ ።
ወጥተውም የይሁዳ ዕጣ በምትሆን በቀርያታርም ሰ
ፈሩ፣ ስለዚህም ያ ቦታ እስከሁን ድረስ የዳን ሰፈር ተባለ
ይኸውም ከቀርያታርም በኋላ ያለ ነው ። ኢያ፣ ፱ ፲፯ ።
ከዚያም አልፈው ወደ ደብረ ኤፍሬም ደርሰው እስከ
ሚካ ቤት ደረሱ ። መሳ፣ ፲፰ ፪ ። ፩ ሳሙ፣ ፲፬ ፲፰ ።
ሊሳ የምትባል ያችን አገር ያዩዋት ዘንድ የሄዱም
እነዚያ አምስት ሰዎች ወንድሞቻቸውን በዚህ ቤት ምስል
እንዳለ የጣኦትም ልብስ እንዳለ ተመትቶ የተሠራ ጣኦ
ትም እንዳለ ብታውቁ ዝም በላላችሁም ነበር፣ አሁንም
የምታደርጉትን ዕወቁ አሏቸው ። ዘፀ፣ ፳፫ ፬ ።
ከዚያም አልፍ ብለው በሚካ ቤት ወዳለ ካህን ወደ
ሚሆን ወደዚያ ልጅ ቤት ገብተው እጅ ነሡት ።
እሊያም ስድስት መቶ ሰዎች መሣሪያቸውን ይዘው
አፋፋቸውን ታጥቀው ነበር፣ ከዳን ልጆች ወገን የሚሆኑ
ሰዎች በበሩ ደጃፍ ተሰበሰቡ ። መሳ፣ ፲፰ ፲፩ ።
ያችን አገር ለማየት አስቀድመው ሄደው የነበሩ እነ
ዚያ አምስቱ ሰዎችም ገቡ፣ ገብተውም መልክ ያለውን
ጣኦትና ያንን ምስል ተመትቶ የተሠራውን ጣኦቱንና የጣ

ኀተ አንቀጽ ወእልክቱኒ ስድስቱ ምእት ብእሲ ይዐውሩ ንዋየ ሐቅሎሙ ቅኑታኒሆሙ ።

፲፱ ወቦኡ እሙንቱ እደው ውስተ ቤተ ሚካ ወነሥኡ ዝክተ ግልፎ ወምስለ ወተራፊን ወሰብኮ ወይቤሎሙ ዝክቱ ካህን ምንተ ትገብሩ አንትሙ ።

፳ ወይቤልዎ አርምም ወደይ እዴከ ውስተ አፉከ ወነዓ ምስሌነ ወትከውነነ አበ ወካህነ፡ ቦኑ ይኄይሰከ ትኩን ካህነ ለአሐዱ ብእሲ እምትኩን ካህነ ለነገድ ወለሕዝበ እስራኤል ።

፳፩ ወተፈሥሐ ልቡ ለውእቱ ካህን ወነሥአ ውእተ ምስለ ወተራፊነ ወግልፎ ወሰብኮ ወቦአ ማእከለ ሕዝብ ።

፳፪ ወተመይጡ ወሖሩ ወነሥኡ ኵሎ ቤቶ ወጥሪቶ ወኵሎ ክብሮ ወነድኡ ቅድሜሆሙ ።

፳፫ ወእንበለ ይርኃቁ እምቤት መጽአ ሚካ ወእደው ሕዝብ እለ ቅድመ ቅሩበ ቤቱ ለሚካ ወጸርሑ እምድኅሬሆሙ ለደቂቀ ዳን ወአውየዉ ሎሙ ለደቂቀ ዳን ።

፳፬ ወሚጡ ገጾሙ ደቂቀ ዳን ወይቤልዎ ለሚካ ምንተ ኮንከ ዘትጸርሕ ።

፳፭ ወይቤሎሙ ሚካ ግልፎየኒ ዘገበርኩ ነሣእክሙኒ ወካህነኒ ወሖርክሙ ወምንተ እንከ ኀደግሙ ሊተ ዘትብሉኒ ምንተ ትጸርሕ ።

፳፮ ወይቤልዎ ደቂቀ ዳን ኢይሰማዕ እንከ ቃልከ ምስሌነ ወእመ አኮሰ ይትራከቡከ እደው መሪራነ ነፍስ ወታሐጕል ዓዲ ነፍሰከኒ ወነፍሰ ቤትከኒ ።

፳፯ ወሖሩ ደቂቀ ዳን ፍኖቶሙ ወርእየ ሚካ ከመ ይጸንዕዎ ወተመይጠ ወአተወ ቤቶ ።

፳፰ ወእሙንቱሰ ነሥኡ ኵሎ ዘገብረ ሚካ ወካህነኒ ወኵሎ ዘቦ ወሖሩ እስከ ሊሳ ላዕለ ሕዝብ ዘተአሚኖ ይነብር፡ ወቀተልዎሙ በአፈ ሐፂን ወሀገሮሙኒ አውዐዩ በእሳት ።

፳፱ ወአልቦ ዘድኅነ እስመ ርኁቃን እሙንቱ እምነ ሲዶና ወአልቦሙ ትልሐፍ ምስለ ባዕድ ሰብእ ወይእቲሰ ውስተ ቈላት እንተ ቤተ ጠብ፡ ወሐነጽዋ ለይእቲ ሀገር ወነበሩ ውስቴታ ።

፴ ወሰመዩ ስማ ለይእቲ ሀገር ዳን በስመ አቡሆሙ ዳን ዘተወልደ ለእስራኤል፡ ወስማሰ ለይእቲ ሀገር ቀዲሙ ሊሳ ።

፴፩ ወአቀሙ ሎሙ ደቂቀ ዳን ግልፎ ዘሚካ፡ ወዮናታን ወልደ ጌርሶም ወልደ ሙሴ ውእቱ ወደቂቁ ካህናት እሙንቱ ለሕዝበ ዳን እስከ አመ ፍልሰተ ምድሮሙ ።

፴፪ ወአቀሙ ሎሙ ግልፎ ዘሚካ ዘገብረ በኵሉ መዋዕል አምጣነ ነበረ ቤተ እግዚአብሔር ውስተ ሴሎም፡ ወበእማንቱ መዋዕል አልቦሙ ንጉሥ ለእስራኤል ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ሌዋዊ ወይነብር ውስተ አሐዱ

አቱን ልብስ ወሰዱ፤ ያ ካህን ግን በደጃፉ ቁሞ ነበር፤ እነ ዚያም ስድስት መቶ ሰዎች መሣሪያቸውን ይዘው አፋቸውን ታጥቀው ነበር ። መሳ፡ ፪ ፲፩፡ ፲፯ ፳ ።

እነዚያም ሰዎች ወደ ሚካ ቤት ገብተው ምስሉንና ያን መልክ ያለውን ጣኦት ተመትቶ የተሠራውን ጣኦትን የጣኦቱን ልብስ ወሰዱ፤ ያም ካህን ምን ታደርጋላችሁ፤ አላቸው ።

ዝም በል አፍህን በእጅህ ያዝና ከኛ ጋራ ሂድ፤ አባት ካህን ትሆንልናለህ፤ ለእስራኤል ወገንና ለብዙ ነገድ ካህን ከመሆን በውኑ ላንድ ሰው ካህን መሆን ይሻላሃልን፤ አሉት ። መሳ፡ ፲፯ ፲፡ ኢዮ፡ ፳፩ ፩፡ ምሳ፡ ፴ ፴፪ ።

የዚያም ካህን ልቡ ደስ አለው፤ የጣኦቱን ልብስና ያንን ምስል ተመትቶ የተሠራውን ጣኦትና መልክ ያለውን ጣኦት ይዞ ከሕዝቡ መካከል ገባ ።

እነዚያም ተመልሰው ሄዱ፤ ጥቃቅኑን ገንዘቡና ሽዙን ሁሉ ከብቱንም (ሃብቱን) ሁሉ ወስደው በፊታቸው ነዱ ።

ከቤቱም ሳይርቁ ሚካ መጣ፤ በሚካ ቤት አቅራቢያ አንጻር ያሉ ወገኖች ሰዎችም መጡ፤ በዳን ልጆች በስተ ኋላ ሁነውም ጮኹ፤ ለዳን ልጆችም ጮኹላቸው ።

የዳንም ልጆች ፊታቸውን መልሰው ሚካን የምት ጮኽ ምን ሁነህ ነው፤ አሉት ። መሳ፡ ፲፰ ፳፬ ፯ ፴፬ ።

ሚካም የሠራሁት ጣኦቴንም ካህኑንም ይዛችሁብኝ ሂዳችሁ ለኔ ምን ተዋችሁልኝ፤ ለምን ትጮኻለህ ትሉኛላችሁን፤ አላቸው ። ዘፍ፡ ፴፩ ፴ ።

የዳንም ልጆች እንግዲህ ቃልህ በኛ ዘንድ አይሰማ፤ ይህስ ካልሆነ ቁጡቁጡ ሰዎች ይገናኙኻል፤ ዳግመኛ ሰውነትህንና የወገኖችህን ሰውነት ታጠፋለህ አሉት ።

የዳን ልጆችም ጕዳናቸውን ሄዱ፤ ሚካም እንደጸኑበት አይቶ ተመልሶ ወደ ቤቱ ገባ ።

እነዚያ ሰዎች ሚካ የሠራውን ሁሉ ካህኑንም ያለ ገንዘቡንም ሁሉ ይዘው እስከ ሊሳ ድረስ ተዘልሎ በሚኖር ወገን ላይ ሄዱ፤ በጦርም አጠፋዋቸው አገራቸውንም በእሳት አቃጠሉ ። ዘዳ፡ ፴፫ ፳፪ ። መሳ፡ ፲፰ ፯ ።

እነሳቸው ከሲዶና የራቁ ናቸውና፤ ከሌላም ሰው ጋር መተዛዘን የላቸውምና የዳነ የለም፤ ይህችም አገር በጦብ ወገን ቈላ ያለች ናት፤ ያችንም አገር ቀጽረዋት በውስጧ ኖሩ ። ኢያ፡ ፲፱ ፳፰ ። መሳ፡ ፲፰ ፯ ።

የዚያችንም አገር ስሟን ከእስራኤል በተወለደ በአባታቸው በዳን ስም "ዳን" አሏት፤ ቀድሞ ግን የዚያች አገር ስም ሊሳ ይባል ነበር ። ዘፍ፡ ፲፬ ፲፬ ።

የዳን ልጆች የሚካን ጣኦት አቆሙላቸው፤ የሙሴ ልጅ የጌርሳም ልጅ ዮናታንም እርሱና ልጆቹ አገራቸው እስኪጠፋ ድረስ ካህናት ነበሩ ። መሳ፡ ፲፫ ፩ ።

የእግዚአብሔር ቤት በሴሎም የኖረውን ያህል በዘመኑ ሁሉ የሠራውን የሚካን ጣኦት አቆሙላቸው፤ በዚያም ወራቶች ለእስራኤል ንጉሥ አልነበራቸውም ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

ከደብረ ኤፍሬም በአንድ ጕን የሚኖር አንድ ካህን

ኅብር ዘደብረ ኤፍሬም ወነሥአ ሎቱ ውእቱ ብእሲ ብእሲተ
ዕቅብተ እምቤተ ልሔም ዘይሁዳ ።
፪ ወተመዐቶ ዕቅብቱ ወኀደገቶ ወአተወት ቤተ አቡሃ
ቤተ ልሔም ዘይሁዳ ወነበረት ህየ መዋዕለ አርባዕተ
ኢውራኀ ።
፫ ወተንሥአ ምታ ወሖረ ወተለዋ ከመ ይትዓረቃ ወያ
ግብኣ ኀቤሁ፣ ወቍልዔሁ ምስሌሁ ወክልኤቱ አእዱግ
ወሖረ ቤተ አቡሃ ወርእዮ አቡሃ ለይእቲ ወለት ወሖረ
ወተቀበሎ ።
፬ ወአብኦ ውስተ ቤቱ ወነበረ ምስሌሁ ሠሉሰ መዋዕለ
ወበልዑ ወሰትዩ ወቤተ ህየ ።
፭ ወእምዝ አመ ራብዕት ዕለት ነቅሐ በጽባሕ ወተንሥአ
ይሑር፣ ወይቤሎ አቡሃ ለይእቲ ወለት ለሐሙሁ አጽንዕ
ልበከ ወብላዕ ፍተ ኅብስት ወእምዝ ተሐውሩ ።
፮ ወነበሩ ወበልዑ ክልኤሆሙ ኅቡረ ወሰትዩ፣ ወይቤሎ
አቡሃ ለይእቲ ወለት ለውእቱ ብእሲ ቢት ዮምኒ ወይትፌ
ሣሕከ ልብከ ።
፯ ወተንሥአ ውእቱ ብእሲ ይሑር ወአገበሮ ሐሙሁ
ወከዐበ ቤተ ህየ ።
፰ ወነቅሐ በጽባሕ አመ ኃምስ ዕለት ከመ ይሑር ወይቤሎ
ሐሙሁ አቡሃ ለይእቲ ወለት ብላዕ እክለ ወእምዝ ተሐውር
እስከ የዐርብ ፀሐይ ወበልዑ ወሰትዩ ክልኤሆሙ ።
፱ ወተንሥአ ውእቱ ብእሲ ከመ ይሑር ውእቱ ወዕቅ
ብቱ ወቍልዔሁ ምስሌሁ ወይቤሎ ሐሙሁ አቡሃ ለይእቲ
ወለት ናሁ መስየ ወተቈልቈለ ፀሐይ፣ ኅድር ዝየ ዮምኒ
ወንበር ዝየ ወይትፌሣሕከ ልብከ ወትገይሡ በጽባሕ ፍኖተ
ክሙ ወተአቱ ቤተከ ።
፲ ወአበየ ውእቱ ብእሲ በይተ ወተንሥአ ወሖረ ወበጽሐ
እስከ ቅድመ ኢያቡሴዎን እንተ ይእቲ ኢየሩሳሌም ወም
ስሌሁ ክልኤቱ አእዱግ ጽዑናን ወይእቲ ዕቅብቱ ምስሌሁ ።
፲፩ ወእንዘ ዓዲሆሙ ሀለዉ አንጻረ ኢያቡሴዎን ፀሐይኒ
ተቈልቈለት ጥቀ ወይቤሎ ቍልዔሁ ለእግዚኡ ነዓ ንግ
ኃሥ ውስተ ሀገረ ኢየሩሳሌም ዛቲ ወንቢት ውስቴታ ።
፲፪ ወይቤሎ እግዚኡ ኢይግኅሥ ውስተ ሀገረ ነኪር እን
ተ ኢኮነት ዘደቂቀ እስራኤል፣ ንኅልፍ እስከ ገባአን ።
፲፫ ወይቤሎ እግዚኡ ለቍልዔሁ ነዓ ንግኃሥ ውስተ አ
ሐዱ መካን ወንኅድር ውስተ ገባአን እንተ ስማ ራማ ።
፲፬ ወኀለፉ ወሖሩ እስከ ዐርበ ፀሐይ ወበጽሐሙ ገባአን
እንተ ብንያም ግኀሡ በህየ ከመ ይባኡ ወይኅድሩ ውስተ
ገባአን ።
፲፭ ወሰበ ቦኡ ወነበሩ ውስተ መርኅበ ሀገር አልቦ ዘያበው
አሙ ውስተ ቤት ወዘያኀድሮሙ ።
፲፮ ወመጽአ ብእሲ ልሂቅ እምግብሩ ወብእሲሁሰ እምደ
ብረ ኤፍሬም ወምንባሪሁ ውስተ ገባአን ወሰብአ ብሔርሰ
ደቂቀ ብንያም ።
፲፯ ወነሆሩ በአዕይንቲሆሙ ወርእይዎ ለዝኩቱ ብእሲ ነጋ
ዲ ውስተ መርኅበ ሀገር ወይቤሎ ዝኩቱ ልሂቅ አይቴ
ተሐውር ወእምአይቴ መጻእከ ።

ሰው ነበረ፣ ያም ሰው የይሁዳ ዕጣ ከምትሆን ከቤተ ል
ሔም አንዲት ሴት አግብቶ ይኖር ነበር ።
ሚስቱም ተጣላችው፣ ትታውም የይሁዳ ዕጣ በምት
ሆን በቤተ ልሔም ወደ አባቷ ሄደች፣ በዚያም አራት
ወር ተቀመጠች ። መሳ፡ ፲፩ ፴፡ ፲፯ ፩ ።
ባሏም ተነሥቶ ተከትሏት፣ ታርቆ ወደሱ ይመልሳት
ዘንድ ሄደ፣ ብላቴናውም ከሱ ጋራ ሂዶ ነበር፣ ሁለት አህ
ዮችም ጭነው ነበር፣ ወደዚያች ልጅ አባት ቤትም ሄደ፣
የዚያች ልጅ አባትም አየው፣ ሂዶም ተቀበለው ።
ወደ ቤቱም አግብቶት ከሱ ጋራ ሦስት ቀን ተቀመጠ፣
በልተውና ጠጥተውም በዚያ አደረ ።
ከዚህ በኋላ በአራተኛይቱ ቀን ማለዳ ነቅቶ ለመሄድ
ተነሣ፣ የዚያችም ልጅ አባት አማቹን ልቡናህን አጽን
ተህ እምበሽህን ብላ ከዚህ በኋላ ትሄዳላችሁ አለው ።
ሁለቱም አንድነት ተቀምጠው በሉ ጠጡ፣ የዚያች
ልጅ አባትም ያንን ሰው ዛሬም እደር ልብህንም ደስ ይበ
ለው አለው ። መሳ፡ ፲፱ ፳፪፣ ፪ ሳሙ፣ ፲፫ ፳፰ ።
ያም ሰው ለመሄድ ተነሣ፣ አማቹ ግድ አለው፣ ዳግ
መኛም በዚያ አደረ ።
በአምስተኛውም ቀን ይሄድ ዘንድ ማልዶ ተነሣ፣ የዚ
ያች ልጅ አባትም አማቹን እኽል ብላ፣ ከዚያ በኋላ ፀሐይ
እስኪገበ ድረስ ትሄዳለህ አለው፣ ሁለቱም በሉ ጠጡ ።
ያም ሰው ከሚስቱ ጋር ይሄድ ተነሣ፡ ብላቴናውም
ከሱ ጋር ሊሄድ ተነሣ፣ የዚያችም ልጅ አባት አማቱን
እነሆ መሸ፣ ፀሐይም ሊገባ ደረሰ፣ ዛሬም ከዚህ እደር
ከዚህም ተቀመጥ፣ ልብህም ደስ ይበለው ሲነጋ ገሥግሣች
ሁን ትሄዳላችሁ ወደ ቤትህም ትገባለህ አለው ።
ያም ሰው አላድር ብሎ ተነሥቶ ሄደ፣ እስከ ኢያቡሴ
ዎን አፍዛዣም ደረሱ ይችውም ኢየሩሳሌም ናት፣ ከሱ
ም ጋር ሁለት የተጫኑ አህዮች ነበሩ፣ ያችም ሚስቱ
ከሱ ጋራ ነበረች ። ኢያ፡ ፲፭ ፷፫ ።
ገና በኢያቡሴዎን አንጻር ሳሉ ፀሐይ ፈጽሞ ሊገባ
ደርሶ ነበር፣ ብላቴናውም ጌታውን ገና ወደዚች ወደ ኢየ
ሩሳሌም እንግባ በዚም እንደር አለው ።
ጌታውም የእስራኤል ዕጣ ወዳልሆነች ወደ ባዕድ መን
ደር አልገባም፣ ወደ ገባአን እንለፍ አለው ።
ጌታውም ወደ አንድ ቦታ ገብተን በገባዖን ሰጊ
ራማ ከምትባል መንደር እንደር አለው ።
ፀሐይ እስኪገባ ድረስ አልፈው ሄዱ፣ የብንያም ዕፃ
ወደ ምትሆን ወደ ገባዖንም በደረሱ ጊዜ ገብተው በገባ
ዖን ያድሩ ዘንድ ወደዚያ አቀኑ ።
ገብተውም ከአገሩ አደባባይ በተቀመጡ ጊዜ፣ ወደ
ቤት አግብቶ የሚያሳድራቸው አላገኙም ። መሳ፡ ፲፱ ፲፰ ።
ሽማግሌ ሰው ከሥራው መጣ፡ ሰውዬው ግን በደብረ
ኤፍሬም ነበር፣ የሚኖረውም በገባዖን ነበር፣ የዚያ አገር
ሰዎች ግን የብንያም ልጆች ነበሩ ።
በዓይናቸውም ተመልክተው ያንን አልፎ ሂያጅ ሰው
በአገሩ አደባባይ አዩት፣ ያም ሽማግሌ ሰው ወዴት ትሄዳ
ለህ፤ ከየትስ መጣህ፤ አለው ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይቤሉ ኀለፍት ንሕነ እምቤተ ልሔም ዘይሁዳ እስከ አመ ንበጽሕ ደብረ ኤፍሬም እስመ እምህየ አነ ወሖርኩ እስከ ቤተ ልሔም ዘይሁዳ ወአአቱ ቤትየ ወአልቦ ዘአግኀሠኒ ውስተ ቤቱ ። | ፲፰ | ወደ ደብረ ኤፍሬም እስክንደርስ ድረስ የይሁዳ ዕጣ ከምትሆን ከቤተ ልሔም አልፈን የምንሄድ ነን ፣ እኔም ከዚያ ነኝና የይሁዳ ዕጣ ወደምትሆን ወደ ቤተ ልሔም ሂጄ ነበር ፣ አሁንም ወደ ቤቴ እመለሳለሁ ፣ ወደ ቤቱም ያገባኝ የለም ። |
| ወኀሠርኒ ወእክልኒ ብነ ለአእዱጊነ ወኅብስትኒ ወወይንኒ ብነ ለአመትክኒ ወላገብርክኒ ወለቍልዔክኒ አልቦ ዘነኀጥአ እምኵሉ መፍቅድነ ። | ፲፱ | ለአህዮቻችንም ገለባ (ገፈራ) አለን ፣ ለኛልጋይህ ለሚስቱም ለባሪያቴናህም ወይንና እምበሻ አለን ፣ ከምንፈልገው ሁሉ የምናጣው የለም አለው ። |
| ወይቤሎ ዝክቱ ብእሲ ልሂቅ ሰላም ለከ ወኵሉ ዘአልብከ ላዕሌየ ወባሕቱ ውስተ መርኅብሰ ኢትኅድር ። | ፳ | ያም ሽማግሌው ሰው ደስ ይበልህ ፣ ላንተ የሌለህ ሁሉ ከኔ ዘንድ አለ ፣ ነገር ግን በአደባባይ አትደር አለው ። |
| ወአብአ ውስተ ቤቱ ወአቅምሐ ለአእዱጊሁ ወሐፀቡ እገሪሆሙ ወበልዑ ወሰትዩ ። | ፳፩ | ወደ ቤቱም አገባው ፣ ለአህዮቹም ገፈራ ጣለላቸው ፣ እግራቸውንም አጠባቸው ፣ በሉም ጠጡም ። |
| ወእምዝ ሰበ ተፈሥሐሙ ልበሙ ናሁ ደቂቀ ኃጥአን ሰብአ ሀገር ዐገትዎ ለውእቱ ቤት ወጐድጐዱ ኆኅቶ ወይቤልዎ ለዝክቱ ብእሲ ልሂቅ በዓለ ቤት አውፅአ ለዝክቱ ብእሲ ዘቦአ ውስተ ቤትከ ከመ ንሕሮ ። | ፳፪ | ከዚህ በኋላ በልተው ጠጥተው ልቡናቸውን ደስ ባለው ጊዜ እነሆ ኃጥአን የሚሆኑ የአገሩ ሰዎች ያንን ቤት ከበቡት ፣ በሩንም ደበደቡ ፣ ያነንም የቤቱ ባለ ቤት ሽማግሌ ሰው እንደርስበት ዘንድ ወደ ቤትህ የገባውን ያንን ሰው አውጣልን አሉት ። ዘፍ፣ ፲፱ ፩ ። ዘዳ፣ ፲፫ ፲፫ ። |
| ወወፅአ ኀቤሆሙ ዝክቱ ብእሲ በዓለ ቤት ወይቤሎሙ ሐሰ ለክሙ አኀዊነ ኢትግበሩ እኩየ እምድኅረ ቦአ ብእሲ ውስተ ቤትየ ኢትግበሩ ዘንተ ዕበደ ። | ፳፫ | ያም የቤቱ ጌታ ሰው ወደነሳቸው ወጥቶ ወንድሞቼ ! ለናንተ አገባባችሁ አይደለም ሰውዬው ወደ ቤቴ ከገባ በኋላ ክፉ ነገር አታድርጉ ፣ ይህን ስንፍና አትሥሩ ። |
| ናሁ ወለትየ ድንግል ወዕቅብቱ ወአውፅአን ወአኀሥርዎን ወግበሩ ላዕሌሆን ዘይኤድመክሙ በውስተ አዕይንቲክሙ ወላዕለ ዝክቱሰ ብእሲ ኢትግበሩ ዘንተ ነገረ ዕበድ ። | ፳፬ | እነሆ ሚስቱና ክወንድ ያልደረሰች ልጄ አሉ ፣ እነሱን ላምጣላችሁ አዋርዱዋቸው ፣ በነሱ ላይ ለዓይናችሁ ደስ የሚያሰኛችሁን አድርጉ ፣ በዚህ ሰው ግን ይህን የስንፍና ሥራ አታድርጉ አላቸው ። ዘፍ፣ ፲፯ ፯ ። ዘዳ፣ ፳፩ ፲፬ ። |
| ወኢፈቀዱ እሙንቱ ሰብእ ይስምዕዎ ፣ ወነሥአ ዝክቱ ብእሲ ለዕቅብቱ ወአውፅአ አፍአ ኀቤሆሙ ወአኃሠርዋ ወተዋነይዋ ኵላ ሌሊተ እስከ ጸብሐ ወፈነውዋ ሰበ ሠርገ ጎሕ ። | ፳፭ | እነዚያም ሰዎች ይሰሙት ዘንድ አልወደዱም ፣ ያም ሰው ሚስቱን ይዞ ወደነሳቸው አወጣት ፣ አዋረድዋት ፣ እስኪነጋም ድረስ በፈረቃ ተጫወቱባት ፣ ጎህ በቀደደ ጊዜም ለቀቁዋት ። ፩ ሳሙ፣ ፴፩ ፬ ። |
| ወመጽአት ይእቲ ብእሲት በጽባሕ ወወድቀት ኀበ መድረከ ኆኅት ዘውእቱ ብእሲ በዓለ ቤት ኀበ ሀለወ ሀየ እግዚኣ እስከ ጸብሐ ። | ፳፮ | ያችም ሴት ሲነጋ መጥታ በዚያ ባሏ ባለበት በቤቱ ጌታ ሰው ደጃፍ መድረክ ላይ እስኪነጋ ድረስ ወደቀች ። መዝ፣ ፵፯ ፫ ። |
| ወተንሥአ እግዚኣ በጽባሕ ወአርኀወ ኆኅተ ውእቱ ቤት ወወፅአ ከመ ይሑር ፍኖቶ ወረከባ ለዕቅብቱ ውድቅተ ኀበ ኆኅተ ውእቱ ቤት ወእደዊሃ ላዕለ መድረክ ። | ፳፯ | ባልዋ ማለዳ ተነሥቶ የዚያን ቤት ደጃፍ ከፈተ ፣ ጐዳናውንም ይሄድ ዘንድ ቢወጣ ሚስቱን በዚያ ቤት ደጃፍ ወድቃ እጆቿን በመድረኩ ላይ ዘርግታ አገኛት ። |
| ወይቤላ ተንሥኢ ንሑር ወኢያውሥአቶ እስመ ሞተት ፣ ወጸዐና ዲበ አድጉ ወተንሥአ ውእቱ ብእሲ ወአተወ ብሔሮ ። | ፳፰ | ተነሺ እንሂድ አላት ፣ ሙታለችና አልመለሰችለትም በህያውም ላይ ጭናት ያ ሰው ወደ አገሩ ተመለሰ ። መሳ ፳ ፫ ። |
| ወቦአ ቤቶ ወነሥአ መጥባሕተ ወአኀዘ ለዕቅብቱ ወመተራ እመለያልየ አዕፅምቲሃ ዐሠርተ ወክልኤተ ክፍለ ረሰያ ወፈነዋ ውስተ ሕዝበ እስራኤል ። | ፳፱ | ወደ ቤቱ ገብቶ ሰይፍን አምጥቶ ሚስቱንም ይዞ ከየአጥንቶቿ መለያያ ላይ ቈራርጦ ዓሥራ ሁለት ክፍል አደረጋት ፣ ወደ እስራኤልም ወገኖች ሰደዳት ። |
| ወእምዝ ኵሉ ዘርእያ ይቤ አልቦ አመ ኮነ ከመዝ ወአልቦ አመ አስተርአየ እምአመ ወፅኡ እስራኤል እምግብጽ እስከ ዮም ። | ፴ | ከዚህ በኋላ ያያት ሁሉ እስራኤል ከግብጽ ከወጡ ጀምሮ እስከሁን ድረስ እንዲህ ያለ ነገር ተደርጎም ታይቶም አያውቅም አለ ። |
| ወአዘዞሙ ውእቱ ብእሲ ለእልክቱ ሰብእ እለ ፈነዎሙ ወይቤሎሙ ከመዝ በልዎሙ ለኵሉ ሰብአ እስራኤል ቦኑ አመ ኮነ ከመዝ እምአመ ወፅኡ ደቂቀ እስራኤል እምግብጽ እስከ ዮም ፣ ወረስዩ ለክሙ ምክረ ወተናገሩ ዘይሔኒ ። | ፴፩ | ያም ሰው የላካቸውን እነዚያን ሰዎች የእስራኤልን ወገኖች ሁሉ እንዲህ በሏቸው ፣ የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ከወጡ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በውኑ እንደዚህ ተደርጎ ያውቃልን ፤ እናንተ ምክር አድርጉ የሚሆነውን ነገር ተነጋገሩ ብሎ አዘዛቸው ። መሳ፣ ፳ ፯ ። ኢሳ፣ ፰ ፲ ። |

ምዕራፍ ፳።

፩ ወወፅኡ ኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል ወአንገለጉ ወተጋብኡ ኵሉ ማኅበሮሙ ከመ አሐዱ ብእሲ እምዳን እስከ ቤርሳቤሕ ወገለዓድኒ ውስተ መሴፋ።

፪ ወቆሙ ኵሉ ሕዝብ ወኵሉ ነገደ እስራኤል ውስተ ማኅበሮሙ ወኵሉ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር አርባዕ እልፍ አጋር ዘይጸውሩ ኲናተ።

፫ ወሰምዑ ደቂቀ ብንያም ከመ ተጋብኡ ደቂቀ እስራኤል ውስተ መሴፋ ወይቤሉ ደቂቀ እስራኤል አይድዑነ በአይቴ ኮነት ዛቲ እኪት።

፬ ወአውሥአ ዝክቱ ካህን ሌዋዊ ምታ ለእንታክቲ ብእሲት እንተ ቀተሉ ወይቤ በገባአን ዘብንያም መጻእኩ አነ ወዕቅብትየ ንኅድር።

፭ ወተንሥኡ ላዕሌነ ሰብአ ገባአን ወዐገቱ ዲቤነ ውእተ ቤተ ሌሊተ ወኪያየ ፈቀዱ ይቅትሉኒ ወለዕቅብትየሰ አኅሠርዋ ወተዋነይዋ ወሞተት።

፮ ወነሣእክዋ ለዕቅብትየ ወመተርክዋ በበመለያልይ ወፈነውኩ ውስተ ኵሉ ደወለ ርስቶሙ ለእስራኤል እስመ ገብሩ ዐበደ ውስተ እስራኤል።

፯ ወናሁ ኵልክሙ አንትሙ ደቂቀ እስራኤል ዝየ አቅሙ ለክሙ ቃለ ወምክረ።

፰ ወቆሙ ኵሉ ሕዝብ ከመ አሐዱ ብእሲ ወይቤሉ ኢንአቱ አብያቲነ ወኢንገብእ በሐውርቲነ።

፱ ወይእዜኒ ከመዝ ግበሩ ላዕለ ገባአን ነዐርግ ላዕሌሆሙ በበመክፈልትነ።

፲ ወንነሥእ በበዐሠርቱ እደው ለምእት ለኵሉ ሕዝበ እስራኤል ወከማሁ ምእተ ለዐሠርቱ ምእት፤ ወዐሠርተ ምእተ ለእልፍ እለ ይፀውሩ ስንቀ ለሕዝብ ውስተ ፍኖት ለእለ የሐውሩ ይትቃተልዎሙ ለገባአን ዘብንያሚ በበይነ ኵሉ ዐበድ እንተ ገብሩ ላዕለ እስራኤል።

፲፩ ወተጋብኡ ኵሉ እስራኤል እምአህጉሪሆሙ፤ ወለአኩ ሕዝበ እስራኤል ውስተ ኵሉ ነገደ ብንያሚ እንዘ ይብሉ ምንት ዛቲ እኪት እንተ ኮነት በውስቴትክሙ።

፲፪ ወይእዜኒ አምጽኡ እደወ እለ አበሱ በገባአን ደቂቀ ዓመፃ ወንቅትሎሙ ወናወፅእ እኪተ እምደቂቀ እስራኤል ወአበዩ ደቂቀ ብንያሚ ሰሚዖቶሙ ለደቂቀ እስራኤል።

፲፫ ወተጋብኡ ደቂቀ ብንያሚ እምአህጉሪሆሙ ውስተ ገባአን ከመ ይፃኡ ይትቃተልዎሙ ለደቂቀ እስራኤል።

፲፬ ወተኈለቁ ደቂቀ ብንያሚ በይእቲ ዕለት እምአህጉሪሆሙ ክልኤቱ እልፍ ወኀምሳ ምእት ብእሲ እለ ይፀውሩ ኲናተ እንበለ እለ ይነብሩ ውስተ ገባአን።

፲፭ ወእሙንቱኒ ተኈለቁ ሰብዐቱ ምእት ወራዙት ኅሩያን እለ ክልኤሆን እደዊሆሙ የማናውያን ኵሎሙ ወኵሎሙ እሉ ወንፉያን በሞዐፍተ እብን ወየሀይጹ ሥዕርተ ወኢይስሕቱ።

፲፮ ወተኈለቁ ኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል እንበለ ደቂቀ ብንያሚ አርባዕ እልፍ ብእሲ ዐቃሬ ኲናት ወኵሎሙ እሉ እደው መስተቃትላን።

ምዕራፍ ፳።

፩ የእስራኤል ልጆች ሁሉ ወጥተው ተሰበሰቡ፤ ከዳን እስከ ቤርሳቤሕ በመሴፋ አስከለች እስከ ገለዓድም ድረስ ያሉ ወገኖቻቸው ሁሉ እንደ አንድ ሰው ሁነው ተሰበሰቡ።

፪ ሕዝቡ ሁሉ የእስራኤልም ነገድ ሁሉ በወገኖቻቸው በጠላትነት የተነሡ የእግዚአብሔርም ወገኖቹ ሁሉ ለጦር የደረሰው ተቈጥሮ አርባ እልፍ አርበኞች ናቸው።

፫ የብንያምም ልጆች የእስራኤል ልጆች በመሴፋ እንደ ተሰበሰቡ ሰሙ፤ የእስራኤልም ልጆች ይህች ክፉት የትም በታ እንደሆነች ንገሩን አሏቸው።

፬ የተገደለችው የዚያች ሴት ባል ከሌዊ የተወለደ ያ ካህንም የብንያም ዕፃ በምትሆን በገባአን ነው ብሎ መለሰ እኔም ከሚስቴ ጋራ እናድር ዘንድ መጣሁ። ዘፀ፡ ፪ ፲፬።

፭ የገባአንም ሰዎች ተነሥተው በኛ ላይ ያንን ቤት ከበቡት፤ እኔንም ይገድሉኝ ዘንድ ፈለጉ፤ ሚስቴን ግን አጕሳቈሏት፤ በፈረቃም ተጫወቱባት ሞተች።

፮ አምጥቼም በየአጥንቷ መለያያ ቈራረጥኋት በእስራኤል ዘንድ ስንፍናን አድርገዋልና በእስራኤል ርስት አውራጃ ሁሉ ሰደድኩ። መሳ፡ ፲፱ ፳፫-፳፱።

፯ እነሆ እናንተ የእስራኤል ልጆች ምክርንና ነገርን በዚህ ፈጽሙ። መሳ፡ ፲፱ ፴።

፰ ሕዝቡም ሁሉ እንደ አንድ ሰው ተነሥተው ወደ ቤታችን አንገባም፤ ወደ አገራችንም አንመለስም አሉ።

፱ አሁንም እንዲህ አድርጉ በየክፍላችን በገባአን ሰዎች ላይ እንዘምታለን። ኢያ፡ ፲፬ ፪። ፩ ሳሙ፡ ፩ ፳፩።

፲ በእስራኤል ላይ ስላደረጉት ስንፍና ሁሉ የብንያም ዕጣ የምትሆን የገባአንን ሰዎች ይዋጉዋቸው ዘንድ ለሚሄዱ ወገኖች በጕዳና ስንቅ የሚሸከሙ ሰዎችን ከእስራኤል ወገኖች ሁሉ በመቶው ዓሥር ዓሥር እንደዚሁም ለሺው መቶ መቶ ለእልፉም ሺሕ ሺሕ እንሰዳለን አሉ።

፲፩ እስራኤል ሁሉ ከአገሮቻቸው ተሰብስበው የእስራኤል ወገኖች ሁሉ በናንተ የተደረገች ይህች ክፉት ምንድር ናት፤ ብለው ወደ ብንያም ነገድ ሁሉ ላኩ።

፲፪ አሁንም በገባአን የበደሉ ሰዎችን እንግደላቸው፤ ከእስራኤል ልጆች ክፉትን እናውጣ አሏቸው፤ የብንያምም ልጆች የእስራኤልን ልጆች አንሰማችሁም አሏቸው።

፲፫ የብንያምም ልጆች የእስራኤልን ልጆች ወጥተው ይዋጉዋቸው ዘንድ ከአገሮቻቸው ወጥተው በገባአን ተሰበሰቡ።

፲፬ የብንያምም ልጆች ከአገሮቻቸው ተሰብስበው በዚያች ቀን ተቈጠሩ፤ በገባአን ከሚኖሩት በቀር ለጦር የደረሱት ሁለት እልፍ አምስት ሺሕ ናቸው። ዘኍ፡ ፩ ፴፯፣ ፳፮ ፵፩።

፲፭ እነዚያም የተመረጡ ሰባት መቶ አርበኞች ተቈጠሩ፤ ሁሉም በቀኛቸውና በግራቸው የሚወረውሩ ናቸው፤ እነዚህም ሁሉ በወንጭፍ ድንጊያ የሚወረውሩ የማይስቱ ከራስ ጠጕር ለይተው የሚመቱ ናቸው።

፲፮ ከብንያም ልጆች በቀር የእስራኤል ልጆች ሁሉ ተቈጥረው ለጦር የደረሱ አርባ እልፍ ሆኑ፤ እነዚያም ሁሉ አርበኞች ናቸው። ዘኍ፡ ፩ ፵፮፣ ፳፮ ፶፩።

፲፯ ወተንሥኡ ወዐርጉ ውስተ ቤቴል ወተሰአሉ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤሉ ደቂቀ እስራኤል መኑ የዐርግ ለነ መስፍነ ዘይትቃተሎሙ ለነ ለብንያሚ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ይሁዳ ይዕርግ ለክሙ መስፍነ ።

ተነሥተውም ወደ ቤቴል መጡ፤ እግዚአብሔርንም ጠየቁ፤ የእስራኤል ልጆች የብንያምን ልጆች ወጥቶ የሚዋጋልን መስፍን ማን ነው፤ አሉ እግዚአብሔርም ይሁዳ መስፍን ሁኖ ይውጣላችሁ አላቸው ። ዘኁ፡ ፳፯ ፳፩ ።

፲፰ ወተንሥኡ ደቂቀ እስራኤል ወኀደሩ ላዕለ ገባኦን ።

የእስራኤልም ልጆች ተነሥተው በገባኦን ሰፈሩ ።

፲፱ ወወፅኡ ኵሎሙ አደወ እስራኤል ውስተ ቀትል ምስለ ብንያሚ ወተአኀዝዎሙ በገባኦን ።

የእስራኤልም አርበኞች ሁሉ ከብንያም ልጆች ጋራ ለመዋጋት ወደ ሰልፍ ወጥተው በገባኦን ተያያዙዋቸው (ተቈራቈሷቸው) ።

፳ ወወፅኡ ደቂቀ ብንያሚ እምሀገር ወቀተሉ እምእስራኤል ክልኤተ እልፈ ወዕሥራ ምእተ ብእሴ ይእተ አሚረ እለ ወድቁ ውስተ ምድር ።

የብንያምም ልጆች ከአገር ወጥተው ከእስራኤል ወገን ሁለት እልፍ ከሁለት ሺሕ ሰው ገደሉ፤ የዚያን ጊዜ ገደል ገብተው የሞቱ ብዙ ናቸው ።

፳፩ ወተጸንዑ ደቂቀ እስራኤል ወዳግመ ወፅኡ ይትቃተሉ ውስተ ዝክቱ መከን ኀበ ተቃተሉ አመ ቀዳሚት ዕለት ሀየ ።

የእስራኤልም ልጆች በዚያች ቀን ተጸናንተው በመጀመሪያው ቀን በዚያ ወደ ተዋጉበት ዳግመኛ ይዋጉ ዘንድ ወደዚያ ቦታ ወጡ ።

፳፪ ወዐርጉ ደቂቀ እስራኤል ወበከዩ ቅድመ እግዚአብሔር እስከ ሠርክ ወተሰአሉ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤሉ ንድግምኑ ዳዲ ተቃትሎ ምስለ ብንያሚ እኁነ፤ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ዕርጉ ኀቤሆሙ ።

የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት እስከ ሠርክ ድረስ አለቀሱ፤ ከወንድማችን ከብንያም ልጆች ጋራ ዳግመኛ እንዋጋለንን፤ ብለው እግዚአብሔርን ጠየቁ፤ እግዚአብሔርም ወደነሳቸው ውጡ አላቸው ።

፳፫ ወመጽኡ ደቂቀ እስራኤል ኀበ ብንያሚ አመ ሣኒታ ዕለት ።

የእስራኤልም ልጆች በሁለተኛው ቀን ወደ ብንያም ልጆች መጡ ።

፳፬ ወወፅኡ ብንያሚ ወተቀበልዎሙ ወተቃተልዎሙ አመ ሣኒታ ዕለት እምገባኦን ወቀተሉ እምኔሆሙ እልፈ ወሰማንያ ምእተ ብእሴ እለ ወድቁ ውስተ ምድር ወኵሎሙ እለ ይፀውሩ ኵናተ ።

የብንያምም ልጆች ወጥተው ተቀበሏቸው፤ በማግሥቱም ዕለት በገባኦን ተዋጉዋቸው ከነሳቸውም እልፍ ከስምንት ሺሕ ሰዎች ገደሉ፤ ገደል ወድቀው በሕር ጠልቀው የሞቱ ብዙ ናቸው፤ ሁሉም ለጦር የደረሱ ናቸው ።

፳፭ ወዐርጉ ኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል ወኵሉ ሕዝብ ወሖሩ ውስተ ቤቴል ወበከዩ ወነበሩ ሀየ ቅድመ እግዚአብሔር ወጾሙ ደቂቀ እስራኤል እስከ ሠርክ ወአዕረጉ መሥዋዕተ መድኀኒት ለእግዚአብሔር ።

የእስራኤል ልጆች ሁሉ ወጡ፤ ሕዝቡም ሁሉ ወጥተው ወደ ቤቴል ሂደው አለቀሱ፤ በዚያም በእግዚአብሔር ፊት ተቀምጠው የእስራኤል ልጆች እስከ ሠርክ ድረስ ጾሙ፤ ድኅነት የሚያሰጥ መሥዋዕትንም ለእግዚአብሔር አቀረቡ ። መሳ፡ ፩ ፲፫ ።

፳፮ ወተስእሉ ደቂቀ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር ወሀለወት ሀየ ታበተ እግዚአብሔር በእማንቱ መዋዕል ።

የእስራኤል ልጆች ወደ እግዚአብሔር ጠየቁ፤ በዚያ ወራት የእግዚአብሔር ማደሪያ (ታቦት) በዚያ ነበረች።

፳፯ ወፊንሐስ ወልደ አልአዛር ወልደ አሮን ይቀውም ቅድሜሃ በእማንቱ መዋዕል ወይቤሉ ንድግምኑ ዳዲ ወፂአ ውስተ ቀትል ምስለ ደቂቀ ብንያሚ እኁነ አው ንኅድግ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ዕርጉ እስመ ጌሠመ አገብአሙ ውስተ እዴክሙ ።

የአሮን ልጅ የአልአዛር ልጅ ፊንሐስ በዚያ ወራት ከፊቷ ይቆም ነበር፤ ከወንድማችን ከብንያም ልጆች ጋራ ለመዋጋት አሁን ዳግመኛ እንውጣ ወይስ እንውጣ፤ አሉ፤ እግዚአብሔርም፣ ነገ በእጃችሁ እጥላቸዋለሁና ውጡ አላቸው ። ዘኁ፡ ፳፭ ፯ ። ዘዳ፡ ፲ ፰ ።

፳፰ ወአንበሩ ደቂቀ እስራኤል እለ የዐግትዋ ለገባኦን ዐውዳ ።

የእስራኤም ልጆች ገባአንን ዙርያዋን የሚከቡዋትን ሰዎች አኖሩ ። ኢያ፡ ፫ ፬ ።

፳፱ ወተአኀዝዎሙ ደቂቀ እስራኤል ለብንያሚ አመ ሣልስት ዕለት ወተቃተልዎሙ በኀበ ገባኦን ከመ ቀዲሙ ።

የእስራኤል ልጆች በሦስተኛዪቱ ቀን የብንያሚን ልጆች ተያያዙዋቸው እንደቀደመውም በገባኦን ይዋጉዋቸው ጀመር ።

፴ ወወፅኡ ደቂቀ ብንያሚ ወተቀበልዎሙ ለሕዝብ ወጕዩ እምኀበ ሀገር ወአኀዙ ይትቃተሉ እምሕዝብ ከመ ቀዲሙ በውስተ ፍኖት አሐቲ እንተ ታዐርግ ለቤቴል ወአሐቲ እንተ ታዐርግ ለገባኦን በውስተ ገዳም ወየአክሉ ሠላሳ እልፍ ብእሲ እምእስራኤል ።

የብንያምም ልጆች ወጥተው ሕዝቡን ተቀበሏቸው፤ ከሀገሩም ሸሹ፤ ከሕዝቡም እንደቀደመው አንዲቱ ወደ ገባአን በምታወጣ አንዲቱ ወደ ቤቴል በምታወጣ ጐዳና ይዋጉ ጀመር፤ በምድረ በዳ ከእስራኤል ሠላሳ እልፍ የሚሆኑ ሰዎች ነበሩ ። መሳ፡ ፳ ፲፰፤ ፳፩ ፪፤ ፲፪ ፲፱ ።

፴፩ ወይቤሉ ደቂቀ ብንያሚ ይመውቱ ቅድሜነ ከመ ቀዲሙ፤ ወይቤሉ ደቂቀ እስራኤል ንጕየይ ወናርኅቆሙ እም ሀገር ውስተ ፍናው ።

የብንያሚም ልጆች እንደቀደመው በፊታችን ይሞታሉ አሉ፤ የእስራኤልም ልጆች ሸሽተን ከከተማ ወደ ጐዳና እናርቃቸው አሉ ። ኢያ፡ ፰ ፭-፯ ።

፴፫ ወተንሥኡ ኵሎሙ እደወ እስራኤል እምነ መካኖሙ ወተቃተሉ በበዓልታምር፣ ወማዕገቶሙኒ ለእስራኤል ተበ እሱ በመካኖሙ እምዐረቢሃ ለገባእን ።

፴፬ ወገብኡ እንተ ቅድሜሃ ለገባእን እልፍ ብእሲ ኅሩያን እምእስራኤል ወጸንዐ ቀትል፣ ወእሙንቱሰ ኢያእመሩ ከመ በጽሐቶሙ እከዮሙ ።

፴፭ ወአውደቆሙ እግዚአብሔር ለብንያሚ ቅድመ እስራ ኤል ወቀተልዎሙ ደቂቀ እስራኤል ለብንያሚ ክልኤቱ እልፍ ወሐምሳ ምእት ወአሐዱ ምእት፣ ወኵሎሙ እለ ይፀውሩ ኲናተ ።

፴፮ ወርእየ ብንያሚ ከመ ተቀትለ ወወሀብዎሙ እስራኤል መካነ እስመ ተአመኑ በማዕገቶሙ ዘሜሙ ላዕለ ገባእን ።

፴፯ ወሖሩ እልክቱ እለ ዐገቱ ወቀተልዋ ለሀገር በአፈ ሐፂን ።

፴፰ ወአዘዝዎሙ እስራኤል ለእለ የዐግቱ ከመ በሐፂን ይቀትልዎሙ ወያዐርግዎ ለጢስ ሀገር ከመ ማኅፈድ ።

፴፱ ወተመይጡ እደወ እስራኤል በውስተ ቀትል ወለብን ያምሰ አኀዝዎ ይቅትልዎ እደወ እስራኤል ወየአክሉ ስድ ስተ ምእተ ብእሴ እስመ ይቤ እንበለ ይቅትሉኒ ቀተልክ ዎሙ በቅድሜየ ከመ ቀትል ዘቀዲሙ ።

፵ ወዝክቱ ጢሰ ማኅፈድ የዓርግ እምሀገር ከመ ዐምድ ወነጸረ ብንያሚ ድኅሬሁ ወናሁ ዐርገ ጥፍአተ ሀገር ው ስተ ሰማይ ።

፵፩ ወተመይጡ እደወ እስራኤል ወተወላወሉ እደወ ብን ያሚ ወርእዩ ከመ በጽሐቶሙ እከዮሙ ።

፵፪ ወነትዑ ቅድሚሆሙ ለእስራኤል ውስተ ፍኖተ ገዳ ም፣ ወበጽሖሙ ቀትል ወእለኒ እምሀገር ቀተልዎሙ በማ እከሎሙ ።

፵፫ ወቀተልዎሙ ለብንያሚ ወአጥፍእዎሙ ወደምሰሰ ደምሰስዎሙ በቅድመ ገባእን መንገለ ጽባሒሃ ።

፵፬ ወወድቁ እምብንያሚ እልፍ ወሰማንያ ምእት ብእሲ ወኵሎሙ እሉ ጽኑዓን እደው ።

፵፭ ወጐዩ ኀበ ኰኵሐ ሬሞን ወአርአይዎሙ በፍኖት ኀ ምሳ ምእተ ብእሴ ወዴገንዎሙ ወቀተልዎሙ እስከ ጌዴ አም ወቀተሉ እምኔሆሙ ዕሥራ ምእተ ብእሴ ።

፵፮ ወኮኑ ኵሎሙ እለ ወድቁ እምብንያሚ ክልኤቱ እልፍ ወሐምሳ ምእት ወእሐዱ ምእት ብእሲ እለ ይፀውሩ ኲና ተ በይእቲ ዕለት ወኵሎሙ እሉ እደው ጽኑዓን ።

፵፯ ወነትዑ ወጐዩ ውስተ ኰኵሐ ሬሞን ስድስቱ ምእት ብእሲ ወነበሩ ውስተ ኰኵሐ ሬሞን አርባዕተ አውራኀ ።

፵፰ ወዐጸውዎሙ ሰብአ እስራኤል ለደቂቀ ብንያሚ ወቀ ተልዎሙ በአፈ ሐፂን ወሀገሮሙኒ አውዐዩ ወእንስሳሆ ሙኒ ወኵሎ ዘተረክበ ውስተ ሀገር አህጉሪሆሙኒ እለ ረከቡ አውዐዩ በእሳት ።

፴፫ የእስራኤል ወንዶች ሁሉ ከቦታቸው ተነሥተው በበ ዓልታምር ተዋጉ፣ የእስራኤልም ከባቢዎች በገባእን ግራ በቦታቸው ተዋጉ ።

፴፬ ከእስራኤል የተመረጡ እልፍ ሰዎች በገባእን አፍዘ ዝ ተመለሱ፣ ሰልፉም (ውጊያው) ጸና፣ እነሳቸው ግን የክ ፉታቸው ፍዳ እንደደረሰችባቸው አላወቁም ።

፴፭ እግዚአብሔርም የብንያሚን ልጆች በእስራኤል ፊት ጣላቸው፣ የእስራኤል ልጆች ሁለት እልፍ ከአምስት ሺሕ ከንድ መቶ የብንያሚን ልጆች ገደሉዋቸው ሁሉም ለጦር የደረሱ ናቸው ።

፴፮ የብንያም ልጆች ድል እንደተነሡ አዩ፣ እስራኤልም በገባእን በኖሩዋቸው ከባቢዎች (ድብቅ ጦር) ታምነዋልና ቦታን ለቀቁላቸው (ሰጧቸው) ።

፴፯ እነዚያም ከባቢ ጦሮች ሄደው አገሪቱን በጦር አጠ ፏት ። ዘፀ፣ ፲፱ ፲፫ ። ኢያ፣ ፰ ፲፱ ።

፴፰ እስራኤልም በጦር ያጠፉዋቸው ዘንድ የአገሪቱንም ጢስ እንደ ግንብ ያወጡት ዘንድ እነዚያን የከበቡ ሰዎች አዘዟቸው ።

፴፱ የእስራኤል አርበኞች ወደ ሰልፉ ተመለሱ በፊቴ እንደ ቀድሞው ሰልፍ ሳያጠፉኝ አጠፋቸዋለሁ ብሏልና፣ የእስ ራኤል አርበኞች ብንያሚን ያጠፉ ዘንድ ጀመሩ፣ እነዚህም ስድስት መቶ ሰዎች ያህሉ ነበሩ ። መሳ፣ ፳ ፴፩ ።

፵ ያም የግንቡ ጢስ እንደ ምሰሶ ከከተማው ቀጥ ብሎ ወጣ፣ የብንያምም ወገን ወደኋላው በየ ጊዜ እነሆ የአገሩ ጥፋት በዝቶ እንደተደረገ ዐወቀ ። መሳ፣ ፳ ፴፰ ።

፵፩ የእስራኤል ወገኖች በተመለሱ ጊዜ የብንያም ልጆች ተሸበሩ፣ የክፋታቸውም ፍዳ እንደረሰችባቸው ዐወቁ ።

፵፪ ከእስራኤል ፊት ወደ ምድረ በዳ ሸሹ፣ ሰልፍም ደረ ሰባቸው በሀገርም ያሉ ሰዎች በመካከላቸው አጠፉዋቸው ። መሳ፣ ፩ ፴፭፣ ኢያ፣ ፰ ፲፭ - ፳፬ ።

፵፫ የብንያሚንም ልጆች ወግተው አጠፉዋቸው፣ በገ በአንም አንጻር በምሥራቅ ፈጽመው አጠፉዋቸው ። ዘኍ፣ ፲ ፴፫ ።

፵፬ ከብንያሚ ልጆች ወገን እልፍ ከስምንት ሺሕ ሰዎች ወደቁ (ሞቱ)፣ እነዚህም ሁሉ አርበኞች ነበሩ ።

፵፭ ወደ ሬሞን ዋሻም ሸሹ፣ በጐዳናም አምስቱን ሺሕ ሰዎች ለቀሟቸው ተከትለውም እስከ ጌዴአም ድረስ አጠ ፏቸው፣ ከነሳቸውም ሁለት ሺሕ ገደሉ ።

፵፮ በዚያችም ቀን ከብንያም ወገን የሞቱ ለጦር የደረሱ ሰዎች ሁለት እልፍ አምስት ሺሕ ከአንድ መቶ ሆኑ፣ እነዚህም ሰዎች ሁሉ አርበኞች ነበሩ ። መሳ፣ ፳ ፴፬ - ፴፭ ።

፵፯ ስድስት መቶም ሰዎች ወደ ሬሞን ዋሻ ፈጽመው ሸሹ፣ በዚያ በሬሞንም ዋሻ አራት ወር ተቀመጡ ።

፵፰ የእስራኤል ሰዎች የብንያሚን ልጆች ዘጉባቸው፣ በጦርም አጠፉዋቸው ሀገራቸውንም ከብቶቻቸውንም በሀ ገር የተገኘውንም ሁሉ አጠፉ፣ ያገኙዋቸው አምበዎቻ ቸውን በእሳት አቃጠሉዋቸው ። ዘፍ፣ ፲፱ ፲፭ ።

## ምዕራፍ ፳፩ ።

፩ ወተማሐሉ ሰብአ እስራኤል በመሴፋ እንዘ ይብሉ ከመ ኢየሀብ ብእሲ እምኔነ ወለቶ ለብንያሚ ያስተዋስብ ።

፪ ወሖሩ ኵሉ ሕዝብ ውስተ ቤቴል ወነበሩ እስከ ሠርክ ቅድመ እግዚአብሔር ወበርሑ ወበከዩ በቢየ ብከየ ።

፫ ወይቤሉ ለምንት እግዚኦ ከነ ዝቲ እኪት በውስተ እስራኤል ከመ ትኅጸእ ዮም አሐቲ ሕዝብ እምእስራኤል ።

፬ ወእምዝ በሳኒታ ጌሡ ሕዝብ ወነደቁ በህየ ምሥዋዐ ወአዕረጉ መሥዋዕተ መድኀኒት ።

፭ ወይቤሉ ደቂቀ እስራኤል መኑ ዘኢዐርገ እማኅበር እምኵሉ ሕዝበ እስራኤል ኀበ እግዚአብሔር እስመ ዐቢይ መሐላሆሙ ከመ ዘኢዐርገ ኀበ እግዚአብሔር ውስተ መሴፋ ሞተ ለይሙት ይቤሉ ።

፮ ወተኣረቅዎ ደቂቀ እስራኤል ለብንያሚ እኁሆሙ ወይቤሉ ትወዕአት ዮም አሐቲ ሕዝብ እምእስራኤል ።

፯ ምንተ እንከ ንሬስዮሙ ለእለ ተርፉ በእንተ አንስት ናሁ መሐልነ ንሕነ በእግዚአብሔር ከመ ኢነሀቦሙ እም አዋልዲነ ያውስቡ ።

፰ ወይቤሉ መኑ እምአኃዊነ ሕዝበ እስራኤል ዘኢዐርገ ኀበ እግዚአብሔር ውስተ መሴፋ ወናሁ አሐዱ ብእሲ ኢመጽአ እምኢያቢስ ዘገለአድ ውስተ ማኅበሮሙ ።

፱ ወተፈቀዱ ሕዝብ ወናሁ አሐዱ ብእሲ ዘእምኢያቢስ ዘገለአድ ኢሀለወ ።

፲ ወለአኩ ህየ ማኅበሮሙ እልፈ ወዕሥራ ምእተ ብእሴ እምደቂቀ ኀይል ወአዘዝዎሙ እንዘ ይብሉ ሑሩ ወቅትሉ ኵሎ እለ ይነብሩ ውስተ ኢያቢስ ዘገለአድ በአፈ ሐፂን አንስተኒ ወሕዝበኒ ።

፲፩ ወከመዝ ግበሩ ኵሎ ተባዕተ ወኵሎ አንስተ እለ የአምራ ብእሴ ቀተሉ ።

፲፪ ወረከቡ እምእለ ይነብሩ ውስተ ገለአድ አርባዕተ ምእተ አዋልደ ደናግለ እለ ኢያአመራ ብእሴ ወአምጽእዎን ውስተ ትዕይንት ውስተ ሴሎ ውስተ ምድረ ከነአን ።

፲፫ ወለአኩ ኵሉ ማኅበሮሙ ኀበ ብንያሚ እለ ውስተ ኰኵሐ ሬሞን ወጸውዕዎሙ በሰላም ።

፲፬ ወገብኡ ብንያሚ ኀበ ደቂቀ እስራኤል በእማንቱ መዋዕል ወወሀብዎሙ አንስተ ዘአሕየዉ እምአንስተ ኢያቢስ ዘገለአድ ወሠምሩ በዝንቱ ።

፲፭ ወሕዝብኒ ተኳነንዎሙ ለብንያሚ እስመ ገብረ እግዚአብሔር ቀትለ በውስተ ሕዝበ እስራኤል ።

፲፮ ወይቤሉ ሊቃናተ ማኅበር ምንተ ንግበር በእንተ እለ ተርፉ ሕዝብ በበይነ አንስት እስመ ጠፍአ አንስት እምብንያሚ ።

፲፯ ወይቤሉ ርስት ተርፈ ለብንያሚ ወኢትደምሰስ ሕዝብ እምእስራኤል ።

፲፰ ወንሕነሰ ኢንክል ውሂቦቶሙ አንስተ እምአዋልዲነ እስመ መሐሉ ደቂቀ እስራኤል እንዘ ይብሉ ርጉም ውእቱ ዘይሁብ ብእሲተ ለብንያሚ ።

## ምዕራፍ ፳፩ ።

የእስራኤል ሰዎች ከኛ አንድ ሰው ሴት ልጁን ያጋባ ዘንድ ለብንያም ልጆች እንዳይሰጥ ብለው ተማማሉ ።

ሕዝቡም ሁሉ ወደ ቤቴል ሂደው እስከ ሠርክ ድረስ በእግዚአብሔር ፊት ጮኹ፤ ፈጽመውም አለቀሱ ።

አቤቱ፤ ከእስራኤል አንዲቱ ወገን አሁን ተለይታ ትወጣ ዘንድ በእስራኤል ዘንድ ይህች ክፉ ለምን ሆነች አሉ ።

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ በማግሥቱ ገሥግሠው ሂደው በዚያ መሠውያን ሠሩ፤ በዚያም የድኅነት መሥዋዕትን ሠዉ ።

የእስራኤልም ልጆች ከእስራኤል ዘንድ ወደ መሴፋ ያልወጣ ሰው ይሞት ዘንድ ይሙት ብለው የተማማሉት መሐላቸው ጽኑ ነውና፤ ከእስራኤል ወገኖች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ያልወጣ ሰው ማነው፤ አሉ ።

የእስራኤል ልጆች አሁን ከእስራኤል አንዲቱ ወገን ተለይታ ትወጣለችን ብለው የብንያምን ልጆች ታረቁዋቸው ።

ከልጆቻችን ያገቡ ዘንድ እንዳንሰጣቸው እነሆ እኛ በእግዚአብሔር ምለናልና ከሞት ለቀሩ ሰዎች ሴት ለሌላቸው እንግዲህ ምን እናደርጋቸዋለን፤ አሉ ።

ከወንድሞቻችን ከእስራኤል ወገኖች ወደ እግዚአብሔር ወደ መሴፋ ያልወጣ ማነው፤ አሉ፤ እነሆ ከገለዓድ ዕጣ ከኢያቢስ የሚሆን አንድ ሰው ወደ እስራኤል ወገኖች አልመጣም ነበር ። ፩ ሳሙ፣ ፲፩ ፩ ።

ሕዝቡም ተቈጣጠሩ እነሆ ከገለዓድ ዕጣ ከኢያቢስ ወገን የሚሆን አንድ ሰው አልነበረም ።

ከአርበኞች ልጆች ወገን አእልፍ ከሁለት ሺሕ ሰዎች የሚሆኑ ወገኖችም ሂዳችሁ የገለዓድ ዕጣ በምትሆን በኢያቢስ የሚኖሩ ሰዎችን ሁሉ በጦር ግደሉ ብለው ወደዚያ ላኩ፤ ሴቶቹንም ሕዝቡንም አጥፉ ብለው አዘዙዋቸው ።

እነሳቸውም እንዲህ አደረጉ ባል ያገቡ ሴቶችን ሁሉና ወንዶቹንም ሁሉ ገደሉ ። ዘኁ፣ ፴፩ ፲፯ ዘዳ፣ ፯ ፪ ።።

በገለዓድ የሚኖሩ ባል ያላገቡ አራት መቶ ደናግሎችን አገኙ፤ በከነዓን ምድር ወዳለችው ወደ ሴሎ ወደ ሰፈሩ አመጡቸው ። ኢያ፣ ፲፰ ፩፣ ፳፩ ፪ ።

ወገኖቻቸው ሁሉ በሬሞን ዋሻ ወዳሉ ወደ ብንያም ልጆች ልከው በፍቅር ጠሩዋቸው ። ዘዳ፣ ፳ ፲ ።

የብንያምም ልጆች በዚያ ወራት ወደ እስራኤል ልጆች ተመለሱ፤ የገለዓድ ዕጣ በምትሆን ከኢያቢስ ያዳኗቸው ሴቶችንም ሰጡዋቸው፤ በዘህም ተስማሙ ።

እግዚአብሔር ከእስራኤል ወገኖች መከከል ለልፍን አድርጎ ነበርና ሕዝቡ የብንያሚን ልጆች ተወቃቀሷቸው ።

የማኅበሩም ሽማግሌዎች ከብንያም ነገድ ሴቶች ጠፍተዋልና ከሞት ስለ ቀሩ ሰዎች የሴቶችን ነገር ምን እናድርግ፤ አሉ ።

ለብንያም ልጆች ርስት ቀረባቸው አንዲቱ ወገን ከእስራኤል ተለይታ አትጥፋ ።

ለብንያም ልጆች ሚስት የሚሰጥ ሰው ርጉም ይሁን ብለው የእስራኤል ልጆች ምለዋልና፣ እኛም ከልጆቻችን ሚስት መስጠት አንችልም አሉ ። መሳ፣ ፳፩ ፩፣ ፲፩ ፴፭ ።

፲፱ ወይቤሉ በዓለ እግዚአብሔር በሴሎ እመዋዕል በበመዋዕሊሁ ውእቱ እመንገለ መስዕ ለቤቴል ወበጽባሒሃ ለፍኖት እንተ ታዐርግ እምቤቴል ለሰቂማ ወእመንገለ አዜብ ለሌብና ።

ከአንዱ ዘመን በየወራቱ የሚደረግ የእግዚአብሔር በዓል ከቤቴል ወደ ሰቂማ በምታወጣ ጐዳና ምሥራቅና በቤቴል ግራ አንጻር በሌብናም ግራ ባለች በሴሎ ይደረጋል አሉ ፡ መሳ፡ ፲፩ ፵፡ ፩ ሳሙ፡ ፩ ፫ ።

፳ ወአዘዝዎሙ ለደቂቀ ብንያሚ ወይቤልዎሙ ሑሩ ወተኀብኡ ውስተ ዐፀደ ወይን፡ ወተዐቀቡ አዋልዲሆሙ ለእላ ይነብሩ ውስተ ሴሎም እንዘ ይትዋነያ በመሰንቆ ።

የብንያምንም ልጆች ሂዱ በወይን ቦታ ተሠወሩ በሴሎም የሚኖሩ ሰዎች ልጆቻቸውን መሰንቆ እየመቱ ሲጫወቱ ተጠባበቁ ።

፳፩ ወትወስኡ እምዓፀደ ወይን ወምስጡ ለክሙ አንስተ እምአዋልደ ሴሎም ወእትዉ ውስተ ብንያሚ ።

ከወይን ቦታ ወጥታችሁም ከሴሎም ልጆች ሏናንተ ሚስት ነጥቃችሁ ወደ ብንያም ዕጣ ተመለሱ ብለው አዘዙዋቸው ። ዘፀ፡ ፲፭ ፳ ። ፩ ሳሙ፡ ፲፰ ፯፡ ፳፩ ፲፩ ።

፳፪ ወለእመ መጽኡ አበዊሆን ወአኀዊሆን ይሰነኑክሙ ንብሎሙ መሐርዎሙ እስመ ኢያውዕኡ አንስቲያሆሙ እምቀትል እስመ እከ አንትሙ ዘወሀብክምዎሙ በእማንቱ መዋዕል ኢትነስሑ ።

ወንድሞቻቸውና አባቶቻቸውም ሊጣሉዋችሁ ቢመጡ ሚስቶቻቸውን ወደ ሰልፍ አላወጡምና ማሩዋቸው በዚያ ወራት እናንተ የሰጣችኋቸው አይደለምና አትጸጸቱ እንላቸዋለን አሉዋቸው ።

፳፫ ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ ብንያሚ ወነሥኡ አንስተ በኍላቄሆሙ እምእለ ይትዋነያ ወተማሰጥዎን ወአተዉ ወገብኡ ውስተ ርስቶሙ፡ ወነደቁ ሎሙ አህጉረ ወነበሩ ውስቴቶን።

የብንያምም ልጆች እንዳሏቸው አደረጉ፣ ከሚጫወቱት ልጆች በቍጥራቸው መጠን ሴቶችን ተጣቅሰው ይዘው ወደ ርስታቸው ተመለሱ፣ ለነሳቸውም ከተሞችን ሠርተው በውስጣቸው ተቀመጡ ።

፳፬ ወአተዉ እምህየ ደቂቀ እስራኤል ብእሲ ብእሲ ውስተ ሕዝቡ ወውስተ ነገዱ ወአተዉ እምህየ ብእሲ ብእሲ ውስተ ርስቱ ።

የእስራኤልም ልጆች ከዚያ አንዱም አንዱም ሰው ወደ ወገኑ ወደ ነገዱ ተመለሰ፣ ከዚያም አንዱም አንዱም ሰው ወደ ርስቱ ገቡ ።

፳፭ ወበእማንቱ መዋዕል አልቦሙ ንጉሥ ለእስራኤል ብእሲ ብእሲ ዘአደሞ ቅድመ አዕይንቲሁ ይገብር ።

በዚያም ወራት ለእስራኤል ንጉሥ አልነበራቸውምና አንዱም አንዱም ሰው በፊቱ የወደደውን ያደርግ ነበር ።

ተፈጸመ አሪት ዘመሳፍንት፣
ወስብሐት ለእግዚአብሔር ዘአልበቱ ጥንት ወተፍጻሜት፣
አሜን።

የመሳፍንትን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ደረሰ ተፈጸመ፣
ጥንትና ፍጻሜ ለሌለው ለእግዚአብሔር ለዘለዓለሙ ክብር ምስጋና ይግባው ።
አሜን።